## ምዕራፍ ሦስት

# ከዐድዋ እስከ ማይጨው 1888 - 1928

## የዐድዋ ድል በታሪክ ያለው ስፍራ

በቅርብ ዘመን ታሪክ ውስጥ እንደ ዐድዋ ድል ለኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ ዝናን የሰጠ ድርጊቶች ማሰብ ያዳግታል። የቅኝ አገዛዝን ማዕበል የገታ አንድ ትልቅ ድርጊት እንደመሆኑ ሁሉ የቅኝ ገዥዎችን ቅስም የሰበረውን ያህል የተገዦቹን አንገት ደግሞ ከተደፋበት ቀና እንዲል ያደረገ ክስተት ነበር። በዚህ ድል ምክንያትም የፖለቲካ መሪዎችም ሆኑ ነጋዴዎች አቋማቸውን እንደገና እንዲመረምሩ ተገደዱ። በዐድዋ ጦርነት ተረካው ለኢጣልያ ግልጽ ወገናዊነት የሚያሳየው ጆርጅ በርክሌ እንኳ የዚህን አዲስ ግንዛቤ መስፈን በሚከተለው መንገድ ይገልፅልናል፤

> ከሰፊው የፖለቲካና የታሪክ ትንታኔ አኳያ የዐድዋ ጦርነት በአፍሪቃ ምድር አዲስ ኃይል መነሣቱን የሚያበስር ይመስላል። የዚያች አህጉር ተወላጆች፣ የማይናቅ ወታደራዊ ኃይል ሊሆኑ እንደሚችሉ ልናሰላስል ተገደናል። እንዲያውም አሁን ነገሩ አስቂኝ ቢመስልም፣ ይህ ሁኔታ (ማለትም ዐድዋ) ጨለማይቱ አህጉር በላይዋ ላይ ሥልጣኗን ባንሰራፋችው በአውሮጳ ላይ የምታደርገው አመፅ የመጀመሪያው ምዕራፍ ነውም ተብሏል።

ዐድዋን ልዩ ትኩረት ያሰጠው ጥቁሮች በነጮች ላይ የተጎናፀፉት የመጀመሪያው ዐቢይ ወታደራዊ ድል በመሆኑ ነው። በዚህም ረገድ ካንድ 10 ዓመት በኋላ የነጩን ዓለም እንደገና ለማናወጥ የበቃው ጃፓን በሩሲያ ላይ ያገኘችው ድል መቅድም ነበር። ስለሆነም የዐድዋ አብነት በተለይም የነጮች የበላይነት ከአስከፊ የዘር መድልዎ ፖሊሲ ጋር በተቆራኘባቸው አካባቢዎች (ለምሳሌ በደቡባዊ አፍሪቃና በአሜሪካ) የላቀ ነበር። በእነዚህ አገሮች ለሚገኙ ጥቁሮች የዐድዋ ባለድል የሆነችው ኢትዮጵያ የነፃነትና የክብር ፋና ሆነች። ቀድሞውንም ቢሆን በመጽሐፍ ቅዱስ በስፋት የምትወሳው ኢትዮጵያ «ኢትዮጵያኒዝም» እየተባለ ለሚጠራ ከነጮች ተጽዕኖ ነፃ የሆነ የጥቁሮች የሃይማኖት እንቅስቃሴ መንሥኤ ሆና ነበር። አሁን ደግሞ በዐድዋ ድል አማካይነት ቀድሞ በረቂቁ ትታወቅ የነበረችው ኢትዮጵያ ሥጋና ደም ተላብሳ ታየች።

ይህ የጥቁር ሕዝቦች ከኢትዮጵያ ጋር መተሳሰር በደስታ ጊዜ ብቻ ሳይሆን በመከራም ነበር። ከአርባ ዓመታት በኋላ ኢትዮጵያን የፋሽስት ፅልመት ሲጋርዳት የዓለም ጥቁሮች በሙሉ ከኢትዮጵያ ጎን ለመሰለፍ ተንቀሳቀሱ። የዚህ የጥቁሮች ራሳቸውን ከኢትዮጵያ ጋር የማዋሐዱ እንቅስቃሴ አንዱ ገጽታ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አምሳል አብያተ ክርስቲያናት ማቋቋሙ ነው። «አቢሲኒያን»፤ «ኢትዮጵያን» እና «ኮፕቲክ» በሚል ቅጽል የሚጠሩ አያሌ አብያተ ክርስቲያናትና የሃይማኖት ንቅናቄዎች በተለይ በአሜሪካ አህጉር

ተቋቋሙ:: ይህንንም ሂደት በጉልህ ሊያስረዳ የሚችለው አንዱ ንቅናቄ «የአቢሲኒያ ኮፕቲክ ኢትዮጵያዊ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን» ተብሎ ይታወቅ የነበረው ነው:: በፖለቲካው መልክም የፋሽስትን ወረራ በመቃወም በዓለም መድረክ ይሟገቱ ከነበሩት ውስጥ እንደነ ጆሞ ኬንያታና ክዋሜ ንክሩማህ የመሳሰሉትን ወጣት አፍሪቃዊ መሪዎች መጥቀስ ይቻላል:: በነዚህ መሪዎች አማካይነትም ነው መላ ጥቁሮችን ለማስተባበር የተነሣሣው የ«ፓን አፍሪካኒዝም» እንቅስቃሴ ከአሜሪካ አህጉር ወደ አፍሪቃ ሊሸጋገር የበቃው:: ቆይቶም በ1955 ይህ በከፊል በዐድዋ ድል የተቀሰቀሰው እንቅስቃሴ ድሉ በተገኘበት አገር የአፍሪቃ አንድነት ድርጅት ሲመሠረት ታሪካዊ ድምዳሜው ላይ ደረሰ ማለት ይቻላል::

መቼም ታሪክ በቅራኔ የተሞላች ናትና ለዓለም ጥቁሮች የነፃነት ፋና ያበራው የዐድዋ ድል ጎረቤት ለሆነችው ጥቁር አገር ሱዳን ከነፃነት ይልቅ ቅኝ አገዛዝን ያስከተለ ሂደት መንሥኤ ሆነ:: የዐድዋ ድል የኢጣልያን ቅስም የሰበረውን ያህል በእንግሊዝ ካምፕም ከባድ ሽብር ነበር የፈጠረው:: ምክንያቱም የእንግሊዝ ስሌት ኢጣልያ ኢትዮጵያን ተቆጣጥራ ፈረንሳይን ወደ ፈለገ ዐባይ ድርሽ እንዳትል ትከላከልልኛለች የሚል ስለነበረ ነው:: ዐድዋ ይህን ስሌት አቃወሰው:: የዐባይ ጥያቄም እንደገና ተቀሰቀሰ:: ባንድ ወገን ሱዳን በማህዲስቶች እጅ ነች:: በሌላ ወገን ደግሞ ኢትዮጵያ ከኢጣልያን ነፃ በመሆኗ በእንግሊዞች ግምት ለፈረንሳይ ወደ ዐባይ የመስፋፋት ፖሊሲ አመቺ ሆና ተገኘች:: በዚህ ሁሉ መሀል የግብፅ ባለቤት የሆነችው እንግሊዝ ወና ቤት ታቅፋ ልትቀር ሆነ:: ይኸኔ ነው የማህዲስት ንቅናቄ በራሱ የውስጥ ቅራኔ ተተብትቦ ይወድቃል ብለው ተስፋ ሲያደርጉ የቆዩት እንግሊዞች ጊዜ ሳያጠፉ በሱዳን ላይ የዘመቱት:: በመጋቢት 1888 የተጀመረው ወረራም ከሁለት ዓመት በኋላ የማህዲስቶች ዋና መዲና የሆነችው ኦምዱርማን በእንግሊዝ መድፍ ተደብድባ ስትወድቅ ተደመደመ:: ሱዳንም ለይስሙላ የእንግሊዝና የግብፅ ጥምር ግዛት (አንግሎ-ኢጅፕሺያን ኮንዶሚኒየም)፣ እንደ እውነቱ ከሆነ ግን የእንግሊዝ ቅኝ ግዛት ለመሆን በቃች::

በሌላ ወገን በዚሁ በዐባይ ጥያቄ ላይ ነው የምኒልክ ዲፕሎማሲያዊ ብስለትና ዓለም አቀፋዊ የፖለቲካ ስብእና ገዝፎ ሊወጣ የቻለው:: እንግሊዞች ፈረንሳይ ባዲሱ ሁኔታ ተጠቅማ ወደ ዐባይ ትስፋፋለች ብለው መሥጋታቸው መሠረተ ቢስ አልነበረም:: በዐድዋ ማግስት ከምዕራብ እስከ ምሥራቅ አፍሪቃ የተንሰራፋ ግዛት ለመመሥረት የነበራቸውን ስፊ ዕቅድ እውን ለማድረግ ፈረንሳዮች በሁለቱም አቅጣጫ ሠራዊቶቻቸውን አዘመቱ:: ዕቅዱ ሁለቱ ጦሮች ነጭ ዐባይ ላይ እንዲገናኙ ለማድረግ ሲሆን ከምዕራብ አፍሪቃ የተነሣውን ዘማች ጦር የመራው ካፒቴን ባፕቲስት ማርሻ ሲሆን፣ ከጅቡቲ የተነሣው ደግሞ የሚመራው በማርክዊዝ ደ ቦንሻም ነበር:: ቀደም ሲል ፈረንሳዮች ከምኒልክ ጋር በተዋዋሉት ስምምነት መሠረት ምኒልክ የጅቡቲው ጦር የኢትዮጵያን ግዛት በሚያቋርጥበት ጊዜ በስንቅ አቅርቦቱ በኩል ሊተባበር ቃል ገብቶ ነበር:: ይሁን እንጂ ይህን ቃል ለማክበር ብዙም አልተጨነቀም:: የራሱንም ሆነ ያገሪቱን እድል ካንድ መንግሥት ጋር የማስተሳሰር ፍላጎት አልነበረውም:: የሱ ዋና ዓላማ አትዮጵያን ለሚፈታተኑት ሦስት ኃይሎች (እንግሊዝ፣ ፈረንሳይና ማህዲስት ሱዳን) ለሁሉም ወዳጅ በመምሰል አንዳቸውንም ሳያስቀይም በመሀሉ የግዛት ማስፋፋት ተግባሩን ለመቀጠል ነው::



በዚህም መሠረት ምኒልክ ለሱዳኑ መሪ ለኸሊፋ ዐብዱላሂ የአፍሪቃውያን ወንድማማችነትን የሚያስተጋቡ የወዳጅነት ደብዳቤዎች ቢጽፍለትም፣ መዘዝ የሚያመጣ መተሳሰር ውስጥ ከመግባት ታቅቦ ነበር:: ይህ ሞቅ ያለ አፍሪቃዊ ስሜትም በግንቦት 1889 ከእንግሊዞች ጋር ባደረገው ስምምነት በማህዲስት ሱዳን ላይ የጦር መሣሪያ ማዕቀብ ከመጣል አላገደውም:: የማህዲስትን ሥልጣን መዳከም አይቶም፣ እንደሚባለውም የኸሊፋውም ቡራኬ ታክሎበት፣ ሥልጣኑን በአሶሳና በቤኒ ሻንጉል ላይ ለመዘርጋት በቃ:: ፈረንሳዮችንም በተመለከተ ደ ቦንሻምን በስንቁም መንገድ በማሳየቱም እንዲያግዝ የላከው የጐሬው ገዥ ደጃች (ኋላ ራስ) ተሰማ ናደው ያተኮረው ፈረንሳዮቹን በመርዳቱ ላይ ሳይሆን የምኒልክን ግዛት ወደ ነጭ ዓባይ በማስፋፋቱ ላይ ነበር:: ተሰማ የኢትዮጵያን ባንዲራ ናሲር ላይ ተክሎ ሲመለስ እንግሊዝና ፈረንሳይ ነጭ ዐባይ ላይ ተፋጠው ቀሩ:: ፋሾዳ የተባለችው ሁለቱ የተፋጠጡባት መንደርም ለጥቂት ጊዜ ዓለም አቀፍ ትኩረት ስባ ነበር:: መላውን ዓለም ያሠጋ የጦርነት ደመና ካንዣበበ በኋላ ፈረንሳዮች አፈግፍገው እንግሊዞች የዚያ የቅኝ አገዛዝ ፖሊሲያቸው አውታር የሆነው የመገናኛ መሥመር ፍጹም ባለቤት ለመሆን በቁ::

ዞሮ ዞሮ ግን ዐድዋ ከፍተኛውን አሻራ ትቶ ያለፈው በሁለቱ ዋና ተፋላሚዎች፣ በተለይም በኢትዮጵያ ላይ ነው:: በጣልያን አገር የሽንፈቱ ወሬ እንደተሰማ የተፈጠረው ስሜት ድብልቅ ነበር:: ባንድ በኩል የኢጣልያ ቅኝ አገዛዝ ፖሊሲ ቅስሙን በመሰበሩ ደስታና ፈንጠዝያ ያስተጋባ ነበር:: «ቪቫ ምኒልክ» የሚለው ጩኸት በሮማና በሌሎችም ዋና ዋና የኢጣልያ ከተማዎች ተሰማ:: መቶ ሺ የሚያህሉ ሰዎች የፈረሙበት ማመልከቻ ኢጣልያ እስከናካቴው የአፍሪቃን ምድር ለቃ እንድትወጣ ጠየቀ:: በኢጣልያ ሽንፈት አንጀቱ የራሰው ቀድሞውኑም ቢሆን የኢጣልያን የቅኝ ግዛት መስፋፋት በጽኑ ሲቃወም የነበረው ወገን ነው:: የዚህ ፀረ ኰሎኒያሊስት ቡድን የድል ዋንጫ እስከ አፉ የሞላው የቅኝ ግዛት ፖሊሲው ዋና አቀንቃኝ የነበረው ጠቅላይ ሚኒስትሩ ፍራንቼስኮ ክሪስፒ ከሥልጣን ወርዶ በምትኩ ለዘብተኛውና የመስፋፋት ፖሊሲን ለመቀልበስ ዝግጁ የነበረው አንቶኒዮ እስታራባ (ማርኬዜ ዲ ሩዲኒ) በስፍራው ሲተካ ነው:: ሌላው የዐድዋ ሰለባ ከሽንፈቱ በፊት ለኢጣልያ አንድነት ሲታገል ዝናንና ተወዳጅነትን ካገኘው ጋሪባልዲ ጋር ተነፃፅሮ የነበረውና የኢጣልያ ፖርላማ አባላት በታላቅ ጭብጨባ ተቀብለውት የነበረው ባራቲዬሪ አሁን ለሽንፈቱ ዋና ተጠያቂ ሆኖ ፍርድ ቤት ቀረበ::

በሌላ በኩል ግን በኢጣልያውያን ዘንድ በጦር ሜዳው ለወደቁት ሐዘን፣ ምርኮኛ ለሆኑት ደግሞ ሥጋት መፈጠሩ አልቀረም:: በብዙ ሺ የሚቆጠሩት የጦር ምርኮኞች ወደ ሀገራቸው መመለስም የአዲሱ መንግሥት ተቀዳሚ ተግባር ሆነ:: ይህም እንዲሳካ ተብሎ ለኢጣልያ መንግሥት ቅርብ የሆነው የሮማው ጳጳስ ሊኦ 13ኛክርስቲያናዊ ርኅራኄ እንዲያሳይ በግንቦት 1888 ለምኒልክ ደብዳቤ ጻፈለት:: ምኒልክ ግን በደብዳቤው ብዙም ሳይሸነገል እርቀ ሰላም ሳይወርድ ምርኮኞቹን ለመልቀቅ ፈቃደኛ አለመሆኑን በመግለጽ መልስ ሰጠ:: «ባለው ሁኔታ» አለ ምኒልክ ሲመልስ፣ «ለሕዝቤ ያለብኝ የንጉሥነትና የአባትነት ግዴታ ለሰላም ያለኝ ብቸኛ ዋስትና እንደዋዛ ከእጄ እንዳያመልጥ እንድጠነቀቅ ያስገድደኛል::» ድርድሩ እየቀጠለ እያለ ግን ምርኮኞቹ አልተንሳቀሉም፣ ሥራም አልፈቱም:: ጣልያን ሰፈር ተብሎ ለመጠራት በበቃው በአሁኑ የማስታወቂያ ሚኒስቴር ጀርባ በሚገኝ አምባ ሰፍረው አስፈላጊው ምግብና ልብስ እየቀረበላቸው ተቀመጡ:: አንዳንዶቹም በማደግ ላይ ባለችው

መናገሻ ከተማ ውስጥ ድልድይና መንገድ በመሥራት ጠቃሚ አገልግሎት ሰጡ።

በመጨረሻ በጥቅምት 15 1889 በአዲስ አበባ የተፈረመው የሰላምና የእርቅ ውል የአዲስ አበባ ውል ተብሎ ታወቀ። የዚህ ውል ዋና አንቀጽ የውጫሌን ውል ሠርዞ ኢጣልያ የኢትዮጵያን ሙሉ ነፃነት ያላንዳች ገደብ ማወቋን የሚገልጸው ነበር። በኢትዮጵያና ኢጣልያ በቅኝ ግዛትነት በያዘቻት በኤርትራ መካከል ያለው ድንበር በሥርዓት እስከሚከለል ድረስ ከጦርነቱ በፊት የነበረው ወሰን እንዲረጋ ተስማሙ። በተጨማሪም ከውሉ ጋር የጦር ምርኮኞቹ የሚለቀቁበት ስምምነት ተፈራረሙ።

በዚህ ሁኔታ ምኒልክ ጦርነቱ በተፈጸመ በስምንት ወር ውስጥ ዮሐንስ ከጉንደትና ጉራ በኋላ ስምንት ዓመት ደክሞ ካገኘው የሰላም ውል የተሻለ ውል ለማግኘት ቻለ። የዐድዋ ትልቁ አብነት አንዲት አፍሪቃዊት አገር ነፃነቷን በኃይሏ ተከላክላ ለማስከበር መቻሏ ነበር። እንደ ማዕበል አህጉራቱን በማጥለቅለቅ ላይ ለነበረው የአውሮጳ ቅኝ አገዛዝ ይህ አንድ ትልቅ ሽንፈት ነበር። የኢትዮጵያ የወደፊት እድልና የእድገት አቅጣጫም ከቀረው የአፍሪቃ አህጉር የተለየ ሊሆን ቻለ። ይህ በሀገሪቱ ፖለቲካዊ ኤኮኖሚ ብቻ ሳይሆን በሕዝቡ ስነ ልቡናም ላይ ተጽዕኖ አሳደረ።

በኤኮኖሚው ረገድ በተቀረው የአፍሪቃ ክፍል የታየው የአውሮጳ ካፒታል ልዕልና በኢትዮጵያ አልታየም። የዚህ ውጤት በጎነት ወይ መጥፎነት አከራካሪ ሆኖ ቆይቷል። ቀደም ሲል እንደ ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ ያሉ ለውጥ ፈላጊ ምሁራን፣ ኋላ ደግሞ የ1953 መፈንቅለ መንግሥት መሪዎች በቅኝ አገዛዝ ሥር በነበሩት የአፍሪቃ አገሮች አንፃር አገራቸው ምን ያህል ኋላ ቀር እንደሆነች በቁጭት አመልክተዋል። ይሁን እንጂ የዐድዋ ድል በተከታታይ ትውልዶች ዘንድ ብሔራዊ ኩራትንና ቀናዔ ነፃነትን አሥርፆ አልፏል። ይህ የኩራትና የነፃነት ስሜት በ1928 የኢጣልያ ወረራ ጥቂት ደብዘዝ ቢልም ድል በተጎናጸፈው የአርበኞች ትግል ሊታደስ ችሏል። የአምስቱ ዓመት የኢጣልያ አገዛዝም አጭርና ገድጋዳ ከመሆኑ የተነሣ ይህን መንፈስ ሊሰብረው አልቻለም። በመጨረሻም ኢትዮጵያ በ1966 በአፍሪቃ ያልታየ የለውጥ ዓይነት ልታካሂድ የቻለችው ዐድዋ በተለመላት የተለየ የእድገት አቅጣጫ ምክንያት ነው ማለት እንችላለን።

ይሁን እንጂ በፖለቲካ ረገድም ሆነ ከግዛቷ ይዞታ አንፃር ዐድዋ ለኢትዮጵያ ፍጹም ነፃነትን አረጋገጠላት ለማለት ያዳግታል። በ1892 የመረብ ወንዝ የኤርትራና የኢትዮጵያ ድንበር መሆኑ በውል ሲደነገግ ኢትዮጵያ ታሪካዊ የሰሜን ግዛቷን አስረከበች። ኢጣልያ በጦር የያዘችው ግዛትም በሕግ ጸደቀላት። ይህ ሁኔታ ምናልባት የዐድዋ ድልና የምኒልክም ፖሊሲ ከፍተኛው ድክመት ነበር ተብሎ ሊታሰብ ይችላል። ዐድዋ በብዙ አንፃር አንጸባራቂ ድል የሆነውን ያህል የኢትዮጵያ መሪዎች ለዘመናት የጓጉለትን የባሕር በር አላስገኘላቸውም። እንዲያውም ትንሹንም ጭላንጭል እስከናካቴው ዘጋው። ቴዎድሮስና ዮሐንስ እራሱም ምኒልክ ቢሆን በደብዳቤዎቻቸው እንዳልወተወቱና እንዳልተማጠኑ ሁሉ፣ ወደር የሌለው ሰፊ ግዛት የመሠረተው ምኒልክ ምናልባት ባላሰበውና ባልጠበቀው ሁኔታ ኢትዮጵያ የባሕር በሯ ጥርቅም ተደርጎ ሲዘጋባት ለማየት በቃ። የሱም ተከታዮች እንደ ቀድሞዎቹ መሪዎች የባሕር በር ለማግኘት መማሰን ግድ ሆነባቸው። በ20ኛው መቶ ዓመት አንዴ እንግሊዞች ዘይላን እንዲሰጡ፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ጣልያኖች አሰብን፣ ወይ ደግሞ ፈረንሳዮች ከጅቡቲ



ግዛታቸው አንድ ወደብ እንዲፈቅዱ ያልተሳኩ ድርድሮች ተካሂደዋል። ይህ የዘመናት ጥያቄ መልስ ያገኘ የመሰለው ኤርትራ በ1933 ከኢጣልያ ቅኝ አገዛዝ ተላቃ ከዚያም ከ11 ዓመታት በኋላ ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን ስትቀላቀል ነው።

የኤርትራ ተቆርሳ መወሰድ ያስከተለው ችግር የባሕር በር እጦት ብቻ አይደለም። በ1888 እንደሆነው ሁሉ ጣልያኖች ኤርትራን ወደ ኢትዮጵያ ሠርጎ የመግቢያ መቆናጠጫ ማድረጋቸው ጭምር ነው። በ20ኛው መቶ ዓመት መጀመርያ ዐሠርት ዓመታት በረቀቀና በተቀነባበረ ስልት በሰሜን ኢትዮጵያ የማዕከላዊውን መንግሥት ከገዘገዙ በኋላ፣ በ1928 ትልቁን ወረራቸውን ከዚሁ ነው የከፈቱት። በመጨረሻም በኤርትራ ውስጥ የተከሰተው ተገንጥሎ ነፃ መንግሥት የማቋቋም ንቅናቄ፣ ምንም እንኳ ብዙ ሌላ አጋዥ ኃይሎች ቢኖሩትም፣ሥረ መሠረቱ ይኸው የኢጣልያ ቅኝ አገዛዝ ዘመን ነው።

የኢትዮጵያ ድኅረ ዐድዋ ነፃነት ፍጹማዊ ያለመሆኑ ጉዳይ ሌሎችም ገጽታዎች ነበሩት። ዙሪያውን የከበቧት የአውሮጳ ቅኝ ገዥዎች በነፃነቷ ላይ ቀላል ነው የማይባል ገደብ አበጅተውባት ነበር። እሷን ሳያማክሩና ሳያሳትፉ በግዛቷ ላይ ውል ይዋዋሉ፣ ጥቅም ይካለሉ ነበር። ለዚህም ሁለት ማስረጃዎች መጥቀስ ይቻላል። አንደኛው በ1889 በእንግሊዝ፣ ፈረንሳይና ኢጣልያ መካከል የተፈረመው የጥቅም ማስከበሪያ የሦስትዮሽ ውል ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ በ1918 በእንግሊዝና በኢጣልያ መካከል የተደረሰው ስምምነት ነው። ኢትዮጵያ ነፃ መንግሥት ነኝ ብላ ወደ መንግሥታት ማኅበር ለመግባት ስትፈልግም ብዙ አሣር ነው ያገኛት። የሥልጣኔ ደረጃሽ ዝቅተኛ ስለሆነ ለማኅበር አባልነት ብቁ አይደለሽም ተብላ ደጅ መጥናት ነበረባት። ባርነትና የባርያ ንግድ የተጧጧፈባት አገር ናት በሚል ሰበብም የጦር መሣሪያ ማዕቀብ ተደረገባት። ሌላው የኢትዮጵያን ነፃ መንግሥትነት አጠያያቂ ያደረገው በ1900 ምኒልክ ከፈረንሳይ ሚኒስትር (ባሁን አጠራር አምባሳደር) ጋር የተዋዋለው የክሎቡኮውስኪ ውል ነው። በዚህ ውል መሠረት ፈረንጆች ከኢትዮጵያ ሕግ በላይ፣ የኢትዮጵያ መንግሥት የቀረጥ መብትም በውጭ ኃይሎች የተደነገገ ሆነ።

በኢኮኖሚውም ረገድ ኢትዮጵያ የአፍሪቃን ኤኮኖሚ እየበረገደ ይገባ ከነበረው ኢምፔሪያሊዝም ሙሉ በሙሉ ነፃ አልነበረችም። መላ ኃይሉን ባታመልጥም ጥላው አርፎባታል። ልዩነቱ የኢትዮጵያ የፖለቲካ መዋቅር ከሞላ ጎደል በራሷ ዜጎች እጅ ስለነበር ኢምፔሪያሊዝም ያልተገደበ ነፃነት ማግኘት አልቻለም። ስለሆነም በኢትዮጵያና በአውሮጳ መካከል የነበረው ግንኙነት እንደ ቱርክና ፋርስ (የዛሬይቱ ኢራን) ከፊል ቅኝ ግዛታዊ ነበር ማለት ይቻላል። በዐድዋው ድል የተዘጋባቸው የመሰለውን የኤኮኖሚ በር አውሮጳውያን በንግድና በሞኖፖል ውሎች አማካይነት ገርበብ ለማድረግ ቻሉ።

## የማኅበረ ኤኮኖሚያዊው ሥርዓት

### የትርፍ ምርት ማካበቻ ስልት

በ19ኛው መቶ ዓመት የኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ጎልተው የሚታዩት ሁለት ሂደቶች ተበታትነው የነበሩት ግዛቶች መዋሐድና የውጭ አደጋን መቋቋም


ናቸው። ዐድዋ የሁለቱም ማሳረጊያ ነበር። የሃያኛውን መቶ ዓመት የኢትዮጵያ ሕይወት መልክና ቅርፅ የሰጠውም የነሱ ቅርስ ነው። የአንድነቱ ሂደት የገኘውን መደብ ሥልጣን ቁሳዊ መሠረት ሲያጠናከር፣ የዐድዋ ድል ደግሞ ከፍ ብለን እንዳየነው አገሪቱ ከውጭው ዓለም ጋር የሚኖራትን ግንኙነት ስልት ቀየሰ።

በ19ኛው መቶ ዓመትም ሆነ ከዚያ በፊት የፖለቲካ ሥልጣን ኤኮኖሚያዊ መሠረት ግብር እና ትርፍ ጉልበት ሆኖ ቆይቷል። ሁለቱም የሚገኙት መሬቱን የዘር ሐረግ ቆጥሮ በርስትነት ከያዘው ገበሬ ወይም ገባር ነበር። ከመሬት ግብር በተጨማሪ ገበሬው የምርቱን አንድ ዐሥረኛ ወይም ዐሥራት ይከፍላል። የውሎ አበል ወይ ሆቴል ባልታወቀበት ዘመን በሰፈሩ ለሚተላለፉ ወይ ለሚሠፍሩ የመንግሥት ባለሥልጣኖች መጥን፣ ለመንግሥት እንግዶች ደግሞ ድርጎ በመክፈል ያስተናግዳል። መልከኛ ወይ ሻለቃ ተብሎ ለሚታወቀው ምስለኔ የማገዶ እንጨት ያቀርባል። የገኘው መደብ ልዩ መብት የነበረው ጠጅ የሚጣልበትን ማር የሚያቀርበውም ይኸው ገባሩ ነው። ከዚህም በላይ አዲስ ሹም ሲሾም ሲሽለም፣ ወይ የማዕረግ ዕድገት ሲያገኝ፣ ወይ ለሹሙ ወንድ ልጅ ሲወለድለት የደስ ደስ ብሎ «ገጸ በረከትም» ማቅረብ ይጠበቅበት ነበር።

ገባሩ ምርቱን ብቻ ሳይሆን ጉልበቱንም ይገብር ነበር። ለምሳሌ ከሥራ ጊዜው ሢሶውን የሚያውለው «ሁዳድ» ወይም «ሑዳድ» ተብሎ የሚታወቀውን የቤተ መንግሥት ወይ ያገረ ገዥ ወይ የባላባት ወይ የመልከኛ መሬት በማረስ ነው። በተጨማሪም ሚስቱ የመልከኛውን እህል ስትፈጭ እሱ ደግሞ ጎተራውንና አጥሩን ይሠራለታል። በዘመኑ የመንግሥት እስር ቤት የማይታወቅ ስለነበር፣ የእስረኛ ጠባቂም ይኸው ገባር ነው። መከረኛው ገባር እስረኛው ካመለጠበት በእግሩ ይተካል። እንዲሁም በሰላም ጊዜም ሆነ በጦርነት የአገረ ገዥውን ዕቃ ይሸከማል፣ ይህም አገልግሎት «አልፍ» ተብሎ ይታወቃል።

የምኒልክ ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ መስፋፋት ጣምራ ውጤቶች ነበሩት። ባንድ በኩል በሰሜን ኢትዮጵያ ተጨናንቆ ይኖር የነበረውን እርስተኛ ወደ ደቡብ በማስፈር ትንሽ ተንፈስ እንዲል አደረገ። በሌላ በኩል ደግሞ በሰሜን ኢትዮጵያ ለዘመናት ሰፍኖ የነበረውን የገባር መልከኛ ግንኙነት ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ አዛመተ። ከገባር ሥርዓት የዳኑት ለምኒልክ በሰላም አሜን ብለው የገበሩት ግዛቶች ብቻ ናቸው። እነዚህም ጅማ አባጅፋር፣ ሌቃ ነቀምቴ፣ ሌቃ ቄለም፣ አሶሳ ቤኒ ሻንጉል፣አውሳ (የአፋሮች ግዛት)፣ ጉባ (መተከል) ነበሩ። በነዚህ ግዛቶች ላይ ዓመታዊ ቁርጥ ግብር ተጥሎባቸው ገዥዎቻቸው በየዓመቱ አዲስ አበባ እየመጡ በትልቅ ሥነ ሥርዓት ለንጉሠ ነገሥቱ ግብራቸውን ከፍለው በዚያውም ታማኝነታቸውን አድሰው ወደ ግዛታቸው ይመለሱ ነበር። ከዚህ ዓመታዊ ግብር ሌላ፣ ማዕከላዊው መንግሥት ተጽዕኖና ቁጥጥር ከማድረግ ይቆጠብ ነበር። ለምሳሌ ምኒልክ የእስልምና ተከታይ በሆነው በአባ ጅፋር ግዛት ቤተ ክርስቲያን ላለመትከል ቃል እስከ መግባት ደርሶ ነበር። የአባ ጅፋር የውስጥ አስተዳደር ነፃነት ከምኒልክ ሞት በኋላም ቀጥሎ በማዕከላዊው መንግሥት መገዝገዝ የጀመረው በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ነው። አባ ጅፋር ለምኒልክ በየዓመቱ የሚያገባው ቁርጥ ግብር 29065 ማርትሬዛ ብር ይደርስ ነበር ተብሎ ይገመታል። (ማኅተመ ሥላሴ፣ 165)






4. ኢትዮጵያ በ1928



3.1 ገባርና ልጁ፣ ሰሜን ምሥራቅ ሸዋ

ቁርጥ ግብር ከተጣለባቸው ግዛቶች ውጭ ያሉት የደቡብ ግዛቶች በምኒልክ የጦር መሪዎች እንዲተዳደሩ ተደርገው ለነዚህ መኳንንት የሀብት ምንጭም የጦር ኃይላቸውም መሠረት ሆነ። አብዛኛውን ጊዜ ግዛቱ የሚሰጠው ላቀናው የጦር መሪ ነበር። በዚህም መሠረት ራስ ወልደ ጊዮርጊስ ከፋን፣ ደጃች ተሰማ ኢሉባቦርን፣ ደጃች ደምስ ወለጋን (ማለትም አርጆን እና ሆሮ ጉድሩን)፣ ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ደግሞ በሬናንና ጅባትና ሜጫን ተሰጥተው ነበር። በተመሳሳይ መንገድም ሐረር የራስ መኮንን ቤተሰብ ዐፅመ ርስት ሆነች። የነዚህ መኳንንት ሹማምንትና ባለሟሎች እንደ ማዕረጋቸው ከ5 እስከ መቶ የሚደርሱ ገባሮች ይመደቡላቸው ነበር። ይህ ሥርዓት «የቁጥር ገባር» ሥርዓት ተብሎ ይታወቃል። እነዚህ ገባሮች ከላይ የዘረዘርናቸውን ዓይነት ግብር ይከፍላሉ፤ የጉልበት ሥራ ይሠራሉ። የደቡቡ ገባር እንደ ሰሜኑ አቻው ዘር ቆጥሮ በሚያገኘው መሬት ላይ ሙሉ ባለቤትነት ሳይሆን አፍርቶ የመጠቀም መብት ነበረው። የገባር ሥርዓት መጀመሪያ ወደ ደቡብ ሲዛመትም ገባሩ የባለመሬትነት መብቱ አልተነካበትም ነበር። ውሎ አድሮ ግን ይህን መብት የሚሸሩ ሁኔታዎች ተከሠቱ።

የደቡብ ኢትዮጵያን የመሬት ሥሪት ከለወጡት ሁኔታዎች አንዱ «ቀላድ» እየተባለ የሚታወቀው የመሬት መለካት ባህል በ20ኛው መቶ ዓመት መጀመሪያ ላይ እየተስፋፋ መሄድ ነው። ቀላድ የሚለው ስም የተገኘው መሬቱን ለመለካት ያገለግል ከነበረው ገመድ ነው። የመሬት መለካት ልምድ በበጌምድር





3.2. የውጭ አገር ጎብኝዎች ድርጎ ሲቀበሉ

ቀደም ያለ ታሪክ ቢኖረውም በሌላው የኢትዮጵያ ክፍል ሥራ ላይ መዋል የጀመረው በምኒልክ ዘመነ መንግሥት ነው። ቀላድ መጀመሪያ የወደቀው በሸዋና በአካባቢዋ ሲሆን እያደር ግን ወደ ሌሎች የደቡብ ግዛቶችም ተዛምቷል። ለምሳሌ በወለጋ በ1902 የተጀመረው የመሬት መለካት ተግባር ሦስት ሩብ የሚያህለውን መሬት የመንግሥት አድርጎታል። «ቀቢዬ» ተብሎ በሚታወቀውና ከሰሜን ኢትዮጵያ ርስት ጋር ተመሳሳይ በሆነው የመሬት ሥሪት መሠረት የመሬት ባለመብት የነበረው ገበሬም ባዲሱ ሥርዓት የገዛ መሬቱን ለመግዛት ተገደደ። ይህን ማድረግ ካልቻለ የሚጠብቀው ጭሰኝነት ሆነ። በወላይታም የቀላድ ሥርዓት ሕዝቡ በጋራ ይጠቀምበት የነበረውን መሬት ባለቤት አልባ አርጎ በመቆጣጠርና በመውረስ ለቤተ ክህነትና ለአንዳንድ ግለሰቦች እንዲታደል አድርጓል።

የመሬት መለካት አንዱ ዐቢይ ዓላማ የግብርን አሰባሰብ ለማመቻቸት ነበር። የተለካው መሬት ለም፣ ለም ጠፍና ጠፍ በሚል ፈርጅ ሲከፈል ግብሩም እንደ ለምነቱ ከፍ እያለ ይሄዳል። ይህም ስሉት ለሙን መሬት ባብዛኛው የያዙትን ገበሬዎች ሲጎዳ ጠፉን መሬት በስፋት ለያዙት ትላልቅ ባለመሬቶች ግን የሚያመች ነበር። ከቀላድ መጣል ጋር ተጎዳኝ የነበሩ ሁለት ክሥተቶችም በዚሁ መቶ ዓመት መጀመሪያ በስፋት መታየት ጀመሩ። እነሱም የግል የመሬት ይዞታና የመሬት ሽያጭ ናቸው። ቀደም ብለን እንዳየነው በሰሜንም ሆነ በደቡብ ኢትዮጵያ መሬት ከትውልድ ሐረግ ጋር የተያያዘ በመሆኑ የጋርዮሽ ባሕሪ ነበረው። ባለርስቶች በመሬት ላይ ያላቸው መብት ፍጹማዊ (ማለትም መሸጥ



3.1 ገባርና ልጁ፣ ሰሜን ምሥራቅ ሸዋ

ቁርጥ ግብር ከተጣለባቸው ግዛቶች ውጭ ያሉት የደቡብ ግዛቶች በምኒልክ የጦር መሪዎች እንዲተዳደሩ ተደርገው ለነዚህ መኳንንት የሀብት ምንጭም የጦር ኃይላቸውም መሠረት ሆኑ። አብዛኛውን ጊዜ ግዛቱ የሚሰጠው ላቀናው የጦር መሪ ነበር። በዚህም መሠረት ራስ ወልደ ጊዮርጊስ ከፋን፣ ደጃች ተሰማ ኢሉባቦርን፣ ደጃች ደምስ ወለጋን (ማለትም አርጆን እና ሆሮ ጉድሩን)፣ ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ደግሞ ቦረናንና ጅባትና ሜጫን ተሰጥተው ነበር። በተመሳሳይ መንገድም ሐረር የራስ መኰንን ቤተሰብ ዐፅመ ርስት ሆነች። የነዚህ መኳንንት ሹማምንትና ባለሟሎች እንደ ማዕረጋቸው ከ5 እስከ መቶ የሚደርሱ ገባሮች ይመደቡላቸው ነበር። ይህ ሥርዓት «የቁጥር ገባር» ሥርዓት ተብሎ ይታወቃል። እነዚህ ገባሮች ከላይ የዘረዘርናቸውን ዓይነት ግብር ይከፍላሉ፣ የጉልበት ሥራ ይሠራሉ። የደቡቡ ገባር እንደ ሰሜኑ አቻው ዘር ቆጥሮ በሚያገኘው መሬት ላይ ሙሉ ባለቤትነት ሳይሆን አፍርቶ የመጠቀም መብት ነበረው። የገባር ሥርዓት መጀመሪያ ወደ ደቡብ ሲዛመትም ገባሩ የባለመሬትነት መብቱ አልተነካበትም ነበር። ውሎ አድሮ ግን ይህን መብት የሚሸሩ ሁኔታዎች ተከሠቱ።

የደቡብ ኢትዮጵያን የመሬት ሥሪት ከለወጡት ሁኔታዎች አንዱ «ቀላድ» እየተባለ የሚታወቀው የመሬት መለካት ባህል በ20ኛው መቶ ዓመት መጀመሪያ ላይ እየተስፋፋ መሄድ ነው። ቀላድ የሚለው ስም የተገኘው መሬቱን ለመለካት ያገለግል ከነበረው ገመድ ነው። የመሬት መለካት ልምድ በበጌምድር





3.2. የውጭ አገር ጎብኚዎች ድርጎ ሲቀበሉ

ቀደም ያለ ታሪክ ቢኖረውም በሌላው የኢትዮጵያ ክፍል ሥራ ላይ መዋል የጀመረው በምኒልክ ዘመነ መንግሥት ነው። ቀላድ መጀመሪያ የወደቀው በሸዋና በአካባቢዋ ሲሆን እያደር ግን ወደ ሌሎች የደቡብ ግዛቶችም ተዛምቷል። ለምሳሌ በወለጋ በ1902 የተጀመረው የመሬት መለካት ተግባር ሦስት ሩብ የሚያህለውን መሬት የመንግሥት አድርጎታል። «ቀቢዬ» ተብሎ በሚታወቀውና ከሰሜን ኢትዮጵያ ርስት ጋር ተመሳሳይ በሆነው የመሬት ሥሪት መሠረት የመሬት ባለመብት የነበረው ገበሬም ባዲስ ሥርዓት የገዛ መሬቱን ለመግዛት ተገደደ። ይህን ማድረግ ካልቻለ የሚጠብቀው ጭሰኝነት ሆነ። በወላይታም የቀላድ ሥርዓት ሕዝቡ በጋራ ይጠቀምበት የነበረውን መሬት ባለቤት አልባ አርጎ በመቁጠርና በመውረስ ለቤተ ክህነትና ለአንዳንድ ግለሰቦች እንዲታደል አድርጓል።

የመሬት መለካት አንዱ ዐቢይ ዓላማ የግብርን አሰባሰብ ለማመቻቸት ነበር። የተለካው መሬት ለም፣ ለም ጠፍና ጠፍ በሚል ፈርጅ ሲከፈል ግብሩም እንደ ለምነቱ ከፍ እያለ ይሄዳል። ይህም ስሌት ለሙን መሬት ባብዛኛው የያዙትን ገበሬዎች ሲጎዳ ጠፉን መሬት በስፋት ለያዙት ትላልቅ ባለመሬቶች ግን የሚያመች ነበር። ከቀላድ መጣል ጋር ተያይዞ የነበሩ ሁለት ክሥተቶችም በዚሁ መቶ ዓመት መጀመሪያ በስፋት መታየት ጀመሩ። እነሱም የግል የመሬት ይዞታና የመሬት ሽያጭ ናቸው። ቀደም ብለን እንዳየነው በሰሜንም ሆነ በደቡብ ኢትዮጵያ መሬት ከትውልድ ሐረግ ጋር የተያያዘ በመሆኑ የጋርዮሽ ባሕሪ ነበረው። ባለርስቶች በመሬት ላይ ያላቸው መብት ፍጹማዊ (ማለትም መሸጥ



3.3 ደጃች (ኋላ ራስ) ደምስ ነሲቡ፣ የወለጋ ገዥ

መለወጥ የሚያስችል) ሳይሆን በተጠቃሚነት ላይ የተመሠረተ ነበር። በ20ኛው መቶ ዓመት ግን ፍጹማዊ የግል የመሬት ባለቤትነት ሥር እየሰደደ መጣ። ለዚህም ሂደት በምሳሌነት ሊጠቀሱ ከሚችሉት አንዱ በዘመኑ ባለብዙ ሀብት የነበረው ደጃች (ኋላ ራስ) ብሩ ወልደ ገብርኤል ነው። ምኒልክ አርሲ ውስጥ በሰጠው ሰፊ መሬት ላይ ነዋሪ የነበሩትን ገበሬዎች ጋሻውን በ30 ማርትሬዛ ብር ሒሳብ እንዲገዙት አለዚያም ጭሰኛው እንዲሆኑ ምርጫ ሰጣቸው። መሬቱን በተባለው ሒሳብ ለመግዛት የቻሉት ገበሬዎችም ቢሆን ዞሮ ዞሮ የሱ ገባር ከመሆን አላመለጡም።

የቀላድ መጣል ሌላው ውጤት ደግሞ መንግሥትን የብዙ መሬት ባለቤት ማድረግ ነው። ቀደም ብሎ በጋርዮሽ ሥሪት የተያዘ ወይም የግጦሽ መሬት የነበረ ሁሉ ባለቤት የለውም እየተባለ የመንግሥት መሬት እንዲሆን እየተደነገገ መንግሥት ለፈቀደው ግለሰብም ሆነ ድርጅት ይሰጥ ጀመር። ይህ ሁኔታ የ20ኛውን መቶ ዓመት የመሬት ሥሪት መልክ ባያሌው ወስኖታል። ባላባት እየተባሉ ለሚታወቁት የአካባቢ አውራዎች ከዚሁ መሬት በዘልማድ ሢሶ እየተባለ የሚጠራ (በርግጥ ግን አንዳንዴ እስከ አንድ ስድስተኛ ዝቅ ሊል የሚችል) መሬት ይሰጣቸዋል። በገበሬዎች እጅ የቀረው መሬት «የገባር መሬት» ሲባል ለቤተ ክህነት «ሰሞን» ተብሎ የሚታወቅ መሬት ይሰጣል። የመንግሥት ባለሟሎች በደመወዝ ምትክ «ማደርያ» ተብሎ የሚጠራ መሬት ይሰጣቸዋል። ከዚህም ሌላ በተለይ ከቤተ መንግሥቱ ጋር የተያያዙ የመሬት ሥሪቶች ነበሩ። እነሱም ባልደራስና ወረገኑ (ለቤተ መንግሥቱ ፈረስና የእርድ ከብት የሚሰጥ)





3.4 ራስ ብሩ ወልደ ገብርኤል

እና ጋንገብ ወይም ማድቤት (ምስለኔ ሁዳድ እያሳረሰ ለቤተ መንግሥት አስፈላጊ የሆነውን እህል የሚያቀርብበት) ናቸው።

በዚህ የገባር ሥርዓት ውስጥ ገበሬና መንግሥትን እንደ ድልድይ ሆኖ የሚያገናኘው ሢሶ የተቆረጠለት ባላባት ነው። እርሱ የሥርዓቱ አስፈጻሚም ተጠቃሚም ነው፤ በወለጋ መሬት የተለካው በአባ ቆሮዎቹ አስተናባሪነት ነው። በሐረር ቁጥር ገባር የተደለደለው በደሚኑና ከሱም ዝቅ ሲል በገራዱ ነው። ከዚህም ከፍ ባለ ሁኔታ የሌቃ ነቀምቴ ገዥዎች በማዕከላዊው መንግሥት አምሳል የደረጀ የግብር ስልት አውጥተው ዐሥራት ሳይቀር ከዳርቻው አገር ይሰበስቡ ነበር። ባጠቃላይም ከደቡብ ሕዝብ መሪዎች ውስጥ የማዕከላዊ ገዥዎችን መደብ ባሕርይ በከፍተኛ ደረጃ መላበስ የቻሉት የወለጋ መሳፍንት ነበሩ። ይኸ ይኸ ሲታይ በኢትዮጵያ ውስጥ የነበረው የብዝበዛ መሠረት ባብዛኛው ብሔረ ሰባዊ ሳይሆን መደባዊ ነበር ከሚል መደምደሚያ ላይ እንደርሳለን።

ከዚህ በላይ በዝርዝር የቀረበው የመሬት ሥሪት አንባቢን ጥቂት ያደናግር ይሆናል። ነገሩን አበጥረን ስናየው ግን የተረፈ ምርት አወሳሰድ መደቡ የገባሩና የመልከኛው ግንኙነት ነው። ገባሩ ዋናው አምራቹ የሆነውን ያህል መልከኛው ደግሞ ስሙም እንደሚያመለክተው የመንግሥት የቅርብ ተጠሪ ነው። የመደብ ቅራኔ ገሃድ ወጥቶ የሚያፋጥጠውም ሁለቱን ነው። ገባሩ ሥርዓቱ ሲያንገሸግሸው በተለያየ መንገድ ተቃውሞውን ይገልጽ ነበር፤መሬቱን ጥሎ በመጥፋት፣ ለበላይ ባለሥልጣን ወይ ለንጉሠ ነገሥቱ አቤቱታ በማቅረብ፣ ወይ ገፍቶ ሲመጣበት ደግሞ በተለይ ማዕከሉ በሚናጋበት ወቅት በማመፅ።



3.3 ደጃች (ኋላ ራስ) ደምስ ነሲቡ፣ የወለጋ ገዥ

መለወጥ የሚያስችል) ሳይሆን በተጠቃሚነት ላይ የተመሠረተ ነበር። በ20ኛው መቶ ዓመት ግን ፍጹማዊ የግል የመሬት ባለቤትነት ሥር እየሰደደ መጣ። ለዚህም ሂደት በምሳሌነት ሊጠቀሱ ከሚችሉት አንዱ በዘመኑ ባለብዙ ሀብት የነበረው ደጃች (ኋላ ራስ) ብሩ ወልደ ገብርኤል ነው። ምኒልክ አርሲ ውስጥ በሰጠው ሰፊ መሬት ላይ ነዋሪ የነበሩትን ገበሬዎች ጋሻውን በ30 ማርትሬዛ ብር ሒሳብ እንዲገዙት አለዚያም ጭሰኛው እንዲሆኑ ምርጫ ሰጣቸው። መሬቱን በተባለው ሒሳብ ለመግዛት የቻሉት ገበሬዎችም ቢሆን ዞሮ ዞሮ የሱ ገባር ከመሆን አላመለጡም።

የቀላድ መጣል ሌላው ውጤት ደግሞ መንግሥትን የብዙ መሬት ባለቤት ማድረግ ነው። ቀደም ብሎ በጋርዮሽ ሥሪት የተያዘ ወይም የግጦሽ መሬት የነበረ ሁሉ ባለቤት የለውም እየተባለ የመንግሥት መሬት እንዲሆን እየተደነገገ መንግሥት ለፈቀደው ግለሰብም ሆነ ድርጅት ይሰጥ ጀመር። ይህ ሁኔታ የ20ኛውን መቶ ዓመት የመሬት ሥሪት መልክ ባያሌው ወስኖታል። ባላባት እየተባሉ ለሚታወቁት የአካባቢ አውራዎች ከዚሁ መሬት በዘልማድ ሢሶ እየተባለ የሚጠራ (በርግጥ ግን አንዳንዴ እስከ አንድ ስድስተኛ ዝቅ ሊል የሚችል) መሬት ይሰጣቸዋል። በገበሬዎች እጅ የቀረው መሬት «የገባር መሬት» ሲባል ለቤተ ክህነት «ሰሞን» ተብሎ የሚታወቅ መሬት ይሰጣል። የመንግሥት ባለሟሎች በደመወዝ ምትክ «ማደርያ» ተብሎ የሚጠራ መሬት ይሰጣቸዋል። ከዚህም ሌላ በተለይ ከቤተ መንግሥቱ ጋር የተያያዙ የመሬት ሥሪቶች ነበሩ። ሰነሱም ባልደራስና ወረገኑ (ለቤተ መንግሥቱ ፈረስና የእርድ ከብት የሚሰጥ)





3.4 ራስ ብሩ ወልደ ገብርኤል

እና ጋነገብ ወይም ማድቤት (ምስለኔ ሁዳድ እያሳረሰ ለቤተ መንግሥት አስፈላጊ የሆነውን እህል የሚያቀርብበት) ናቸው።

በዚህ የገባር ሥርዓት ውስጥ ገበሬና መንግሥትን እንደ ድልድይ ሆኖ የሚያገናኘው ሢሶ የተቀረጠለት ባላባት ነው። እርሱ የሥርዓቱ አስፈጻሚም ተጠቃሚም ነው፤ በወለጋ መሬት የተለካው በአባ ቆሮዎቹ አስተናባሪነት ነው። በሐረር ቁጥር ገባር የተደለደለው በደሚና ከሱም ዝቅ ሲል በገራዱ ነው። ከዚህም ከፍ ባለ ሁኔታ የሌቃ ነቀምቴ ገዥዎች በማዕከላዊው መንግሥት አምሳል የደረጀ የግብር ስልት አውጥተው ዐሥራት ሳይቀር ከዳርቻው አገር ይሰበስቡ ነበር። ባጠቃላይም ከደቡብ ሕዝብ መሪዎች ውስጥ የማዕከላዊ ገዥዎችን መደብ ባሕርይ በከፍተኛ ደረጃ መላበስ የቻሉት የወለጋ መሳፍንት ነበሩ። ይኸ ይኸ ሲታይ በኢትዮጵያ ውስጥ የነበረው የብዝበዛ መሠረት ባብዛኛው ብሔረ ሰባዊ ሳይሆን መደባዊ ነበር ከሚል መደምደሚያ ላይ እንደርሳለን።

ከዚህ በላይ በዝርዝር የቀረበው የመሬት ሥሪት አንባቢን ጥቂት ያደናግር ይሆናል። ነገሩን አበጥረን ስናየው ግን የተረፈ ምርት አወሳሰድ መደቡ የገባሩና የመልከኛው ግንኙነት ነው። ገባሩ ዋናው አምራቹ የሆነውን ያህል መልከኛው ደግሞ ስሙም እንደሚያመለክተው የመንግሥት የቅርብ ተጠሪ ነው። የመደብ ቅራኔ ገዛድ ወጥቶ የሚያፋጥጠውም ሁለቱን ነው። ገባሩ ሥርዓቱ ሲያንገሸግሸው በተለያየ መንገድ ተቃውሞውን ይገልጽ ነበር፤መሬቱን ጥሎ በመጥፋት፣ ለበላይ ባለሥልጣን ወይ ለንጉሠ ነገሥቱ አቤቱታ በማቅረብ፣ ወይ ገፍቶ ሲመጣበት ደግሞ በተለይ ማዕከሉ በሚናጋበት ወቅት በማመፅ።

ገባሩ ብሶቱን የሚያስተጋቡለት አጋሮችም አሳጣም ነበር:: ዘመናዊ ትምህርት የቀሰሙት የመጀመሪያዎቹ የኢትዮጵያ ምሁራን በጋዜጣም በመጽሐፍም የገባሩን ሁኔታ እየገለጹ ኑሮው እንዲሻሻልለት ይመክሩ ነበር:: በተጨማሪም ስያሜው ለጆሮ እንግዳ ቢመስልም «የቅኝ አገዛዝ አብዮተኞች» ሊሰኙ የሚችሉ አውሮጳውያን ታዛቢዎችም ነበሩ:: እነዚህ የገባሩ ሥርዓት ገበሬውን በማስለሉ ምክንያት የአውሮጳ ካፒታልም ሆነ ሸቀጥ በስፋት ወደ አገር እንዳይገባ በማድረጉ የኢትዮጵያ ኅብረተሰብ መሠረታዊ ለውጥ ያስፈልገዋል ብለው የሚከራከሩ ነበሩ:: ለምሳሌ «ዘታይምስ» የተባለው የለንደን ጋዜጣ እ.ኤ.አ በኤፕሪል 18፣ 1931 እትሙ የገባር ሥርዓትን «ከባርነት እጅግ የከፋ» ሥርዓት ብሎ ገልጾታል:: ኢትዮጵያውያን ምሁራኑና አወሮጳውያኑ ለገባሩ የሚያዝኑት በተለያየ ምክንያት ነው:: የመጀመሪያዎቹ ከሰብአዊ ርኅራኄና ብሔራዊ ቁጭት የተነሣ፣ የኋለኞቹ ባብዛኛው ከጥቅም አንፃር:: ላገሪቱ የተለሙላት የእድገት ጎዳናም እንዲሁ የተለያየ ነው:: የመጀመሪያዎቹ የጃፖንን አርአያ የሚከተል ነፃ ብሔራዊ ካፒታሊስት እድገት፣ የኋለኞቹ ጥገኛ ካፒታሊዝም::

ከገዥው መደብ አባላት ውስጥ ነቃ ነቃ ያሉትም ቢሆን የፊውዳሉን ሥርዓት አባካኝ ገጽታዎች አስወግደው ለእድገት የሚያመች ስልት ለመመሥረት ፍላጎት ነበራቸው:: ልጅ ኢያሱና አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን የወሰዷቸው ተከታታይ እርምጃዎች የግል ንብረትን በማጠናከር ለገጠሩ ኅብረተሰብ የማምረት ኃይል አመች ሁኔታዎች ለመፍጠር የሚጥሩ ነበሩ:: ለምሳሌ ኢያሱ የመንግሥት ንብረት ያባከነ መሬቱ ውርስ እንዲሆንበት የሚደነግገውን የቀድሞ ደንብ በመሻር የግል ሀብትን ከቡርነት አረጋግጧል:: በተጨማሪም ዐሥራት የሚገምቱ የመንግሥት ደንበኞች የገበሬውን የምርት መጠን እስኪገምቱ ድረስ መኸር አይሰበሰብም የሚለው ደንብ ገበሬው ከረምት ከበጋ ሳይለይ የለፋበትን እህል የሚያባክን ሆኖ ስላገኘው ገበሬው ቋሰ መሐላ ፈጽሞ ባመነው ብቻ ዐሥራት እንዲሰፍር ደንግጓል:: ተፈሪም እንዲሁ በውርስ እንዳይነጠቅ የተጀመረውን ማሻሻያ ከማጠናከሩም በላይ የዐሥራት አሰባሰብን የሚያቀላጥፉ እርምጃዎች ወስዷል:: በመጨረሻም ዘውድ ደፍቶ አፄ ኃይለ ሥላሴ ከሆነ በኋላ በግንቦት 1927 የግዴታ የጉልበት ሥራንና የማር ግብርን በዐዋጅ ሽሯል:: የዚህ ዐዋጅ ሌላው ጠቃሚ ገጽታ ብዙ ለውጥ ፈላጊ ምሁራን የደከሙለትን የቁርጥ ግብር ሥርዓት በጋሻ 30 ብር ሒሳብ እንዲሆን መደንገጉ ነበር:: ይሁን እንጂ የገባርን ሥርዓት እስከናካቴው የማስወገዱ ጉዳይ ከነፃነት ወዲህ እንጂ ከዚያ በፊት የሚታሰብ ነገር አልነበረም::

ገዥው መደብ የተደላደለ ኑሮውን የሚመራው በገባሩ ብቻ ሳይሆን በባሮችም ጉልበት ነበር:: በሁለቱ መካከል ያለው መሠረታዊ ልዩነት ገባሩ የስልተ ምርቱ መሠረት ሲሆን የባርያው አገልግሎት ግን በአብዛኛው በቤት ውስጥ የተወሰነ መሆኑ ነው:: ባሮች በምርት ተግባር ተሳተፉ ሊባሉ የሚችሉባቸው እንደ አባ ጅፋር እርሻዎች ያሉ ቦታዎች በጣም ጥቂቶች ነበሩ:: ያም ሆነ ይህ የገዥው መደብ የገባሩንም ሆነ የባርያውን ጉልበት የሚጠቀምበት ለመብላት ለመጠጣት እንጂ ሸቀጦች ለመለዋወጥ ወይም ገንዘብ ለማካበት አልነበረም:: ስለሆነም ለምሳሌ እንግሊዝ አገር እንደታየው መሳፍንቱና መኳንንቱ ራሳቸውን ወደ ንግድ ከበርቴነት ለመለወጥ የነበራቸው ዝንባሌና ችሎታ ውሱን ነበር:: ስለዚህም በአውሮጳና በጃፓንም እንደታየው ከኢትዮጵያ ፊውዳሊዝም ካፒታሊዝም ሊወለድ አልቻለም::



ባርነትና የባርያ ንግድ ከጥንት ጀምሮ የኢትዮጵያ ኅብረተሰብ ፀይነተኛ ገጽታ ሆነው የቆዩ ሲሆን፣ በ20ኛው መቶ ዓመት መጀመሪያ ላይ አዲስ ሕይወት እንዲዘሩ ያደረጋቸው ለባርያ ፍንገላ አመቺ ሁኔታዎች መፈጠራቸው ነው:: የምኒልክ ድንበር የማስፋት ፖሊሲ ፍትሕና ኃላፊነት በተሞላበት አስተዳደር አልታጀበም:: የጦር አዝማቾቹና ወታደሮቹ የአዲሶቹን ግዛቶች ሕዝብ እንደፈቀዳቸው የሚነዱት እንጂ በሥርዓት ሊያስተዳድሩትና ከጠላትም ሊጠብቁት የሚገባቸው ሆኖ አልታየቻውም:: ስለዚህ በተለይ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሰው እንደዱር አራዊት የሚታደንበት አውድማ ሆነ:: ነጋዴዎችና አዳኞች ወደዚያው እየዘመቱ ባርያና የዝሆን ጥርስ በገፍ ይዘው በመመለስ ቶሎ የመክበሪያ መንገድ አበጁ:: መኳንንቱ በሺ የሚቆጠሩ ባርያዎች ባለቤት ሆኑ:: እንደ አባ ጅፋር ያለው መሪማ የጥርስ ሐኪሙን ሒሳብ ባርያ በመስጠት ያወራርድ ነበር ተብሎ ይነገርለታል:: ባርያዎች በገጸ በረከት መልክ መለዋወጥም የተለመደ ነበር:: በአጭሩ አንድ መኰንን በኅብረተሰቡ ውስጥ ያለው ሚዛንና ግምት የሚለካው በባርያዎቹ ቁጥር ሆነ::

ይህ ለብዙ ዓመታት የቀጠለ የባርያ ፍንገላ በሕዝብ ቁጥርና ባጠቃላይም በማኅበራዊ ኑሮ ላይ ከባድ ጉዳትን አስከትሏል:: በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ የሚገኘው ሕዝብ የፍንገላው ዒላማ በመደረጉ ቀድሞ ከነበረው ብዛት እጅግ ሊመነምን በቅቷል:: ለምሳሌም በ1904 ልጅ ኢያሱ ራሱ ጊሚራ ላይ ባካሄደው ኢሰብአዊ ዘመቻ 40000 የሚያህሉ ጊሚራዎች ከቤት ንብረታቸው ተነቅለው በባርነት ተግዘዋል:: ብዙዎቹ ወደ መሀል አገር ሲነዱ በጉዞው ላይ ሞተዋል:: ከተረፉት መሀል ጥቂቶቹ ስድስት ኪሎ አጠገብ ሰፍረው ነው ጊሚራ ሰፈር የሚለውን ስያሜ ለትውልድ ለማስተላለፍ የበቁት:: በከፋና በማጂም እንዲሁ አያሌ ተመሳሳይ ጉዳት ደርሷል:: እንዲህ ያለ ሕይወትና ነፃነት ያልተረጋገጠበት ሁኔታ ለምርትና ለንግድ እንቅስቃሴ ከቶም አመቺ አልነበረም:: ሌላው የዚህ የፍንገላ ታሪክ ጎጂ ጎን ደግሞ ትቶ ያለፈው ስነ ልቦናዊ ጠባሳ ነው:: እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በመሀል አገርና በደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች መካከል የነበረው ግንኙነት በእኩልነት የተመሠረተ ሳይሆን የበላይነትና የበታችነት ስሜት የተንተራሰ ሆኖ ቆይቷል::

በዓለም አቀፍ ግንኙነት ረገድም ባርነትና የባርያ ንግድ በኢትዮጵያ ላይ ብዙ መዘዝ አምጥቶባታል:: በተለይ በአካባቢው ያሉት የአውሮጳ ቅኝ ገዥዎች አንዳንዴ ወደ ግዛቶቻቸው ዘልቆ የሚሄደውን ፍንገላ ሰበብ በማድረግ በኢትዮጵያ ላይ በየጊዜው ተጽዕኖ ያደርጉ ነበር:: ከመቶ ዓመት በፊት እነሱ ራሳቸው የአፍሪቃን ሕዝብ በባርነት እየነዱ ብዙም ትርፍ አካብተው ነበር:: ባርነት እንዲህ በቀላሉ የሚወገድ ሥርዓት እንዳልሆነም አንዳንዶቻቸው መረዳታቸው አልቀረም:: አንድ እንግሊዛዊ ታዛቢ «ባርነትን ከምድረ ኢትዮጵያ ከመንቀል የእንግሊዝን የካፒታሊስት ሥርዓት መሻር ይቀላል» ብሎ ጽፏል:: ይህ ሁሉ እየታወቀ ኢትዮጵያ በተአምር ባርነትን ከመቅጽበት እንድታስወግድ ይጠበቅ ነበር:: የዓለም መንግሥታት ማኅበር ለመግባት ደጅ እንድትጠና የተደረገችውም ገና ያልሠለጠነች የባሮችና የባርያ ፈንጋዮች ጉረኖ ናት በሚል ሰበብ ነበር:: ከዚህም በላይ የፍንገላውን እንቅስቃሴ ይገታል በሚል ምክንያት የተደረገባት የጦር መሣሪያ ማዕቀብ እጅና እግሯን አስሮ ለኢጣልያ ወረራ ዳረጋት:: ወረራውን ራሱንም ቢሆን ጣልያኖች በዓለም ፊት ተቀባይነት ለማስጠት የሞከሩት ባርነትን የመሰለ አስከፊ ሥርዓት የምታስተናግድ አገር ማስገበር

ለዓለም ሥልጣኔ መስፋፋት አንድ የተቀደሰ አስተዋፅኦ ማድረግ ይሆናል በሚል ሽንገላ ነው።

በመጨረሻ ዓለም አቀፍ ተጽዕኖና ያገር ውስጥ ሂደቶች ተጋግዘው ባርነትና የባርያ ንግድ ቀስ በቀስ እየቀነሱ እንዲመጡ ረዱ። የቀድሞ ነገሥታት ቴዎድሮስና ምኒልክ ይህን በሰው የመነገድ ባህል ለማስቀረት አንዳንድ ካንገት በላይ የሆኑ እርምጃዎች የወሰዱ ቢሆንም፣ በነገሩ ላይ በርግጥም ለውጥ መምጣት የተጀመረው በራስ ተፈሪ መኩንን ዘመን ነው። እንደ አውሮጳ አቆጣጠር በ1920ዎቹ መጀመሪያ ላይ በተለይ በእንግሊዝ ጋዜጦች በኢትዮጵያ ላይ የተካሄደው የተቀነባበረ ዘመቻ ለዚህ ለውጥ አንዱ ምክንያት ነበር። ከዚህም ጠለቅ ሲል በኢትዮጵያ ኅብረተሰብ ሥር እየሰደዱ የመጡት አንዳንድ ለውጦች የባርያን አስፈላጊነት ቀነሱት። የገኘው መደብ የኑሮ ስልት እየተለወጠ ሲመጣ ብዙ ባርያዎች ማሳደሩ ከትርፉ ኪሳራው እያመዘነ መጣ። የባርያ ንግድንና ኋላም ባርነትን ለመሻር የወጡት ደንቦችና ዐዋጆች የዚህ ድምር ግፊት ውጤት ናቸው። በመጀመሪያ የባርያ ንግድ በዐዋጅ ሲከለከል፣ በመጋቢት 16፣ 1916 የወጣ ዐዋጅ ደግሞ ባሮች ቀስ በቀስ ነፃ እንዲወጡ ደነገገ። እነዚህን ዐዋጆች ተከታትሎ የሚያስከብር ጽ/ቤትም ተቋቋመ። ነፃ የወጡትን ባሮች ልጆች ሙያ አስተምሮ ራሳቸውን እንዲችሉ ለማድረግም ት/ቤት ተከፈተ። ትምህርት ቤቱን እንዲያስተዳድር የተመረጠው ከሕይወቱ አብዛኛውን ጊዜ ከእንግሊዞች ጋር ያሳለፈውና ባርነትን በጽኑ ይቃወሙ ከነበሩት አንዱ ሐኪም ወርቅነህ ነበር። ከጥቂት ዓመታት በኋላም የፀረ ባርነት ቢሮው ባዲስ መልክ ተደራጅቶ በእንግሊዛዊው አማካሪ በፍራንክ ደሃልፔርት እንዲመራ ተደረገ።

## ንግድ

ከመሬት ቀጥሎ ሌላው የገዢው መደብ የገቢ ምንጭ ንግድ ነበር። ስለሆነም የንግድ መሥመሮችንና ቀረጥን መቆጣጠር የፖለቲካ ሥልጣን ትግል አንዱ ገፅታ ሆነ። ከ19ኛው መቶ ዓመት ሁኔታ ጋር ሲነፃፀር የንግድን መሥመር በተመለከተ በ20ኛው መቶ ዓመት አንድ ዐቢይ ለውጥ ተካሂዶ ነበር። ይኸውም ቀድሞ በሁለተኛ ደረጃ የነበረው ወደ ምሥራቅ የሚያመራው የንግድ መሥመር አሁን ቀዳሚ ስፍራ መያዙ ነው። ይህ ለውጥ እንዲከሠት ከረዱት ሁኔታዎች አንዱ በእምባበ ጦርነት የሸዋ መንግሥት ያገኘው ድል ነው። በዚህ ድል አማካይነት ሸዋ ግዛቷን አቋርጦ የሚሄደውን መሥመር ስታዳብር ጎጃምና ጉንደርን አቋርጦ ይሄድ የነበረው መሥመር እየከሰመ ሄደ። ሌላው ለዚህ ሁኔታ አጋዥ የሆነው ደግሞ በኢትዮጵያና ማህዲስት ሱዳን ጦርነት ምክንያት የመተማና የጉንደር የንግድ መዲናነት መቀዝቀዝ ነው። በተለይ ጉንደር ከ1880ው የማህዲስት ወረራ በኋላ ክፉኛ ተመትታለች። የፖለቲካው ማዕከል ወደ ደቡብ መዞር፣ ማለትም የአዲስ አበባ መቆርቆርና የምኒልክ አፄያዊ ዙፋን መጨበጥ፣ ሂደቱን አጠናከረው። ከኢትዮጵያና ኢጣልያ የጦር ፍጥጫ በኋላ የመረብ ምላሽ ግዛት (ኤርትራ) በባዕድ አገዛዝ ሥር ስትወድቅ የኢትዮጵያ ዋና የውጭ ንግድ በርም ከምፅዋ ወደ ጅቡቲ ተዛወረ። ጅቡቲ ምፅዋን ብቻ ሳይሆን ዘይላና በርበራንም ተክታ እስከ 20ኛው መቶ ዓመት አጋማሽ ድረስ የኢትዮጵያ ዋና የባሕር በር ለመሆን በቃች።





3.5 መሀል አዲስ አበባ፣ የኋላው ፒያሳ


ለዓለም ሥልጣኔ መስፋፋት አንድ የተቀደሰ አስተዋፅኦ ማድረግ ይሆናል በሚል ሽንገላ ነው።

በመጨረሻ ዓለም አቀፍ ተጽዕኖና ያገር ውስጥ ሂደቶች ተጋግዘው ባርነትና የባርያ ንግድ ቀስ በቀስ እየቀነሱ እንዲመጡ ረዱ። የቀድሞ ነገሥታት ቴዎድሮስና ምኒልክ ይህን በሰው የመነገድ ባህል ለማስቀረት አንዳንድ ካንገት በላይ የሆኑ እርምጃዎች የወሰዱ ቢሆንም፣ በነገሩ ላይ በርግጥም ለውጥ መምጣት የተጀመረው በራስ ተፈሪ መኰንን ዘመን ነው። እንደ አውሮጳ አቆጣጠር በ1920ዎቹ መጀመሪያ ላይ በተለይ በእንግሊዝ ጋዜጦች በኢትዮጵያ ላይ የተካሄደው የተቀነባበረ ዘመቻ ለዚህ ለውጥ አንዱ ምክንያት ነበር። ከዚህም ጠለቅ ሲል በኢትዮጵያ ኅብረተሰብ ሥር እየሰደዱ የመጡት አንዳንድ ለውጦች የባርያን አስፈላጊነት ቀነሱት። የገኘው መደብ የኑሮ ስልት እየተለወጠ ሲመጣ ብዙ ባርያዎች ማሳደሩ ከትርፉ ኪሳራው እያመዘነ መጣ። የባርያ ንግድንና ኋላም ባርነትን ለመሻር የወጡት ደንቦችና ዐዋጆች የዚህ ድምር ግፊት ውጤት ናቸው። በመጀመሪያ የባርያ ንግድ በዐዋጅ ሲከለከል፣ በመጋቢት 16፣ 1916 የወጣ ዐዋጅ ደግሞ ባሮች ቀስ በቀስ ነፃ እንዲወጡ ደነገገ። እነዚህን ዐዋጆች ተከታትሎ የሚያስከብር ጽ/ቤትም ተቋቋመ። ነፃ የወጡትን ባሮች ልጆች ሙያ አስተምሮ ራሳቸውን እንዲችሉ ለማድረግም ት/ቤት ተከፈተ። ትምህርት ቤቱን እንዲያስተዳድር የተመረጠው ከሕይወቱ አብዛኛውን ጊዜ ከእንግሊዞች ጋር ያሳለፈውና ባርነትን በጽኑ ይቃወሙ ከነበሩት አንዱ ሐኪም ወርቅነህ ነበር። ከጥቂት ዓመታት በኋላም የፀረ ባርነት ቢሮው ባዲስ መልክ ተደራጅቶ በእንግሊዛዊው አማካሪ በፍራንክ ደሃልፔርት እንዲመራ ተደረገ።

### ንግድ

ከመሬት ቀጥሎ ሌላው የገዢው መደብ የገቢ ምንጭ ንግድ ነበር። ስለሆነም የንግድ መሥመሮችንና ቀረጥን መቆጣጠር የፖለቲካ ሥልጣን ትግል አንዱ ገፅታ ሆነ። ከ19ኛው መቶ ዓመት ሁኔታ ጋር ሲነፃፀር የንግድን መሥመር በተመለከተ በ20ኛው መቶ ዓመት አንድ ዐቢይ ለውጥ ተካሂዶ ነበር። ይኸውም ቀድሞ በሁለተኛ ደረጃ የነበረው ወደ ምሥራቅ የሚያመራው የንግድ መሥመር አሁን ቀዳሚ ስፍራ መያዙ ነው። ይህ ለውጥ እንዲከሠት ከረዱት ሁኔታዎች አንዱ በእምባቦ ጦርነት የሸዋ መንግሥት ያገኘው ድል ነው። በዚህ ድል አማካይነት ሸዋ ግዛቷን አቋርጦ የሚሄደውን መሥመር ስታዳብር ጎጃምና ጐንደርን አቋርጦ ይሄድ የነበረው መሥመር እየከሰመ ሄደ። ሌላው ለዚህ ሁኔታ አጋዥ የሆነው ደግሞ በኢትዮጵያና ማህዲስት ሱዳን ጦርነት ምክንያት የመተማና የጐንደር የንግድ መዲናነት መቀዝቀዝ ነው። በተለይ ጐንደር ከ1880ው የማህዲስት ወረራ በኋላ ክፉኛ ተመትታለች። የፖለቲካው ማዕከል ወደ ደቡብ መዞር፣ ማለትም የአዲስ አበባ መቆርቆርና የምኒልክ አፄያዊ ዙፋን መጨበጥ፣ ሂደቱን አጠናከረው። ከኢትዮጵያና ኢጣልያ የጦር ፍጥጫ በኋላ የመረብ ምላሽ ግዛት (ኤርትራ) በባዕድ አገዛዝ ሥር ስትወድቅ የኢትዮጵያ ዋና የውጭ ንግድ በርም ከምፅዋ ወደ ጅቡቲ ተዛወረ። ጅቡቲ ምፅዋን ብቻ ሳይሆን ዘይላና በርበራንም ተክታ እስከ 20ኛው መቶ ዓመት አጋማሽ ድረስ የኢትዮጵያ ዋና የባሕር በር ለመሆን በቃች።





3.5 መሀል አዲስ አበባ፣ የኋላው ፒያሳ



3.6 ከፈረንሳይ ለመጣ የልዑካን ቡድን ክብር ግብዣ በተደረገበት ወቅት

ሌላው የ20ኛው መቶ ዓመት መጀመሪያ ንግድ ባሕሪ በቀጥታ ከዐድዋ ድል ውጤት የመነጨ ነው:: ኢትዮጵያን ዙሪያዋን ያጠሯት ቅኝ ገዥዎች ዋና ጥረታቸው አዋሳኝ የሆነውን ያገሪቱን ክፍል ከቅኝ ግዛታቸው ጋር በንግድ ማስተሳሰር ሆነ:: የንግድ መተሳሰር ውሎ አድሮ ለፖለቲካ ቁጥጥርም ያመቻል የሚል እምነት ነበር:: በዚህ ዓይነት በኢጣልያ የተሞከረው ኢትዮጵያን ቅኝ የማድረግ ሐሳብ ሲከሽፍ ሁሉም በየፊናው የንግድ ተጽዕኖ ክልሉን ለማስፋፋት መሯሯጥ ያዘ:: በየዳር አገሩ ቆንስላ ማቋቋሙም ከዚሁ ጥረት ጋር የተያያዘ ነው:: ይህ ጥረት በተለይ ጎልቶ የሚታየው ከኢትዮጵያ ጋር እጅግ ረጅሙን ወሰን በምትጋራው በእንግሊዝ ዘንድ ነው:: እንግሊዞች ሦስቱን አዋሳኝ ግዛቶቻቸውን ተቆናጠው የንግድ መረባቸወን ዘረጉ:: ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያን ከምኒልክ በምረት ባገኙት በጋምቤላ አማካኝነት ወደ ሱዳን፣ ደቡብ አትዮጵያን ወደ ኬንያ፣የሐረርን ክፍል ደግሞ ወደ እንግሊዝ ሶማሊላንድ ለመሳብ ጥረታቸውን ቀጠሉ:: ለዚህ የሚረዷቸውን ቆንስላዎቻቸውንም በሐረር፣ በሜጋ፣ በጎሬና በዳንግላ አቋቋሙ:: ጣልያኖችም በተመሳሳይ መንገድ የሰሜን አትዮጵያን አካባቢ ከኤርትራ ጋር በንግድ ለማስተሳሰር የተቻላቸውን ሁሉ አደረጉ:: ቆንስላዎቻቸውን በዐድዋ፣ በደሴና በጉንደር አቋቋሙ:: ፈረንሳዮች በአካባቢው እጅግ አነስተኛ የሆነውን ቅኝ ግዛት ቢይዙም እንኳ የአትዮጵያ ዋና የንግድ የደም



ሥር የነበረው የባቡር መሥመር በቁጥጥራቸው ሥር ስለነበር የእንግሊዝና የኢጣልያንን ያህል መራወጥ አልነበረባቸውም:: ምንም ቅኝ ግዛት የሌላቸው ጀርመንና አሜሪካ ደግሞ በዳር አገሩ ተስፋም ስላልነበራቸው ትኩረታቸው በመሀሉ አገር የንግድ የበላይነቱን ማግኘቱ ላይ ሆነ::

የዳር አገሩን ንግድ ወደ አዋሳኝ ቅኝ ግዛቶች ለመሳብ ብዙ ጥረት ቢደረግም፣ የኢትዮጵያን የውጭ ንግድ በተመለከተ የጅቡቲ የበላይነት ከቶም አጠያያቂ አልነበረም:: ባማካይ ሰባ አምስት ከመቶ የሆነው ንግድ የሚተላለፈው በጅቡቲ በኩል ነበር:: ከዚያ በኋላ በርቀት የሚፎካከሩት የኤርትራ፣ የሱዳንና የእንግሊዝ ሶማሊላንድ የንግድ መሥመሮች (በዚያው ቅደም ተከተል) ነበሩ:: ወደ ኬንያ (ወይም በዚያን ጊዜ አጠራሩ የእንግሊዝ ምሥራቅ አፍሪቃ) እና ወደ ኢጣልያ ሶማሊላንድ የሚሄደው ንግድ ይህን ያህልም ከቁጥር የሚገባ አልነበረም:: በሌላ በኩል ወጪ ንግድን በተመለከተ የሱዳን መሥመሩ ድርሻ ከፍ ያለ ነበር:: ለምሳሌ በ1922 ገደማ 20 ከመቶ ደርሶ ነበር:: ይኸም የሆነበት ምክንያት በአብዛኛው በደቡብ ምዕራብ የሚበቅለው የአትዮጵያ የቡና ሀብት ወደ ውጭ የሚወጣው በሱዳን በኩል ስለሆነ ነው:: በዚህም ምክንያት በሱዳን በኩል የወጪው ንግድ ከገቢው ንግድ የተሻለ ሚዛን ያሳይ ነበር:: ባንፃሩም በጅቡቲው መሥመር ተቃራኒ ሁኔታ ነበር:: ይህም የሚያመለክተው የባቡሩ መሥመር በጋምቤላ በኩል ከነበረው የጀልባ ንግድ ይልቅ ምን ያህል ኢትዮጵያን የዓለም የንግድ አካል እንዳደረጋት ነው::

የንግድ ሸቀጦችን በተመለከተም ከ19ኛው መቶ ዓመት የታለየ ሁኔታ ነበር:: የዝሆን ጥርስና ዝባድ የመሳሰሉት ቀድሞ ጎላ ብለው ይታዩ የነበሩት ሸቀጦች አላቂ ከመሆናቸው የተነሣ እየከሰሙ መጡ:: በቦታቸው እስካሁንም ጉልህ ስፍራ ይዞ የቆየው ቡና ተተካ:: ወደ አገር በሚገቡት ሸቀጦች በኩል ደግሞ የቡና አቻ ለልብስና ለድንኳን በጣም ተፈላጊ የሆነው አቡጀዲ ነበር:: የውጭ መንግሥታት የንግድ ፉክክርም በአብዛኛው ይሽከረከር የነበረው በዚሁ ሸቀጥ ዙሪያ ነበር:: መጀመሪያ አሜሪካኖችን፣ ኋላ ደግሞ ጃፖኖችን ወደ ምድረ አትዮጵያ ያመጣቸውም ይኸው አቡጀዲ ነው:: የባቡር ሐዲድ ተዘርግቶ ሲያልቅ ደግሞ የሕዝቡም የፍጆታ ፍላጎት እየተራቀቀ መጥቶ እነ ውስኪና ብራንዲ መለመድ ጀመሩ::

የኢትዮጵያ የውጭ ንግድ በአብዛኛው በውጭ አገር ዜጎች እጅ ነበር:: ይህም በ19ኛው መቶ ዓመት ከነበረው ሁኔታ የተለየ ነበር:: እንዲህም የሆነበት ምክንያት ከዐድዋ ድል በኋላ ብዙ የውጭ ሀገር ዜጎች በተለያየ መስክ እድላቸውን ለመሞከር ወደ ኢትዮጵያ ስለጎረፉ ነው:: በመጀመሪያ በዐድዋ ጦርነት ወቅት ፈረንሳይ የጦር መሣሪያ ወደ ኢትዮጵያ እንዲገባ ባሳየችው ትብብር ምክንያት ባገኘችው ጥሩ ስም ተጠቅመው የፈረንሳይ ዜጎች በንግዱ ቀዳሚውን ስፍራ ይዘው ነበር:: ከነዚህም ውስጥ የባቡር ውል ከምኒልክ ጋር የተፈራረመውና የንጉሠ ነገሥቱ የቅርብ አማካሪ የነበረው ሊእን ሽፍነና ኤ.ሲ.ሳቡሬ የተባሉት ነጋዴዎች ይገኙበታል:: የኋላ ኋላ ግን የእንግሊዝ ዜጎች የነበሩት የሕንድ ተወላጆች ፈረንሳዮቹን እየበለጧቸው መጡ:: ሕንዶች የበላይነት እንዲያገኙ የረዳቸው ዋነኛው ምክንያት በቁጠባ እየኖሩ በቀላል ወጪ ንግዳቸውን ለማንቀሳቀስ መቻላቸው ነው:: እስከ ጣልያን ወረራ ድረስ አብዛኛውን ያገሪቱን የውጭ ንግድ ያንቀሳቅስ የነበረው መሐመድ ዓሊ የሕንድ ነጋዴዎቹ ቁንጮ ነበር::



3.6 ከፈረንሳይ ለመጣ የልዑካን ቡድን ክብር ግብዣ በተደረገበት ወቅት

ሌላው የ20ኛው መቶ ዓመት መጀመሪያ ንግድ ባሕሪ በቀጥታ ከዐድዋ ድል ውጤት የመነጨ ነው። ኢትዮጵያን ዙሪያዋን ያጠሯት ቅኝ ገዥዎች ዋና ጥረታቸው አዋሳኝ የሆነውን ያገሪቱን ክፍል ከቅኝ ግዛታቸው ጋር በንግድ ማስተሳሰር ሆነ። የንግድ መተሳሰር ውሎ አድሮ ለፖለቲካ ቁጥጥርም ያመቻል የሚል እምነት ነበር። በዚህ ዓይነት በኢጣልያ የተሞከረው ኢትዮጵያን ቅኝ የማድረግ ሐሳብ ሲከሽፍ ሁሉም በየፊናው የንግድ ተጽዕኖ ክልሉን ለማስፋፋት መሯሯጥ ያዘ። በየዳር አገሩ ቆንስላ ማቋቋሙም ከዚሁ ጥረት ጋር የተያያዘ ነው። ይህ ጥረት በተለይ ጎልቶ የሚታየው ከኢትዮጵያ ጋር እጅግ ረጅሙን ወሰን በምትጋራው በእንግሊዝ ዘንድ ነው። እንግሊዞች ሦስቱን አዋሳኝ ግዛቶቻቸውን ተቆናጠው የንግድ መረባቸውን ዘረጉ። ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያን ከምኒልክ በምሪት ባገኙት በጋምቤላ አማካኝነት ወደ ሱዳን፣ ደቡብ ኢትዮጵያን ወደ ኬንያ፣የሐረርን ክፍል ደግሞ ወደ እንግሊዝ ሶማሊላንድ ለመሳብ ጥረታቸውን ቀጠሉ። ለዚህ የሚረዷቸውን ቆንስላዎቻቸውንም በሐረር፣ በሜጋ፣ በጎሬና በዳንግላ አቋቋሙ። ጣልያኖችም በተመሳሳይ መንገድ የሰሜን ኢትዮጵያን አካባቢ ከኤርትራ ጋር በንግድ ለማስተሳሰር የተቻላቸውን ሁሉ አደረጉ። ቆንስላዎቻቸውን በዐድዋ፣ በደሴና በጐንደር አቋቋሙ። ፈረንሳዮች በአካባቢው እጅግ አነስተኛ የሆነውን ቅኝ ግዛት ቢይዙም እንኳ የኢትዮጵያ ዋና የንግድ የደም



ሥር የነበረው የባቡር መሥመር በቁጥጥራቸው ሥር ስለነበር የእንግሊዝና የኢጣልያንን ያህል መራወጥ አልነበረባቸውም። ምንም ቅኝ ግዛት የሌላቸው ጀርመንና አሜሪካ ደግሞ በዳር አገሩ ተስፋም ስላልነበራቸው ትኩረታቸው በመሀሉ አገር የንግድ የበላይነቱን ማግኘቱ ላይ ሆነ።

የዳር አገሩን ንግድ ወደ አዋሳኝ ቅኝ ግዛቶች ለመሳብ ብዙ ጥረት ቢደረግም፣ የኢትዮጵያን የውጭ ንግድ በተመለከተ የጅቡቲ የበላይነት ከቶም አጠያያቂ አልነበረም። ባማካይ ሰባ አምስት ከመቶ የሆነው ንግድ የሚተላለፈው በጅቡቲ በኩል ነበር። ከዚያ በኋላ በርቀት የሚፎካከሩት የኤርትራ፣ የሱዳንና የእንግሊዝ ሶማሊላንድ የንግድ መሥመሮች (በዚያው ቅደም ተከተል) ነበሩ። ወደ ኬንያ (ወይም በዚያን ጊዜ አጠራሩ የእንግሊዝ ምሥራቅ አፍሪቃ) እና ወደ ኢጣልያ ሶማሊላንድ የሚሄደው ንግድ ይህን ያህልም ከቁጥር የሚገባ አልነበረም። በሌላ በኩል ወጪ ንግድን በተመለከተ የሱዳን መሥመሩ ድርሻ ከፍ ያለ ነበር። ለምሳሌ በ1922 ገደማ 20 ከመቶ ደርሶ ነበር። ይኸም የሆነበት ምክንያት በአብዛኛው በደቡብ ምዕራብ የሚበቅለው የኢትዮጵያ የቡና ሀብት ወደ ውጭ የሚወጣው በሱዳን በኩል ስለሆነ ነው። በዚህም ምክንያት በሱዳን በኩል የወጪው ንግድ ከገቢው ንግድ የተሻለ ሚዛን ያሳይ ነበር። ባንፃሩም በጅቡቲው መሥመር ተቃራኒ ሁኔታ ነበር። ይህም የሚያመለክተው የባቡሩ መሥመር በጋምቤላ በኩል ከነበረው የጀልባ ንግድ ይልቅ ምን ያህል ኢትዮጵያን የዓለም የንግድ አካል እንዳደረጋት ነው።

የንግድ ሸቀጦችን በተመለከተም ከ19ኛው መቶ ዓመት የተለየ ሁኔታ ነበር። የዝሆን ጥርስና ዝባድ የመሳሰሉት ቀድሞ ጎላ ብለው ይታዩ የነበሩት ሸቀጦች አላቂ ከመሆናቸው የተነሣ እየከሰሙ መጡ። በቦታቸው እስካሁንም ጉልህ ስፍራ ይዞ የቆየው ቡና ተተካ። ወደ አገር በሚገቡት ሸቀጦች በኩል ደግሞ የቡና እቻ ለልብስና ለድንኳን በጣም ተፈላጊ የሆነው አቡጀዲ ነበር። የውጭ መንግሥታት የንግድ ፉክክርም በአብዛኛው ይሽከረከር የነበረው በዚሁ ሸቀጥ ዙሪያ ነበር። መጀመሪያ አሜሪካኖችን፣ ኋላ ደግሞ ጃፓኖችን ወደ ምድረ ኢትዮጵያ ያመጣቸውም ይኸው አቡጀዲ ነው። የባቡር ሐዲድ ተዘርግቶ ሲያልቅ ደግሞ የሕዝቡም የፍጆታ ፍላጎት እየተራቀቀ መጥቶ እነ ውስኪና ብራንዲ መለመድ ጀመሩ።

የኢትዮጵያ የውጭ ንግድ በአብዛኛው በውጭ አገር ዜጎች እጅ ነበር። ይህም በ19ኛው መቶ ዓመት ከነበረው ሁኔታ የተለየ ነበር። እንዲህም የሆነበት ምክንያት ከዐድዋ ድል በኋላ ብዙ የውጭ ሀገር ዜጎች በተለያየ መስክ እድላቸውን ለመሞከር ወደ ኢትዮጵያ ስለጎረፉ ነው። በመጀመሪያ በዐድዋ ጦርነት ወቅት ፈረንሳይ የጦር መሣሪያ ወደ ኢትዮጵያ እንዲገባ ባሳየችው ትብብር ምክንያት ባገኘችው ጥሩ ስም ተጠቅመው የፈረንሳይ ዜጎች በንግዱ ቀዳሚውን ስፍራ ይዘው ነበር። ከነዚህም ውስጥ የባቡር ውል ከምኒልክ ጋር የተፈራረመውና የንጉሡ ነገሥቱ የቅርብ አማካሪ የነበረው ሊኦን ሼፍነና ኢ.ሲ.ሳቡሬ የተባሉት ነጋዴዎች ይገኙበታል። የኋላ ኋላ ግን የእንግሊዝ ዜጎች የነበሩት የሕንድ ተወላጆች ፈረንሳዮቹን እየበለጧቸው መጡ። ሕንዶች የበላይነት እንዲያገኙ የረዳቸው ዋነኛው ምክንያት በቁጠባ እየኖሩ በቀላል ወጪ ንግዳቸውን ለማንቀሳቀስ መቻላቸው ነው። እስከ ጣልያን ወረራ ድረስ አብዛኛውን ያገሪቱን የውጭ ንግድ ያንቀሳቅስ የነበረው መሐመድ ዓሊ የሕንድ ነጋዴዎቹ ቁንጮ ነበር።

በተለይም በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ደግሞ እንደ ሕንዶች የቀናቸው ግሪኮች ነበሩ። እንደ ክርስቲያን ኢትዮጵያውያን እነሱም የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች መሆናቸው በኢትዮጵያ ኅብረተሰብ ውስጥ በቀላሉ ለመዋሐድ ረድቷቸው ነበር። ኅብረተሰቡን በመምሰል ከፍተኛውን ደረጃ የያዙት እንደ ግሪኮች ኦርቶዶክስ የሆኑትና በተጨማሪም በትውልድ ሀገራቸው ከተከፈተባቸው ፍጅት እምልጠው የመጡ በመሆናቸው ከኢትዮጵያ ሌላ አገር ያልነበራቸው አርመኖች ናቸው። አርመኖች የተሰማሩት አብዛኛውን ከንግድ ይልቅ በእጅ ሙያ ነበር። ዝነኛ ከነበሩት አርመኖች አንዱ ለምኒልክ ከውጭ የጦር መሣሪያ በማቅረብና በስሙ የሰርኪስ ባቡር የተባለውን የመጀመሪያውን ዳምጠው ወደ ኢትዮጵያ በማምጣት የታወቀው ሰርኪስ ቴርዝያን ነው። ያ ዳምጠው («ባቡር») ሰባራ ባቡር ተብሎ የሚጠራው አካባቢ ተሰናክሎ መቅረቱንም የዘመኑ ሰው በሚከተለው ግጥም ሕያው አድርጎት ቆይቷል፤

ብነግርሽ ብነግርሽ አታጠናቅሪ
እንደ ሰርኪስ ባቡር ተገትረሽ ቅሪ

እንደዚሁም አይሁዳዊው ነጋዴ በኒን በስሙ ሰፈር (በኒን ሰፈር) ሊሰየምለት በቅቷል። የእንግሊዝ ዜግነት የነበረው በትውልድ ሶርያዊው ሐሲብ ይድልቢ ደግሞ የንግዱንና የሞኖፖሉን ውል ዓለም ካሰስ በኋላ የኢያሱን ልብ ማርኮ ከፍተኛ ባለሟል እስከመሆን ደርሷል። በሱ ጥላ ሥር ያደገው ያገሩ ተወላጅ የሆነው መጅድ ዐቡድም በምዕራብ ኢትዮጵያ በላስቲክ ንግድ ወኪልነት ጀመረና ኋላም የመንግሥት ሹም ሆኖ እጉዋኮችን በማስገበር ከፍተኛ የታሪክ ሚና ተጫውቷል። ጊዜው እየገፋ ሲሄድ እንደነይድልቢ ያሉት ጀብደኞች ስከንና ደርጅት ላሉት የአውሮጳ ኩባንያዎች (ለምሳሌ የእንግሊዙ ሴፌሪያንና የፈረንሳዩ ቤስ፣ በተለምዶ አጠራር ቢስ) ሥፍራውን ይለቃሉ።

የኢትዮጵያውያን ነጋዴዎች ድርሻ የአገር ውስጥና ያካባቢ ንግድ ነበር። በሌላ ወገን ደግሞ አዲስ የተከሰተው ሁኔታ የገኘው መደብ ከዐድዋ በፊት የነበረውን የጦረኛነት ባሕሪ ቀስ በቀስ እየተወ የንግድ ስሜቱ እያቆጠቆጠ መምጣቱ ነው። ስለሆነም በገኘው መደብ አባላትና በውጭ አገር ነጋዴዎችና የሞኖፖል ባለውሎች መካከል በርከት ያሉ አትራፊ ሽርክናዎች ተመሠረቱ። ምኒልክ ለሕንድ ነጋዴዎች ገንዘብ ማበደር ሲጀምር ጣይቱ ደግሞ እቴጌ የተሰኘ ውን ሆቴል ከፈተች፤ ይህም ሆቴል በአዲስ አበባ የመጀመሪያው መሆኑ ነው። ጣይቱ ከዚህም አልፋ የዘመኑ ታላላቅ መሳፍንት የተሳተፉበትን የዘመናችን የልማት ባንክ መቅድም የሆነውን የእርሻና የንግድ ማስፋፊያ ማኅበር የተባለ ድርጅት አቋቋመች። ራስ ተፈሪም እንዲሁ የኤረርን የአትክልት እርሻ በመመሥረትና ቡሬንና ጋምቤላን የሚያገናኘው የመንገድ ሥራ ኩባንያ ዋነኛ ባለአክሲዮን በመሆን በንግዱ ዓለም መሪ ተዋናይ ሲሆን በፖለቲካውም በኢኮኖሚውም ተቀናቃኝ የሆነው የጉጃሙ ራስ ኃይሉ ደግሞ አዲስ አበባ ውስጥ ሲኒማ ቤት በመክፈት (ራስ ኃይሉ ሲኒማ፣ የዛሬው ራስ ቴአትር) እና ታክሲዎች በማሰማራት ተፎካክሮታል። የራስ ተፈሪን ልጅ ተናኘ ወርቅን የሚያገባው ራስ ደስታ ዳምጠው ደግሞ በዋና ከተማይቱ የሸያጭ ውሀ ያቀርብ እንደነበር ይነገራል።

መሳፍንቱ እንዲህ ዓይነቱን የንግድ እንቅስቃሴ ያካሂዱ እንጂ ዋና ትኩረታቸው ያረፈው በጉምሩክ ቀረጥ ላይ ነው። በዚህ ረገድም ሽቀጥ እየቀረጠ



ገቢ የሚያስገኘው ነጋድራሱ ነው። ቀደም ብለን እንዳየነው ወትሮ ነጋድራስ ማለት የነጋዴዎች ራስ ወይም አለቃ ማለት ነበር። የኋላ ኋላ ግን በተለይ በጉንደር የተጀመረው ሂደት ቀጥሎ ነጋድራሱ ከነጋዴነት ወደ መንግሥት ሹምነት ተሸጋገረ። ይህም ሂደት በ20ኛው መቶ ዓመት መጀመሪያ ላይ ፍጹም ተረጋገጠ የቀድሞ ትርጉሙ ደብዛው እየጠፋ ሄደ። የጉምሩክ ቀረጥ ለመንግሥት አስፈላጊነቱ እየጎላ ሲሄድ፣ እሱ የሚባሉት ያገሪቱ ጭንቅላቶችም ለዚህ ተግባር ይታጩ ጀመር። በማስረጃነትም የዘመኑ ምሁራን ቁንጮዎች የነበሩት ገብረ ሕይወት ባይከዳኝና አፈወርቅ ገብረ ኢየሱስ እስካሁንም የሚታወቁት በነጋድራስነት ማዕረጋቸው መሆኑን መጥቀስ ይቻላል።

ይህ ለጉምሩክ የሚሰጠው ልዩ ትኩረት በምኒልክ ጊዜ ይጀምርና በተፈሪ-ኃይለ ሥላሴ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ይደርሳል። ምኒልክ በ1900 ሚኒስትሮች ሲሾም ከሚኒስቴሮቹ አንዱ «የንግድና የጉምሩክ ሚኒስቴር» ነበር። ሚኒስትሩም «የኢትዮጵያ ጉምሩክና የነጋድራሶች ሁሉ አለቃ» ተብሎ ነበር የተጠቀሰው። ከሚኒስቴሩ ተግባራት አንዱም «የጉምሩክ ሥርዓት ለነጋዴዎች የሚመችና ቀረጥ የሚያበዛ አስተውሎ» ለመንግሥት ማመልከት ነበር። ሚኒስቴሩ በአምስት ክፍሎች ሲከፈል ከነዚህ ውስጥ ሁለቱ ዋና ተግባራቸው የጉምሩክ ሥራ ነበር፤ አንዱ ለአዲስ አበባ፣ ሌላኛው ደግሞ ለተቀረው ያገሪቱ ክፍል። ይህን መሠረት አድርጎ ተፈሪ የደረጀ የጉምሩክ ሥርዓት አቋቋመ። በዚህም ዋና ረዳት የሆኑት የሚሲዮን ትምህርት የቀሰመውና ተፈሪ ከሚከራባቸው ባለሟሎች አንዱ የሆነው ገብረ እግዚአብሔር ፍራንሷና አሜሪካዊው የገንዘብ ጉዳይ አማካሪ ኮልሰን ናቸው። በ1917 የንግድ ሚኒስቴር የጉምሩክ ክፍል የዲሬክተር ጄኔራል መሥሪያ ቤት ሆኖ ተቋቋመ። ከሥሩም አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋና ሰዮ (ደምቢ ደሎ) ባንደኛ ደረጃ ዲሬክተሮች ሲተዳደሩ፤ ሐረር፣ አልዩ አምባና ጨኖ ደግሞ በሁለተኛ ደረጃ ዲሬክተሮች እንዲተዳደሩ ተደረገ። (የደረጃው አመዳደብ ራሱ በ19ኛው መቶ ዓመት ዋና መናኸርያ የነበሩት እነ ሐረርና አልዩ አምባ በ20ኛው መቶ ዓመት ምን ያህል እየተዳከሙ እንደመጡ ይጠቁማል።) ባዲሱ ደንብ መሠረት በዋና ከተማይቱና በየአውራጃው የጉምሩክ መርማሪዎች (ተቆጣጣሪዎች) ተመደቡ።

የተፈሪ የገንዘብ ፖሊሲ ዋና መርህ የጉምሩክን አስተዳደር በማዕከላዊ መንግሥት ሙሉ ቁጥጥር ሥር ማድረግ ነበር። ይህንንም በ1918 አዲሱን የአዲስ አበባን ጉምሩክ ሲከፍት እንዲህ ሲል አብራርቶታል፤

> በማናቸውም ዓለም ላይ ቢሆን የመንግሥት ትልቅ ሕይወቱ ገንዘብ መሆኑን ማንም ሰው ሊያውቀው ይችላል። ሥጋ በነፍሱ ሕያው ሆኖ እንዲኖር መንግሥትም ከችግሩ ሁሉ ሕያው ሆኖ የሚኖረው በገንዘብ ነው። ነገር ግን ማንም ሰው ቢሆን እግዚአብሔር እስከወሰነለት ዘመን ድረስ ሕይወቱ የምትሆን ነፍሱ ከርሱ እንዳትለየውና መዋቲ እንዳይሆን የሚችለውን ያህል ማሰቡና መጣጣሩ አይቀርም። መንግሥትም ተብሎ እስከሚኖርበት ዘመን ድረስ ገንዘቡ ከግምጃ ቤት እንዳያልቅ ለመስጠት እንዳይቸገር የሚቻለውን ያህል ማሰብና ማድረግ ይገባዋል። (ፍሬ ከናፍር፣ 1ኛ መጽሐፍ፣ 15)

በተፈሪና በአንዳንዶቹ መሳፍንት መካከል የነበረው ጠብ ምንጩም ይኸው የጉምሩክ ባለቤትነት ነው። ለዚህም አንድ ጥሩ ምሳሌ በተፈሪና በራስ ጉግሣ ወሌ መካከል የተፈጠረው የግንኙነት መሻከር ነው። የአንችምን ጦርነት ያስከተለው ጠብ አንዱ መነሾ የመተማ ጉምሩክ ለማን ይገባል የሚል ጥያቄ ነበር። የማዕከላዊ የጉምሩክ አስተዳደር ፖሊሲ አንዱ ገጽታ እንደ አሸን የፈሉትን መቅረጫ ኬላዎች አስወግዶ በምትካቸው ጥቂት በውል የታወቁና ማዕከላዊው መንግሥት የሚያዝባቸው የጉምሩክ ጣቢያዎች ማቋቋም ነበር። ለምሳሌ በ1924 ራስ ኃይሉ ከጐጃም ገዥነት ተሽሮ በምትኩ ራስ እምሩ ኃይለ ሥላሴ ሲሾም ካደረጋቸው ለውጦች አንዱ እኒህኑ ለነጋዴው እንደመቅሠፍት የነበሩትን ኬላዎች ማስወገድ ነው።

ማዕከላዊው መንግሥት በጉምሩክ አሰባሰብ ጥያቄ የሚታገለው ከመሳፍንት ብቻ ሳይሆን ከባዕድ መንግሥታት ጋር ጭምርም ነበር። በ1920ዎቹ መጀመሪያ ላይ የጋምቤላ ጉምሩክ ጉዳይ የኢትዮጵያንና የሱዳንን መንግሥት ያጨቃጭቅ ጀመር። በመጨረሻ በተደረሰበት ስምምነት የኢትዮጵያ መንግሥት በፊት ያገኘው ከነበረው የቀረጥ ገቢ ከፍ ያለ ለማግኘት በቃ። መንግሥት በፊት ያገኘው ከነበረው የቀረጥ ገቢ ከፍ ያለ ለማግኘት በቃ። ቀደም ብለን እንዳየነው አትዮጵያ በክለቡኩውስኪ ውል በመታሰሯ ወደ አገር ከሚገቡ ሸቀጦች ማግኘት የምትችለው ቀረጥ ውሱን ነበር። መጠኑም ከሸቀጡ ዋጋ 10 ከመቶ እንዳይበልጥ ሲደነገግ እንዲያውም ይባስ ብሎ ደግሞ የአልኮል መጠጥ ቀረጥ ወደ 8 ከመቶ ዝቅ ብሎ ነበር። ከዚያም በላይ ደግሞ ውሉ የፈረንሳይን ዜጎች ከኢትዮጵያ ሕግ ክልል ውጪ ሲያደርጋቸው ኋላ ሌሎች መንግሥታትም ባገኙት ተመሳሳይ ውል ምክንያት ፈረንጅ የተባለ ሁሉ በኢትዮጵያ ሕግ የማይዳኝ፤ እንደልቡ የሚፈልል ሊሆን በቃ። በክሉብኩውስኪ ውል አማካይነት ኢትዮጵያ ባንድ በኩል ፈረንጆች የሚዘባነኑባት፤ በሌላ በኩል ደግሞ ሸቀጣቸውን ያለገደብ የሚያራግፉባት አገር ሆነች።

ስለዚህ ይህን ውል የማሰረዙን ጉዳይ ተፈሪ (ኋላም ኃይለ ሥላሴ) ተቀዳሚ ተግባሩ አድርጎ ያዘው። በ1916 የአውሮጳን አገሮች እየዞረ በጎበኘበት ሰዓት ጉዳዩን ለፈረንሳይ መንግሥት አንሥቶ ነበር። ይሁን እንጂ ምንም ዓይነት አዎንታዊ ምላሽ ባለማግኘቱ በመጨረሻ በ1923 በገዛ ሥልጣኑ ውሉን ሽሮ የኤክሳይዝ ቀረጥ ዐዋጅ ዐወጀ። በዚህም ዐዋጅ መሠረት እንደ ቅንጦት ዕቃ በተቆጠሩት ባንዳንድ ሸቀጦች ላይ (የአልኮል መጠጥ፤ ሲጃራ፤ ዣንጥላ፤ ምንጣፍ፤ የውስጥ ልብስ) ቀረጡ እስከ 30 በመቶ ከፍ እንዲል ተደረገ። የአውሮጳ ሌጋሲዮኖች ቢነጫነጩም፣ መንግሥት የፈለግኩትን ቀረጥ መደንገግ የነፃ መንግሥትነት መብቴ ነው ብሎ አሻፈረኝ አለ። የሸቀጦች ዋጋ ከፍ ማለት አትዮጵያዊውን ሸማች ቢጎዳውም አዲሱ ቀረጥ ከባዕዳን ቁጥጥር ነፃ ለመሆን የተደረገ ያንድ ነፃ መንግሥት እርምጃ ነበር። በመንግሥት ገቢ ላይም ጉልህ የሆነ ለውጥ ለማምጣት ችሏል። ከጠቅላላው የመንግሥት ገቢ ከሆነው ከ400000 ፓውንድ ውስጥ አዲሱ ቀረጥ 25000 ፓውንድ (ወይም 6 ከመቶ) ያህሉን አስተዋፅኦ አድርጓል። (Perham, 194)

## የሞኖፖል ውሎች (ኮንሴሽን)

ከንግድ ቀጥሎ አውሮጳውያን በድኅረ ዐድዋ ዘመን ወደ ኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ሥርገው ለመግባት የቻሉት በሞኖፖል ውሎች አማካይነት ነው። በነሱ ግምት



እንዲህ ዓይነት ውሎች ኢጣልያ ዐድዋ ላይ ስትሸነፍ የተነፈገችውን የሀገሪቱን የዳበሩ የተፈጥሮ ሀብቶች ለጥቅማቸው የማዋል ዓላማ ተግባራዊ ለማድረግ ሁነኛ መሣሪያ ሆነው ታዩ። እንዲያውም የቅኝ ግዛት አስተዳደር ዘርግቶ ኪሣራ ከመግባት አበሻ ራሱን እያስተዳደረ እኛ ሀብቱን እንበጠብጣለን የሚል ስሌት መስፈን ጀመረ። አንዱ የአውሮጳ ኢምፔሪያሊዝም አፈ ቀላጤ አሳምሮ እንዳስቀመጠው:- «የአቢሲኒያ (ኢትዮጵያ) ታላቅ የተፈጥሮ ሀብቶች ለአውሮጳ ንግድና እንዱስትሪ ክፍት ይሆኑ ዘንድ ጦር መምዘዝ አያስፈልግም፤ የቅኝ አስተዳደር እመሠርታለሁ ብሎ ኪሳራ መግባትም አያሻም።» (Bahru, "Fumbling Debut", 331) የኢትዮጵያ ሁኔታ ብቻ ሳይሆን የአውሮጳ ኢምፔሪያሊዝም የደረሰበት የእድገት ደረጃም ለዚሁ ለሞኖፖል ውል መስፋፋት የሚያመች ነበር። «ሞኖፖሊ ካፒታሊስት» ተብሎ በታወቀው የታሪክ ምዕራፍ የአውሮጳውያን ዓይነተኛ ዓላማ ካፒታል ከአውሮጳ ወደ አፍሪቃና ወደ ሌሎች ተመሳሳይ አህጉሮች እየላኩ ትርፍ ማካበት ነው።

ይሁን እንጂ አውሮጳውያን ኢትዮጵያን በተመለከተ በንግዱ ረድፍ እንደተሳቀቁት ሁሉ፣ ሀገሪቱ ለባለ ካፒታሎች ወርቅ የሚታፈስባት ምድረ ገነት ትሆናለች የሚለው ትንቢት ቀቢጸ ተስፋ ሆኖ ቀረ። የኢትዮጵያ ባለሥልጣኖች አያሌ የሞኖፖል ውሎች ቢፈራረሙም ለቁም ነገር የበቁት እጅግ ጥቂቶች ናቸው። አንዳንዶም ተቦጥቧጮቹ ኢትዮጵያውያን ሳይሆኑ ፈረንጆች ነበሩ ማለት ይቻላል። ውሉን ለማግኘትና ይዞም ለመቆየት ሀብታቸውን ሲከሰክሱ ኢትዮጵያውያን ባለሥልጣኖች ገንዘባቸውን ኪሳቸው አድርገው ውሉን ለማስፈጸም ግን እምብዛም አይቸገሩም ነበር። በዚህ ሁኔታ ነው «የሞኖፖል ውል አዳኞች» (concession hunters) የተባሉት ሙሌዎች የተከሠቱት። በአውሮጳ ካፒታሊስቶችና በኢትዮጵያ ባለሥልጣኖች መሐል ሆነው የሁለቱንም ቋንቋ እየተናገሩ ባንድ በኩል አገናኝ ድልድይ ሲሆኑ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ሁለቱንም እያምታቱ መጠነኛ ሀብት ያካበቱ ቀቶች ነበሩ። በዚህ ረገድ በግንባር ቀደምነት ሊጠቀሱ የሚችሉትም ጀርመናዊው አርኖልድ ሆልትስ፤ ኢጣሊያዊው አልቤርቶ ፕራሰና ሶርያዊው ይድልቢ ናቸው።

አብዛኞዎቹ የሞኖፖል ውሎች የሚፈራረሙበትን ወረቀት ዋጋ እንኳ ሳያስመልሱ ሲቀሩ ሁለቱ ግን በኢትዮጵያ ሕይወት ውስጥ የጎላ ስፍራ ለመያዝ በቁ። እነሱም በ1886 የተፈረመው የባቡር መሥመር ውልና በ1897 የተፈረመው የባንክ ውል ናቸው። በኢትዮጵያ በኩል የሁለቱም ውል ሰጭ ምኒልክ ሲሆን ተቀባዮቹ ደግሞ አፍሪቃን የተቃረጡት ሁለቱ ኃያላን ፈረንሳይና እንግሊዝ ነበሩ፤ ፈረንሳይ ባቡሩን እንግሊዝ ባንኩን አገኙ። የባቡሩ ውል እንደተፈረመ የዐድዋ ጦርነት በመከሰቱ ከጅቡቲ እስከ ነጭ ዐባይ ይዘልቃል ተብሎ የታቀደው የባቡር መስመር ሥራው የተጀመረው ውሉ በተፈረመ በሦስት ዓመቱ በ1890 ነው። በ1895 መጀመሪያ የታለመለትን የሐረር ከተማ በከፍታው ምክንያት ወደ ጐን በመተው አዲሱ ጣቢያ ደረሰ። እንደማካካስ ይመስላል ይህ ጣቢያ መጀመሪያ አዲስ ሐረር ተብሎ ነበር፤ ኋላ ግን ድሬዳዋ በሚል ስያሜ ታወቀ።




3.7 የድሬደዋ ባቡር ጣቢያ

የባቡሩ መሥመር ድሬዳዋ ከደረሰ በኋላ የመሥመሩን ይዞታ በተመለከተ በተፈጠረው ውዝግብ ምክንያት ሥራው ለስድስት ዓመት ተቋረጠ:: የውዝግቡ መነሻ የእንግሊዝ ካፒታል ወደ ባቡሩ ኩባንያ ሠርጎ በመግባቱ ምክንያት የፈረንሳይ መንግሥት ተደናግጦ የወሰደው እርምጃ ነው:: የፈረንሳይ መንግሥት ጠቀም ያለ የገንዘብ እርዳታ ለኩባንያው በመስጠት በዚያውም ለግል ኩባንያ ሰጥቶ የነበረውን መብት መንግሥታዊ መልክ ስላስያዘው ምኒልክ እርምጃው መጀመሪያ የተሰጠውን ውል ይፃረራል ብሉ ተቃወመ:: ከዚያ በኋላ ባንድ ወገን በሦስቱ ቅኝ ገዥዎች (ማለትም እንግሊዝ፣ ፈረንሳይና እጣልያ) መካከል፣ በሌላ ወገን ደግሞ በፈረንሳይና በምኒልክ መካከል ድርድሩ ቀጥሎ ነገሩ እልባት ለማግኘት ቻለ:: የባቡሩ መሥመር ዓለም አቀፋዊ ተቋምነት በ1899 የሦስቱ ኃያላን ስምምነት ሲደነገግ፣ በ1900 ደግሞ ምኒልክ ከፈረንሳይ ጋር ለኢትዮጵያ ከፊተኛው የተሻለ መብት የሚሰጥ አዲስ ውል ተፈራረመ:: የባቡር ሐዲድ ሥራውም ቀጥሎ በ1909 አዲስ አበባ ለመድረስ ቻለ:: ወደ ነጭ ዐባይ የማዝለቁ ጉዳይ እንደሁ ሱዳንን የሚቆጣጠሩት እንግሊዞች ባነሡት ተቃውሞ ምክንያት ወደ ጎን ቀርቷል::

የባቡሩ መሥመር ሥራ መጠናቀቅ በኢትዮጵያ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ሕይወት ላይ ከፍተኛ እንደምታ ነበረው:: ባንድ ወገን የአዲስ አበባ ማዕከላዊነት





3.8 የአበሻ ባንክ፣ አዲስ አበባ

ሲረጋገጥ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ድሬዳዋ፣ ናዝሬትና ሞጆን የመሳሰሉ አዳዲስ ከተሞች መሥመሩን ተከትለው ለመመሥረት በቁ:: ኢትዮጵያን ከዓለም ኢኮኖሚ ጋር ያስተሳሰራት ዋነኛው መንገድ ይኸው የባቡር መሥመር ነው:: ምንም እንኳን ዋጋው አለቅጥ ከፍ እያለ ቢያስቸግርም መንገደኛም ሆነ ሸቀጥ ከኢትዮጵያ የሚሄደው ወይ ወደ ኢትዮጵያ የሚመጣበት ዋና መንገድ ይኸው ባቡሩ ሆነ:: የአዳዲስ ሐሳቦችና ፋሽኖች መሸጋገሪያውም እሱው ነበር:: በፖለቲካ የኃይል ሚዛን ረገድም ራስ ተፈሪ በሥልጣን ልቆ ለመውጣት የቻለበት አንዱ ምክንያት ዋና ከተማይቱን ከሥልጣን መቆናጠጫው ከሐረር ጋር በሚያገናኘው የባቡር መሥመር አማካይነት ወታደር በፍጥነት ለማጓጓዝ በመቻሉ ነው::

የባንኩ ውል የተሰጠው በመጋቢት 1897 በእንግሊዞች ቁጥጥር ሥር ለነበረው ለግብፅ ባንክ (ባንክ ኦፍ ኢጅብት) ነው:: በውሉም መሠረት ባንኩ በኢትዮጵያ ብቸኛ ባንክ ሆኖ ሲታወቅ የብር ኖቶችና ሳንቲሞችን ማተምና ማውጣት የሚችለውም እሱው ብቻ ነበር:: በኢትዮጵያ የተቋቋመው የግብፁ ቅርንጫፍ ባንክ ኦፍ አቢሲኒያ (የሀበሻ ባንክ) ተብሎ ሲታወቅ መነሻ ካፒታሉም 100000 ፓውንድ ነበር:: በባቡሩ መስመር የተነሣውን ውዝግብ ለማስወገድ ተብሎም የባንኩን ይዞት ዓለም አቀፋዊ መልክ ለማስያዝ የተለየ ጥረት ተደርጎ ነበር:: የመሥራች ኮሚቴው አባላት ሦስቱ እንግሊዛዊ፣ ሦስቱ ኢጣሊያዊና አንዱ ደግሞ ጀርመናዊ ሲሆኑ፣ አክስዮኖቹም አዲስ አበባ፣ ካይሮ፣ ኒውዮርክና




3.7 የድሬደዋ ባቡር ጣቢያ

የባቡሩ መሥመር ድሬዳዋ ከደረሰ በኋላ የመሥመሩን ይዞታ በተመለከተ በተፈጠረው ውዝግብ ምክንያት ሥራው ለስድስት ዓመት ተቋረጠ:: የውዝግቡ መነሻ የእንግሊዝ ካፒታል ወደ ባቡሩ ኩባንያ ሠርጎ በመግባቱ ምክንያት የፈረንሳይ መንግሥት ተደናግጦ የወሰደው እርምጃ ነው:: የፈረንሳይ መንግሥት ጠቀም ያለ የገንዘብ እርዳታ ለኩባንያው በመስጠት በዚያውም ለግል ኩባንያ ሰጥቶ የነበረውን መብት መንግሥታዊ መልክ ስላስያዘው ምኒልክ እርምጃው መጀመሪያ የተሰጠውን ውል ይፃረራል ብሎ ተቃወመ:: ከዚያ በኋላ ባንድ ወገን በሦስቱ ቅኝ ገዥዎች (ማለትም እንግሊዝ፣ ፈረንሳይና አጣልያ) መካከል፣ በሌላ ወገን ደግሞ በፈረንሳይና በምኒልክ መካከል ድርድሩ ቀጥሎ ነገሩ እልባት ለማግኘት ቻለ:: የባቡሩ መሥመር ዓለም አቀፋዊ ተቋምነት በ1899 የሦስቱ ኃያላን ስምምነት ሲደነገግ፣ በ1900 ደግሞ ምኒልክ ከፈረንሳይ ጋር ለኢትዮጵያ ከፊተኛው የተሻለ መብት የሚሰጥ አዲስ ውል ተፈራረመ:: የባቡር ሐዲድ ሥራውም ቀጥሎ በ1909 አዲስ አበባ ለመድረስ ቻለ:: ወደ ነጭ ዐባይ የማዝለቁ ጉዳይ እንደሁ ሱዳንን የሚቆጣጠሩት እንግሊዞች ባነሡት ተቃውሞ ምክንያት ወደ ጎን ቀርቷል::

የባቡሩ መሥመር ሥራ መጠናቀቅ በኢትዮጵያ ኤኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ሕይወት ላይ ከፍተኛ እንደምታ ነበረው:: ባንድ ወገን የአዲስ አበባ ማዕከላዊነት





3.8 የአበሻ ባንክ፣ አዲስ አበባ

ሲረጋገጥ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ድሬዳዋ፣ ናዝሬትና ሞጆን የመሳሰሉ አዳዲስ ከተሞች መሥመሩን ተከትለው ለመመሥረት በቁ:: ኢትዮጵያን ከዓለም ኤኮኖሚ ጋር ያስተሳሰራት ዋነኛው መንገድ ይኸው የባቡር መሥመር ነው:: ምንም እንኳን ዋጋው አለቅጥ ከፍ እያለ ቢያስቸግርም መንገደኛም ሆነ ሸቀጥ ከኢትዮጵያ የሚሄደው ወይ ወደ ኢትዮጵያ የሚመጣበት ዋና መንገድ ይኸው ባቡሩ ሆነ:: የአዳዲስ ሐሳቦችና ፋሽኖች መስረጊያውም እሱው ነበር:: በፖለቲካ የኃይል ሚዛን ረገድም ራስ ተፈሪ በሥልጣን ልቆ ለመውጣት የቻለበት አንዱ ምክንያት ዋና ከተማይቱን ከሥልጣን መቆናጠጫው ከሐረር ጋር በሚያገናኘው የባቡር መሥመር አማካይነት ወታደር በፍጥነት ለማጓጓዝ በመቻሉ ነው::

የባንኩ ውል የተሰጠው በመጋቢት 1897 በእንግሊዞች ቁጥጥር ሥር ለነበረው ለግብፅ ባንክ (ባንክ ኦፍ ኢጅብት) ነው:: በውሉም መሠረት ባንኩ በኢትዮጵያ ብቸኛ ባንክ ሆኖ ሲታወቅ የብር ኖቶችና ሳንቲሞችን ማተምና ማውጣት የሚችለውም እሱው ብቻ ነበር:: በኢትዮጵያ የተቋቋመው የግብፁ ቅርንጫፍ ባንክ ኦፍ አቢሲኒያ (የሀበሻ ባንክ) ተብሎ ሲታወቅ መነሻ ካፒታሉም 100000 ፓውንድ ነበር:: በባቡሩ መስመር የተነሣውን ውዝግብ ለማስወገድ ተብሎም የባንኩን ይዞታ ዓለም አቀፋዊ መልክ ለማስያዝ የተለየ ጥረት ተደርጎ ነበር:: የመሥራች ኮሚቴው አባላት ሦስቱ እንግሊዛዊ፣ ሦስቱ ኢጣሊያዊና አንዱ ደግሞ ጀርመናዊ ሲሆኑ፣ አክስዮኖቹም አዲስ አበባ፣ ካይሮ፣ ኒውዮርክና

በተለያዩ የአውሮጳ ከተሞች ለሽያጭ እንዲቀርቡ ተደረገ:: በእንግሊዞች እጅ የነበረው የአክሲዮን ብዛትም ፈረንሳዮችና ጣሊያኖች በጣምራ ከያዙት እንዳይበልጥ ሆኖ ተመጥኖ ነበር:: ይህ ሁሉ ሆኖ ግን ቁልፍ የአስተዳደር ሥፍራዎች የያዙት እንግሊዞች በመሆናቸው ባንኩ በመሠረቱ እንግሊዛዊ መሆኑ ብዙም አያጠራጥር ነበር::

የባንኩ ቅርንጫፎች በተለያዩ የሀገሪቱ ከተሞች ቢከፈቱም ባንኩ በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ውስጥ የነበረው ሚና እምብዛም የጎላ አልነበረም:: ለብድር የሚጠየቀው የ15 በመቶ ወለድ ብዙም የሚያደፋፍር አልነበረም:: ለዐሥር ዓመት ያህል ባንኩ ያለ ትርፍ ነበር የሚንገታገተው:: በመሠረቱ የባንኩ ችግር የማንኛውም በፊውዳል ኅብረተ ሰብ ላይ የተለጠፈ የካፒታሊስት ድርጅት ችግር ነው:: ቀደም ብሎ ሥር የሰደደውን የግል አበዳሪዎች መዋቅር መቋቋሙም ቀላል አልነበረም:: ገንዘብ ያላቸው ብዙ ሰዎችም ገንዘባቸውን ለባዕድ አካል ሰጥተው ከመሥጋት ትራሳቸው ሥር ወይ ማሰሮ ውስጥ ማድረጉን ይመርጡ ነበር:: በሌላ ወገን ደግሞ ባንኩ የተሰጠው የሞኖፖል ውል ተቃውሞ ማስነሣቱ አልቀረም:: ውሉን አጥብቀው ከሚቃወሙት አንዱ የዘመኑ ቁንጮ ምሁር የሆነው ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ ነበር:: እቴጌ ጣይቱም በ1901 የእርሻና የንግድ ማስፋፊያ ማኅበር የሚባል አበዳሪ ድርጅት በማቋቋም የባንኩን ሞኖፖል ለመቃወም ሞክራለች:: በመጨረሻም በ1923 ባንኩን የኢትዮጵያ መንግሥት ገዝቶ ብሔራዊ ሀብት አድርጎታል:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮም የኢትዮጵያ ባንክ (ባንክ ኦፍ ኢትዮጵያ) በመባል ታወቀ:: ይህም ከነፃነት ወዲህ የተቋቋመው የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ (እስቴት ባንክ ኦፍ ኢትዮጵያ) አባትና በ1955 የተቋቋመው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ (ኮሜርሻል ባንክ ኦፍ ኢትዮጵያ) አያት መሆኑ ነው::

## ዘመናዊ ትምህርትና የለውጥ ፈላጊ ምሁራን መብቀል

የዘመናዊ ትምህርት ፍላጎት እያደገ መምጣት የጀመረው በ19ኛው መቶ ዓመት ነው:: ትምህርት የምእመናን ማፍሪያ ዓይነተኛ መሣሪያ ነው ብለው የገመቱት ሚሲዮናውያን ትምህርት ቤቶች በመክፈትም ሆነ ኅበዝ ኅበዞቹን ተማሪዎች ወደ ውጭ አገር ለትምህርት በመላክ በዚህ ረገድ ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል:: በምዕራፍ ሁለት እንደተገለጸውም ቴዎድሮስ በአውሮጳ ቴክኖሎጂ፣በተለይም በዚያ ቴክኖሎጂ ወታደራዊ ጥቅም ተማርኮ ወጣት ኢትዮጵያውያን በእጅ ሙያ የሚሠለጥኑበት ትምህርት ቤት ጋፋት ላይ አቋቁሞ ነበር:: ከዐድዋ በኋላ ኢትዮጵያ ከአውሮጳና ከአውሮጳውያን ጋር ያላት ግንኙነት እየተጠናከረ ሲሄድ ዘመናዊ ትምህርት ለማስፋፋት አመቺ ሁኔታዎች ተፈጠሩ::

የመንግሥት አውታሮች፣ በተለይም የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች፣ ከተቋቋሙና የጉምሩክ አስተዳደር ከተመሠረተ በኋላ እየተስፋፉ ሲሄዱ እነዚህን አውታሮች የሚያንቀሳቅሱ ባለሙያዎች ማሠልጠኑ አማራጭ የማይገኝለት ጉዳይ ሆነ:: ይህ ስለተባለ ግን የተማሩት ኢትዮጵያውያን መጨረሻቸው ጸሐፊነትና የሒሳብ ሠራተኛነት ብቻ ነበር ማለት አይደለም:: አንዳንዶቹ ያገራቸውን ኋላ ቀርነት በስላ ብዕራቸው በመግለጽና ለውጥም ለማምጣት በመድከም የጎላ አስተዋፅኦ አድርገዋል:: ድርጅታዊ ጥንካሬን ባይታደሉም ላገር





3.9 በ1903 ወደ አውሮጳ የሄደው የልዑካን ቡድን

ያላቸው ስሜትና መቆርቆር ጥልቅ ነበር:: ፈረንጆች በቱርክና በሌሎችም አገሮች ቀደም ብለው በቅለው የነበሩትን የለውጥ ሃዋርያት በማስታወስ እነዚህን ምሁራን «ወጣት ኢትዮጵያውያን» የሚል ስያሜ አውጥተውላቸው ነበር:: በ1950ዎቹና በ1960ዎቹ ዓመታት በኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ የተንቦገቦገው የለውጥ ችቦ መጀመርያ የተቀጣጠለው በነዚህ የቀድሞ ምሁራን ነው::

ቀደም ብለን እንደጠቀስነው የመጀመሪያዎቹ ምሁራን ባብዛኛው የትምህርት እድል የተከፈተላቸው በሚስዮናውያን አማካይነት ነው:: ከነዚህም ውስጥ ጎላ ብለው የሚታዩት የፈላሻዎች (ወይም ባሁን አጠራራቸው ቤተ እሥራኤሎች) እና የሚሲዮናውያን የቅርብ መተባበር ተጠቃሚ ከሆኑት አንዱ ፕሮፌሰር ታምራት አማኑኤል፣ ከአፄ ዮሐንስ ጀምሮ እስከ ጣልያን ወረራ ድረስ በአስተርጓሚነት፣ በመንግሥት ልዑክነት፣ በከንቲባነት፣ በሴኔተርነትና፣ በአርበኝነት አገሩን ያገለገለው ከንቲባ ገብሩና መጽሐፍ ቅዱስን ወደ ኦሮምኛ

በተለያዩ የአውሮጳ ከተሞች ለሽያጭ እንዲቀርቡ ተደረገ:: በእንግሊዞች እጅ የነበረው የአክሲዮን ብዛትም ፈረንሳዮችና ጣሊያኖች በጣምራ ከያዙት እንዳይበልጥ ሆኖ ተመጥኖ ነበር:: ይህ ሁሉ ሆኖ ግን ቁልፍ የአስተዳደር ሥፍራዎች የያዙት እንግሊዞች በመሆናቸው ባንኩ በመሠረቱ እንግሊዛዊ መሆኑ ብዙም አያጠራጥር ነበር::

የባንኩ ቅርንጫፎች በተለያዩ የሀገሪቱ ከተሞች ቢከፈቱም ባንኩ በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ውስጥ የነበረው ሚና እምብዛም የጎላ አልነበረም:: ለብድር የሚጠየቀው የ15 በመቶ ወለድ ብዙም የሚያደፋፍር አልነበረም:: ለዐሥር ዓመት ያህል ባንኩ ያለ ትርፍ ነበር የሚንገታገተው:: በመሠረቱ የባንኩ ችግር የማንኛውም በፊውዳል ኅብረተ ሰብ ላይ የተለጠፈ የካፒታሊስት ድርጅት ችግር ነው:: ቀደም ብሎ ሥር የሰደደውን የግል አበዳሪዎች መዋቅር መቋቋሙም ቀላል አልነበረም:: ገንዘብ ያላቸው ብዙ ሰዎችም ገንዘባቸውን ለባዕድ አካል ሰጥተው ከመሥጋት ትራሳቸው ሥር ወይ ማሰሮ ውስጥ ማድረጉን ይመርጡ ነበር:: በሌላ ወገን ደግሞ ባንኩ የተሰጠው የሞኖፖል ውል ተቃውሞ ማስነሣቱ አልቀረም:: ውሉን አጥብቀው ከሚቃወሙት አንዱ የዘመኑ ቁንጮ ምሁር የሆነው ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ ነበር:: እቴጌ ጣይቱም በ1901 የእርሻና የንግድ ማስፋፊያ ማኅበር የሚባል አበዳሪ ድርጅት በማቋቋም የባንኩን ሞኖፖል ለመቃወም ሞክራለች:: በመጨረሻም በ1923 ባንኩን የኢትዮጵያ መንግሥት ገዝቶ ብሔራዊ ሀብት አድርጎታል:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮም የኢትዮጵያ ባንክ (ባንክ ኦፍ ኢትዮጵያ) በመባል ታወቀ:: ይህም ከነፃነት ወዲህ የተቋቋመው የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ (እስቴት ባንክ ኦፍ ኢትዮጵያ) አባትና በ1955 የተቋቋመው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ (ኮሜርሻል ባንክ ኦፍ ኢትዮጵያ) አያት መሆኑ ነው::

## ዘመናዊ ትምህርትና የለውጥ ፈላጊ ምሁራን መብቀል

የዘመናዊ ትምህርት ፍላጎት እያደገ መምጣት የጀመረው በ19ኛው መቶ ዓመት ነው:: ትምህርት የምእመናን ማፍሪያ ዓይነተኛ መሣሪያ ነው ብለው የገመቱት ሚሲዮናውያን ትምህርት ቤቶች በመክፈትም ሆነ ጎበዝ ጎበዞቹን ተማሪዎች ወደ ውጭ አገር ለትምህርት በመላክ በዚህ ረገድ ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል:: በምዕራፍ ሁለት እንደተገለጸውም ቴዎድሮስ በአውሮጳ ቴክኖሎጂ፣በተለይም በዚያ ቴክኖሎጂ ወታደራዊ ጥቅም ተማርኮ ወጣት ኢትዮጵያውያን በእጅ ሙያ የሚሠለጥኑበት ትምህርት ቤት ጋፋት ላይ አቋቁሞ ነበር:: ከዐድዋ በኋላ ኢትዮጵያ ከአውሮጳና ከአውሮጳውያን ጋር ያላት ግንኙነት እየተጠናከረ ሲሄድ ዘመናዊ ትምህርት ለማስፋፋት አመቺ ሁኔታዎች ተፈጠሩ::

የመንግሥት አውታሮች፣ በተለይም የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች፣ ከተቋቋሙና የጉምሩክ አስተዳደር ከተመሠረተ በኋላ እየተስፋፋ ሲሄዱ እነዚህን አውታሮች የሚያንቀሳቅሱ ባለሙያዎች ማሠልጠኑ አማራጭ የማይገኝለት ጉዳይ ሆነ:: ይህ ስለተባለ ግን የተማሩት ኢትዮጵያውያን መጨረሻቸው ጸሐፊነትና የሒሳብ ሠራተኛነት ብቻ ነበር ማለት አይደለም:: አንዳንዶቹ ያገራቸውን ኋላ ቀርነት በሰላ ብዕራቸው በመግለጽና ለውጥም ለማምጣት በመድከም የጎላ አስተዋፅኦ አድርገዋል:: ድርጅታዊ ጥንካሬን ባይታደሉም ሳገር





3.9 በ1903 ወደ አውሮጳ የሄደው የልዑካን ቡድን

ያላቸው ስሜትና መቆርቆር ጥልቅ ነበር:: ፈረንጆች በቱርክና በሌሎችም አገሮች ቀደም ብለው በቅለው የነበሩትን የለውጥ ሃዋርያት በማስታወስ እነዚህን ምሁራን «ወጣት ኢትዮጵያውያን» የሚል ስያሜ አውጥተውላቸው ነበር:: በ1950ዎቹና በ1960ዎቹ ዓመታት በኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ የተንቦገቦገው የለውጥ ችቦ መጀመርያ የተቀጣጠለው በነዚህ የቀድሞ ምሁራን ነው::

ቀደም ብለን እንደጠቀስነው የመጀመሪያዎቹ ምሁራን ባብዛኛው የትምህርት እድል የተከፈተላቸው በሚስዮናውያን አማካይነት ነው:: ከነዚህም ውስጥ ጎላ ብለው የሚታዩት የፈላሻዎች (ወይም ባሁን አጠራራቸው ቤተ እሥራኤሎች) እና የሚሲዮናውያን የቅርብ መተሳሰር ተጠቃሚ ከሆኑት አንዱ ፕሮፌሰር ታምራት አማኑኤል፣ ከአፄ ዮሐንስ ጀምሮ እስከ ጣልያን ወረራ ድረስ በአስተርጓሚነት፣ በመንግሥት ልዑክነት፣ በከንቲባነት፣ በሴኔተርነትና፣ በአርበኝነት አገሩን ያገለገለው ከንቲባ ገብሩና መጽሐፍ ቅዱስን ወደ ኦሮምኛ



3.10 ሐኪም ወርቅነህ እሸቴ (ዶ/ር ቻርልስ ማርቲን)

ቋንቋ የተረጎመው የኢሉባቦር ተወላጅ ኦኒሲሞስ ነሲብ ይገኙበታል። ሌሎቹ ደግሞ ዘመናዊ ትምህርት የቀሰሙት ከዚህ ለየት ባለ መንገድ ነው። ለምሳሌ የእጌ ቴዎድሮስና የእጌ ዮሐንስ አስተርጓሚ የነበረው ማህደረ ቃል የተማረው በፈረንሳይ መንግሥት እርዳታ ነው። በተለይም ተአምራዊ በሆነ መንገድ ለከፍተኛ ማዕረግ የበቃው የሐኪም ወርቅነህ እሸቴ (ወይም በፈረንጅኛ ስሙ ዶክተር ቻርልስ ማርቲን) የሕይወት ታሪክ ራሱን የቻለ ገድል ነው። በመቅደላ ጦርነት ጊዜ አራት ዓመት ያልሞላው ወርቅነህ እናትና አባቱ ጠፍተውበት ሲባዝን የእንግሊዝ ወታደሮች አግኝተውት ይዘውት ወደ አገራቸው ተመለሱ። በሕንድና በስኮትላንድ የሕክምና ትምህርት ካጠና በኋላ ወደ አገሩ ተመልሶ የረጅም ዘመን አገልግሎት ሰጥቷል። ከነዚህም ዋና ዋናዎቹ የተፈሪ መኮንን ት/ቤት አስተዳዳሪነት፣ ነፃ የወጡ ባሮች ልጆች ት/ቤት ዲሬክተርነት፣ ጣና ሐይቅ ላይ ግድብ ለመሥራት ከአሜሪካ ኩባንያ ጋር ተደራዳሪነት፣ የጨርጨር ገዥነትና በኢጣልያ ወረራ ዋዜማ በለንደን የኢትዮጵያ ሚኒስትርነት (አምባሳደርነት) ናቸው።

ውጭ አገር የሄዱ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ዲግሪ ይዘው ይመለሱ ነበር ማለት አይደለም። እንዲያውም ብዙውን ጊዜ መደበኛ ትምህርት በመከታተል ሳይሆን ውጭ አገር በመኖር ብቻ ነው ተለውጠው ይመጡ የነበሩት። አንድ ሁለቱ ደግሞ ውጭ አገር ዝናን ያተረፉት በተማሪነት ሳይሆን በመምህርነት ነው። አለቃ ታየ ገብረ ማርያምንና ነጋድራስ አፈወርቅ ገብረ ኢየሱስን ለአብነት መጥቀስ ይቻላል። አለቃ ታየ ትምህርቱን የጀመረው ምፅዋ አጠገብ በሚገኘው በምንኩሉ ወንጌላዊ ሚሲዮን ሲሆን፣ በ1897 ወደ ኢትዮጵያ የመጣውን ከፍተኛ የጀርመን ልዑካን ቡድን አጅቦ ወደ በርሊን በመሄድ እዚያ የግዕዝ አስተማሪ ሆኖ ቆይቷል። አፈወርቅም እንዲሁ በረጅም ዘመን የኢጣልያ አገር ቆይታው በፕሮፌሰርነት ማዕረግ የአማርኛ አስተማሪ በነበረበት ወቅት ነው እያሌ መጻሕፍትን መጻፍ የቻለው። ከነዚህም ውስጥ "ልበለድ" ወይም "ጦቢያ" የተባለው የመጀመሪያው የአማርኛ ልብወለድ ታሪክ ይገኝበታል።

ሦስት ኢትዮጵያውያን ደግሞ ሥልጠናቸውን ያገኙት በቅድመ አብዮት ሩስያ ነው። ግዛውና ዳኘ የተባሉት በሕክምና ሙያ ሠልጥነው ከተመለሱ በኋላ የዳግማዊ ምኒልክን ሆስፒታል በማቋቋም ሲረዱ፣ ተክለ ሐዋርያት ተክለ ማርያም ደግሞ በሴይንት ፒተርስበርግ ከተማ የመድፈኝነት ሙያ ተምሮ እስከ ኮሎኔልነት ማዕረግ ደርሶ ወደ ሀገሩ ተመልሷል። ከተመለሰ በኋላ ግን ዝናን ያተረፈው በሠለጠነበት ሙያ ሳይሆን በአገረ ገዥነት፣ በእርሻ ጠቢብነት፣ በ1923ቱ ሕገ መንግሥት አርቃቂነትና በበጅሮንድነት ነው።

ከዘመኑ ምሁራን ሁሉ ልቆ የሚታየው ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ ውጭ ሀገር ሄዶ ዘመናዊ ትምህርት ሊቀስም የቻለው በግል ጥረቱ ነው። ገና በጨቅላነቱ በመርከብ ተደብቆ አውስትሪያ በመሄድ የሕክምና ትምህርት አጥንቶ ወደ ሀገሩ ተመለሰ። ተመልሶ ዓለምን ያስደነቀው ግን በሕክምና ጥበቡ ሳይሆን የፖለቲካ ኢኮኖሚን አበጥሮ በማወቁና በተለይም ከኢትዮጵያ ሁኔታ ጋር ለማዛመድ በመቻሉ ነው። እንግሊዞች ያስተዳድሯት በነበረችው በሱዳንም የአጭር ጊዜ ቆይታ አድርጎ ነፃይቱ ኢትዮጵያ ምን ያህል ቅኝ ግዛት ከሆነችው ሱዳን ወደ ኋላ እንደቀረች በመገንዘቡ ከፉኛ ታውኮ መጥቷል። ቁጭቱንና የእድገት ሐሳቦቹንም "አጤ ምኒልክና ኢትዮጵያ" እና "መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር" በተሰኙት ሁለት መጻሕፍቱ (የመጀመሪያው እ.ኤ.አ. በ1912፣ የኋለኛው በ1916 የታተመ) ዘርዝሮ ጽፎታል። ገና በሠላሳ ሦስት ዓመቱ የተቀጨው ገብረ ሕይወት የያዘው ከፍተኛ የመንግሥት ሥልጣን የሐረር ነጋድራስነት ነበር።

በራሳቸው ጥረት ተምረው ሀገርን የማሻሻል ሐሳቦች ያስመታከት ከሚያቀርቡት መካከል የወለጋ መሳፍንት ተወላጅ የሆነውን ፊታውራሪ፣ ኋላ ብላታ፣ ዴሬሳ አመንቴን መጥቀስ ተገቢ ነው። በገብረ ሕይወት ባይከዳኝ የለውጥ ሐሳቦች ከተማረኩት አንዱ የሆነው ዴሬሣ «የምሁራን መድረክ» ተብሎ ሊጠቀስ በሚችለው ሳምንታዊው «ብርሃንና ሰላም» ጋዜጣ ምናልባት ከሁሉም የበለጠ በተከታታይ ጽፏል።

በአካባቢ ካሉት ቅኝ ግዛቶች ሱዳን ብቻ ሳትሆን ኤርትራም በኢትዮጵያ የለውጥ እርምጃ ላይ የተወሰነ ተጽዕኖ ማሳደሯ አልቀረም። ይህም በሁለት የተለያዩ መንገዶች ነው። ባንድ በኩል በተለይ በ1920ቹ ዓመታት እያሌ ኤርትራውያን ለኢትዮጵያ ባላቸው ስሜት እየተሳቡና የተሻለ የሥራ ዕድል ፍለጋ ወደ ኢትዮጵያ እየመጡ የለውጡ ሂደት ተሳታፊና አንዳንዴም መሪ ሆነዋል። በመሪነት ሊጠቀሱ ከሚችሉት ዋነኛው ኤርትራን ወደ ኢትዮጵያ ለማስመለስ



3.10 ሐኪም ወርቅነህ እሸቴ (ዶ/ር ቻርልስ ማርቲን)

ቋንቋ የተረጎመው የኢሉባቦር ተወላጅ ኦኔሲሞስ ነሲብ ይገኙበታል:: ሌሎቹ ደግሞ ዘመናዊ ትምህርት የቀሰሙት ከዚህ ለየት ባለ መንገድ ነው:: ለምሳሌ የአፄ ቴዎድሮስና የአፄ ዮሐንስ አስተርጓሚ የነበረው ማህደረ ቃል የተማረው በፈረንሳይ መንግሥት እርዳታ ነው:: በተለይም ተአምራዊ በሆነ መንገድ ለከፍተኛ ማዕረግ የበቃው የሐኪም ወርቅነህ እሸቴ (ወይም በፈረንጅኛ ስሙ ዶክተር ቻርልስ ማርቲን) የሕይወት ታሪክ ራሱን የቻለ ገድል ነው:: በመቅደላ ጦርነት ጊዜ አራት ዓመት ያልሞላው ወርቅነህ እናትና አባቱ ጠፍተውበት ሲባዝን የእንግሊዝ ወታደሮች አግኝተውት ይዘውት ወደ አገራቸው ተመለሱ:: በሕንድና በስኮትላንድ የሕክምና ትምህርት ካጠና በኋላ ወደ አገሩ ተመልሶ የረጅም ዘመን አገልግሎት ሰጥቷል:: ከነዚህም ዋና ዋናዎቹ የተፈሪ መኰንን ት/ቤት አስተዳዳሪነት፣ ነፃ የወጡ ባሮች ልጆች ት/ቤት ዲሬክተርነት፣ ጣና ሐይቅ ላይ ግድብ ለመሥራት ከአሜሪካ ኩባንያ ጋር ተደራዳሪነት፣ የጨርጨር ገዥነትና በኢጣልያ ወረራ ዋዜማ በለንደን የኢትዮጵያ ሚኒስትርነት (አምባሳደርነት) ናቸው::

ውጭ አገር የሄዱ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ዲግሪ ይዘው ይመለሱ ነበር ማለት አይደለም:: እንዲያውም ብዙውን ጊዜ መደበኛ ትምህርት በመከታተል ሳይሆን ውጭ አገር በመኖር ብቻ ነው ተለውጠው ይመጡ የነበሩት:: አንድ



ሁለቱ ደግሞ ውጭ አገር ዝናን ያተረፉት በተማሪነት ሳይሆን በመምህርነት ነው:: አለቃ ታየ ገብረ ማርያምንና ነጋድራስ አፈወርቅ ገብረ ኢየሱስን ለአብነት መጥቀስ ይቻላል:: አለቃ ታየ ትምህርቱን የጀመረው ምፅዋ አጠገብ በሚገኘው በምንኩሉ ወንጌላዊ ሚሲዮን ሲሆን፣ በ1897 ወደ ኢትዮጵያ የመጣውን ከፍተኛ የጀርመን ልዑካን ቡድን አጅቦ ወደ በርሊን በመሄድ እዚያ የግዕዝ አስተማሪ ሆኖ ቆይቷል:: አፈወርቅም እንዲሁ በረጅም ዘመን የኢጣልያ አገር ቆይታው በፕሮፌሰርነት ማዕረግ የአማርኛ አስተማሪ በነበረበት ወቅት ነው እያሌ መጻሕፍትን መጻፍ የቻለው:: ከነዚህም ውስጥ "ልቦለድ" ወይም "ጦቢያ" የተባለው የመጀመሪያው የአማርኛ ልብወለድ ታሪክ ይገኝበታል::

ሦስት ኢትዮጵያውያን ደግሞ ሥልጠናቸውን ያገኙት በቅድመ አብዮት ሩስያ ነው:: ግዛውና ዳኘ የተባሉት በሕክምና ሙያ ሠልጥነው ከተመለሱ በኋላ የዳግማዊ ምኒልክን ሆስፒታል በማቋቋም ሲረዱ፣ ተክለ ሐዋርያት ተክለ ማርያም ደግሞ በሴይንት ፒተርስበርግ ከተማ የመድፈኝነት ሙያ ተምሮ እስከ ኰሎኔልነት ማዕረግ ደርሶ ወደ ሀገሩ ተመልሷል:: ከተመለሰ በኋላ ግን ዝናን ያተረፈው በሠለጠነበት ሙያ ሳይሆን በአገረ ገዥነት፣ በእርሻ ጠቢብነት፣ በ1923ቱ ሕገ መንግሥት አርቃቂነትና በበጅሮንድነት ነው::

ከዘመኑ ምሁራን ሁሉ ልቆ የሚታየው ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ ውጭ ሀገር ሄዶ ዘመናዊ ትምህርት ሊቀስም የቻለው በግል ጥረቱ ነው:: ገና በጨቅላነቱ በመርከብ ተደብቆ አውስትሪያ በመሄድ የሕክምና ትምህርት አጥንቶ ወደ ሀገሩ ተመለሰ:: ተመልሶ ዓለምን ያስደነቀው ግን በሕክምና ጥበቡ ሳይሆን የፖለቲካ ኢኮኖሚን አበጥሮ በማወቁና በተለይም ከኢትዮጵያ ሁኔታ ጋር ለማዛመድ በመቻሉ ነው:: እንግሊዞች ያስተዳድሯት በነበረችው በሱዳንም የአጭር ጊዜ ቆይታ አድርጎ ነፃይቱ ኢትዮጵያ ምን ያህል ቅኝ ግዛት ከሆነችው ሱዳን ወደ ኋላ እንደቀረች በመገንዘቡ ክፉኛ ታውኮ መጥቷል:: ቁጭቱንና የእድገት ሐሳቦቹንም "አጤ ምኒልክና ኢትዮጵያ" እና "መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር" በተሰኙት ሁለት መጻሕፍቱ (የመጀመሪያው እ.ኤ.አ. በ1912፣ የኋለኛው በ1916 የታተሙ) ዘርዝሮ ጽፎታል:: ገና በሠላሳ ሦስት ዓመቱ የተቀጨው ገብረ ሕይወት የያዘው ከፍተኛ የመንግሥት ሥልጣን የሐረር ነጋድራስነት ነበር::

በራሳቸው ጥረት ተምረው ሀገርን የማሻሻል ሐሳቦች ያስመታከት ከሚያቀርቡት መካከል የወለጋ መሳፍንት ተወላጅ የሆነውን ፊታውራሪ፣ ኋላ ብላታ፣ ዴሬሳ አመንቴን መጥቀስ ተገቢ ነው:: በገብረ ሕይወት ባይከዳኝ የለውጥ ሐሳቦች ከተማረኩት አንዱ የሆነው ዴሬሣ «የምሁራኑ መድረክ» ተብሎ ሊጠቀስ በሚችለው ሳምንታዊው «ብርሃንና ሰላም» ጋዜጣ ምናልባት ከሁሉም የበለጠ በተከታታይ ጽፏል::

በአካባቢ ካሉት ቅኝ ግዛቶች ሱዳን ብቻ ሳትሆን ኤርትራም በኢትዮጵያ የለውጥ አርምጃ ላይ የተወሰነ ተጽዕኖ ማሳደሯ አልቀረም:: ይህም በሁለት የተለያዩ መንገዶች ነው:: ባንድ በኩል በተለይ በ1920ቹ ዓመታት እያሌ ኤርትራውያን ለኢትዮጵያ ባላቸው ስሜት እየተሳቡና የተሻለ የሥራ ዕድል ፍለጋ ወደ ኢትዮጵያ እየመጡ የለውጡ ሂደት ተሳታፊና አንዳንዴም መሪ ሆነዋል:: በመሪነት ሊጠቀሱ ከሚችሉት ዋነኛው ኤርትራን ወደ ኢትዮጵያ ለማስመለስ



3.11 ነጋድራስ ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ፣ የሃያኛው መቶ ዓመት መጀመሪያ ቀንም ምሁር




3.12 ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወ/ሥላሴ፣ ደራሲና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር

እንደታገለ የሞተውና የአማርኛ ቋንቋ ጋዜጣ መሥራች የሆነው ብላታ ገብረ እግዚአብሔር ጊላ ማርያም ይገኙበታል። በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ በኤርትራ የነበረው ሻል ያለ አስተዳደር አንዳንድ የኢትዮጵያ ሹማምንትን ሕሊና ስቦ በኢትዮጵያስ ለምን ተመሳሳይ አስተዳደር አንመሠርትም የሚል ሐሳብ ፈጥሮ ነበር። በዚህም ረገድ ሊጠቀሱ የሚችሉት የዐድዋው ገዥ ደጃች ገብረ ሥላሴ ባርያ ጋብርና በአሥመራ የኢትዮጵያ ቆንስል ሆነው በተከታታይ ያገለገሉት ወንድማማቾች ወሰኔና ነሲቡ ዛማኑኤል ናቸው።

አገር በቀል ከሆኑት ምሁራንና የመንግሥት ሹማምንት መካከል አያሌ መጻሕፍትን በመድረስና በአስተዳደርም ረገድ ለሚኒስትርነት ማዕረግ በመብቃት ከፍተኛ ዝና ያተረፈውን ኅሩይ ወልደ ሥላሴን መጥቀስ ይቻላል። ኅሩይ መደበኛ ትምህርቱ የቤተ ክህነት ሲሆን ከዚያም ፈረንጆችን በመጠጋትና ከነሱም ጋር በመወዳጀት የአውሮጳ ቋንቋዎችን ለመቅሰምና የዕውቀቱንም አድማስ ሰፋ





3.13 ተፈሪ መኰንን ት/ቤት በተቆረቆረበት ዘመን

ለማድረግ ችሏል። እንደሱው ሌሎችም በቤተ ክህነት ትምህርት የታነፁ ምሁራን በዘመኑ የምሁራን እንቅስቃሴና በማቆጥቆጥ ላይ ባለው ዘመናዊ አስተዳደር ውስጥ የማይናቅ ሚና ተጫውተዋል። በተለይም የእንጦጦ ራጉኤል ቤተ ክርስቲያን በዚህ ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አበርክታለች። ዝናና ሥልጣን ካተረፉት የራጉኤል ምሩቃን መካከል ከኅሩይ በተጨማሪ ታከለ ወልደ ሐዋርያትና መኰንን ሀብተ ወልድ ይገኙበታል። ታከለ በጉምሩክ ሹምነት፣ በአዲስ አበባ ከንቲባነት፣ በስመ ጥር አርበኝነት አገሩን ያገለገለ ሲሆን የመጨረሻ የሕይወት ዘመኑን አፄ ኃይለ ሥላሴን ከሥልጣን ለማውረድ ባላሰለሰ ትግል ደምድሞታል። በተቃራኒው መኰንን ሀብተ ወልድ በነመንግሥቱ ንዋይ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ወቅት እስከተገደለበት ጊዜ ድረስ የኃይለ ሥላሴ ታማኝ አገልጋይና የፖለቲካ ሥርዓቱም መከታ ሆኖ ቆይቷል።

የመደበኛ ትምህርት በኢትዮጵያ መስፋፋትን በተመለከተ በምኒልክ ዘመነ መንግሥት ፍጻሜ አካባቢ አንድ ዐቢይ ድርጊት ተከናውኗል። ይህም በንጉሡ ነገሥቱ ስም የሚታወቀው ትምህርት ቤት በ1900 መከፈቱ ነው።



3.11 ነጋድራስ ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ፣ የሃያኛው መቶ ዓመት መጀመሪያ ቁንጮ ምሁር




3.12 ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወ/ሥላሴ፣ ደራሲና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር

እንደታገለ የሞተውና የአማርኛ ቋንቋ ጋዜጣ መሥራች የሆነው ብላታ ገብረ እግዚአብሔር ጊላ ማርያም ይገኝበታል:: በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ በኤርትራ የነበረው ሻል ያለ አስተዳደር አንዳንድ የአትዮጵያ ሹማምንትን ሕሊና ስቦ በኢትዮጵያስ ለምን ተመሳሳይ አስተዳደር አንመሠርትም የሚል ሐሳብ ፈጥሮ ነበር:: በዚህም ረገድ ሊጠቀሱ የሚችሉት የዐድዋው ገኘ ደጃች ገብረ ሥላሴ ባርያ ጋብርና በአሥመራ የኢትዮጵያ ቆንስል ሆነው በተከታታይ ያገለገሉት ወንድማማቾች ወሰኔና ነሲቡ ዛማኑኤል ናቸው::

አገር በቀል ከሆኑት ምሁራንና የመንግሥት ሹማምንት መካከል አያሌ መጻሕፍትን በመድረስና በአስተዳደርም ረገድ ለሚኒስትርነት ማዕረግ በመብቃት ከፍተኛ ዝና ያተረፈውን ኅሩይ ወልደ ሥላሴን መጥቀስ ይቻላል:: ኅሩይ መደበኛ ትምህርቱ የቤተ ክህነት ሲሆን ከዚያም ፈረንጆችን በመጠጋትና ከነሱም ጋር በመወዳጀት የአውሮጳ ቋንቋዎችን ለመቅሰምና የዕውቀቱንም አድማስ ለፋ





3.13 ተፈሪ መኰንን ት/ቤት በተቆረቆረበት ዘመን

ለማድረግ ችሏል:: እንደሱው ሌሎችም በቤተ ክህነት ትምህርት የታነፁ ምሁራን በዘመኑ የምሁራን እንቅስቃሴና በማቆጥቆጥ ላይ ባለው ዘመናዊ አስተዳደር ውስጥ የማይናቅ ሚና ተጫውተዋል:: በተለይም የእንጦጦ ራጉኤል ቤተ ክርስቲያን በዚህ ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አበርክታለች:: ዝናና ሥልጣን ካተረፉት የራጉኤል ምሩቃን መካከል ከኅሩይ በተጨማሪ ታከለ ወልደ ሐዋርያትና መኰንን ሀብተ ወልድ ይገኙበታል:: ታከለ በጉምሩክ ሹምነት፣ በአዲስ አበባ ከንቲባነት፣ በስመ ጥር አርበኝነት አገሩን ያገለገለ ሲሆን የመጨረሻ የሕይወት ዘመኑን አፄ ኃይለ ሥላሴን ከሥልጣን ለማውረድ ባላሰለሰ ትግል ደምድሞታል:: በተቃራኒው መኰንን ሀብተ ወልድ በነመንግሥቱ ንዋይ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ወቅት እስከተገደለበት ጊዜ ድረስ የኃይለ ሥላሴ ታማኝ አገልጋይና የፖለቲካ ሥርዓቱም መከታ ሆኖ ቆይቷል::

የመደበኛ ትምህርት በኢትዮጵያ መስፋፋትን በተመለከተ በምኒልክ ዘመነ መንግሥት ፍጻሜ አካባቢ አንድ ዐቢይ ድርጊት ተከናውኗል:: ይህም በንጉሠ ነገሥቱ ስም የሚታወቀው ትምህርት ቤት በ1900 መከፈቱ ነው::



3.14 የሃያኛው መቶ ዓመት መጀመሪያ ተማሪዎች

በአስተማሪነት እንዲያገለግሉ ግብፃውያን ክርስቲያን (ቆብጦች) መመረጣቸው እንደሚያመለክተው፣ የንጉሡ ነገሥቱ ፍላጎት ባህላዊ ፈር ያልለቀቀ ዘመናዊ ሥልጣኔ ለማስገባት ነበር። ግብፃውያኑ መምህራን እንደ ኢትዮጵያውያን ኦርቶዶክስ ክርስቲያን በመሆናቸው ለተማሪዎቹ ዘመናዊ ሐሳቦችን በተለምዶ እምነት አለዝበው ያቀርቡላቸዋል የሚል አስተሳሰብ የነበረ ይመስላል። ሥርዓተ ትምህርቱን ስንመለከት ደግሞ ለጊዜው በጣም የሚያስፈልጉት አስተርጓሚዎች ስለሆኑም ይመስላል የሚያደላው ወደ ቋንቋ ትምህርቱ ነበር። የማስተማሪያ ቋንቋውና ባጠቃላይም ከ1933 በኋላ በእንግሊዝኛ እስከተተካ ድረስ የምሁራኑ መገናኛ ፈረንሳይኛ ነበር።

ከ1904 በኋላ በድሬዳዋና በአዲስ አበባ የአልያንስ ፍራንሴዝ ትምህርት ቤቶች መቋቋም ይህን የፈረንሳይ ባህላዊ የበላይነት ይበልጥ አጠናክሮታል። ራስ ተፈሪ በ1917 የከፈተው የተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት ከአንጋፋው ከምኒልክ ትምህርት ቤት የበለጠ ፈረንሳዊ ዝንባሌ ነበረው። ዲሬክተሮቹ ፈረንሳዮች ሲሆኑ፣ ተማሪዎቹም የፈረንሳይ መንግሥት ሠርቲፊኬት ፈተናዎች እንዲወስዱ ተደርጎ ነበር። በመጠኑም ቢሆን ት/ቤቱ ከኢትዮጵያ ቁጥጥር ውጭ እንዳይወጣ ለማረጋገጥ የተቻለው በአስተዳዳሪው ቢሮ አማካይነት ነው። ማዕከላዊ የትምህርት አስተዳደርን ስንመለከት ደግሞ ሚኒስትሮች ሲቋቋሙ የትምህርት ጉዳይ ለጻጻሱ ጽ/ቤት ተትቶ ነበር። ኋላ ግን ከ1923 በኋላ የትምህርት ሚኒስቴር ራሱን የቻለ መሥሪያ ቤት ሆኖ ተቋቋመ። ከዐፄ ኃይለ ሥላሴ ሥርዓተ ንግሥ




በኋላም በአዲስ አበባም ሆነ በክፍላተ ሀገር በማዕከላዊው መንግሥትና በክፍለ ሀገር ገዥዎች አያሌ ትምህርት ቤቶች ተከፍተዋል።

ከአልጋ ወራሽ ራስ ተፈሪ ዘመን ጀምሮ የታየ አንድ ሌላ ነገር፣ በብዛት ወጣት ኢትዮጵያውያንን ለትምህርት ወደ ውጭ አገር የመላኩ ጉዳይ ነው። ብዙዎቹ የሄዱት ወደ ፈረንሳይ ሲሆን፣ እንደ መሸጋገሪያ ጣቢያ ያገለግላቸው የነበረው ግን በግብፅ ሀገር እስክንድርያ የሚገኘው ሊሴ ነበር። ከነፃነት በኋላ ከፍተኛ ሥልጣን የያዙት አያሌ ባለሥልጣኖች በዚህ ዓይነት መንገድ ነበር የሄዱት። ጥቂቶች ደግሞ ወደ እንግሊዝና አሜሪካ እንዲሁም ወደ ስዊዘርላንድ ሄደዋል። ባጠቃላይ ከኢጣልያ ወረራ በፊት በመንግሥት ድጋፍም ሆነ በግል ጥረት 200 የሚያህሉ ኢትዮጵያውያን ውጭ ሀገር ተምረዋል።

በሌሎች ኅብረተሰቦች እንደታየው ሁሉ በኢትዮጵያም የዘመናዊ ትምህርት መስፋፋት ሁለት ውጤቶች ነበሩት። እነሱም ታዳጊውን ቢሮክራሲ የሚሞላ የሠለጠነ የሰው ኃይል ማፍራትና የለውጥ ሐሳቦችን ማስራጩት ናቸው። ባጭር አነጋገር ዘመናዊ ትምህርት ባለሟሎችና ምሁራንን ያፈራል። በኢትዮጵያም የሆነው ይኸው ነው። ባለሟሎቹ ከመንግሥት መዋቅር ጋር በቅርብ የተሳሰሩና በዕለት ተዕለት አስተዳደር ተጠምደው ለምሁራዊ ምርምርና ትንታኔ እምብዛም ጊዜ የሌላቸው ናቸው። ይህን ሐቅ የሚሽረው ቢኖር ምናልባት የተሰጠው የመንግሥት ኃላፊነት አያሌ መጻሕፍትን ከመድረስ ያላገደው ኅሩይ ወልደ ሥላሴ ነው። ምሁራኑ ደግሞ ብዙውን ጊዜ ከመንግሥት መዋቅር ጋር የነበራቸው ግንኙነት የያዝ ለቀቅ ነው። ባለሟሎች ባብዛኛው አገር ቤት የተማሩ ሲሆኑ፣ ምሁራኑ ደግሞ ውጭ የተማሩ ወይ የኖሩ ናቸው። ባለሟሎቹ በመንግሥቱ መዋቅር ቋሚ ስፍራ ቢያገኙም እስከ ጣልያን ወረራ ድረስ ለሚኒስትርነት ማዕረግ መብቃት የቻሉት ከሁለት ሦስት አይበልጡም። አብዛኛውን ጊዜ የተማሩ ኢትዮጵያውያን የቢሮክራሲያዊ እድገት ጣራ የዋና ዲሬክተርነት ማዕረግ ነበር።

ምሁራኑ ያገራቸውን ኋላ ቀርነት በመተቸት ከዐድዋ ድል በኋላ ሰፍኖ የነበረውን የማን አለብኝና ምን ጎደለብኝ ስሜት ባዶነት አሳይተዋል። የተረጋገጠው የፖለቲካ ነፃነት ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ መሠረት ካልተሰጠው አስተማማኝ አለመሆኑን ጠቁመዋል። ስለሆነም የሚከተሉት የማሻሻያ እርምጃዎች እንዲወሰዱ አበክረው መክረዋል፤ ቁርጥ ግብር፣ የሃይማኖት እርነት፣ ያረጀውን ፍትሐ ነገሥት በዘመናዊ የፍትሕ ሥርዓት መተካት፣ አለቅጥ የተንዛዛውን የአማርኛ ሥርዓተ ፊደል ማቀላጠፍ፣ ማዕከላዊና አንድ ወጥ የጉምሩክ አስተዳደር መመሥረትና ወታደራዊና የገንዘብ ማሻሻያ እርምጃዎች መውሰድ ናቸው። በተለይ ምሁራኑ ያተኮሩባቸው ሁለት ዐበይት ነጥቦች ግን የአስከፊው የገባር ሥርዓት መወገድና የትምህርት መስፋፋት ናቸው። ምሁራኑን የሚያስተባብር አንድ መፈክር ቢኖር ትምህርት ነው፤ ቀጥሎ ደግሞ የገባሩን የስቆቃው ኑሮ ያልገለጸና ከመከራው እንዲገላገልም ሐሳብ ያልሰነዘረ ምሁር በጣም ጥቂት ነው። ምሁራኑ እንደ አርአያ ይመለከቷት የነበረው በጥቂት ዓመታት ውስጥ እንደ ኢትዮጵያ ፊውዳል ከነበረ ኅብረተ ሰብ ወደ ኢንዱስትሪ ባለቤትነት የተለወጠችውን ጃፓንን ነበር። ስለዚህም ምሁራኑ አንዳንዴ ናፋቂ ጃፓን (ወይም «ጃፖናይዘርስ») የሚል ቅጥያ ተሰጥቷቸዋል። ተከለ ሐዋርያት ያረቀቀው የ1923 ሕገ መንግሥትም ባብዛኛው በ1881 የታወጀውን የሜይጂ ጃፓን ሕገ መንግሥትን የተመረከዘ ነው።



3.14 የሃያኛው መቶ ዓመት መጀመሪያ ተማሪዎች

በአስተማሪነት እንዲያገለግሉ ግብፃውያን ክርስቲያን (ቀብጦች) መመረጣቸው እንደሚያመለክተው፣ የንጉሡ ነገሥቱ ፍላጎት ባህላዊ ፈር ያልለቀቀ ዘመናዊ ሥልጣኔ ለማስገባት ነበር:: ግብፃውያኑ መምህራን እንደ ኢትዮጵያውያን ኦርቶዶክስ ክርስቲያን በመሆናቸው ለተማሪዎቹ ዘመናዊ ሐሳቦችን በተለምዶ እምነት አለዝበው ያቀርቡላቸዋል የሚል አስተሳሰብ የነበረ ይመስላል:: ሥርዓተ ትምህርቱን ስንመለከት ደግሞ ለጊዜው በጣም የሚያስፈልጉት አስተርጓሚዎች ስለሆኑም ይመስላል የሚያደላው ወደ ቋንቋ ትምህርቱ ነበር:: የማስተማሪያ ቋንቋውና ባጠቃላይም ከ1933 በኋላ በእንግሊዝኛ እስከተተካ ድረስ የምሁራኑ መግባቢያ ፈረንሳይኛ ነበር::

ከ1904 በኋላ በድሬዳዋና በአዲስ አበባ የአልያንስ ፍራንሴዝ ትምህርት ቤቶች መቋቋም ይህን የፈረንሳይ ባህላዊ የበላይነት ይበልጥ አጠናክሮታል:: ራስ ተፈሪ በ1917 የከፈተው የተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት ከአንጋፋው ከምኒልክ ትምህርት ቤት የበለጠ ፈረንሳዊ ዝንባሌ ነበረው:: ዲሬክተሮቹ ፈረንሳዮች ሲሆኑ፣ ተማሪዎቹም የፈረንሳይ መንግሥት ሠርቲፊኬት ፈተናዎች እንዲወስዱ ተደርጎ ነበር:: በመጠኑም ቢሆን ት/ቤቱ ከኢትዮጵያ ቁጥጥር ውጭ እንዳይወጣ ለማረጋገጥ የተቻለው በአስተዳዳሪው ቢሮ አማካይነት ነው:: ማዕከላዊ የትምህርት አስተዳደርን ስንመለከት ደግሞ ሚኒስትሮች ሲቋቋሙ የትምህርት ጉዳይ ለጻጻሉ ጽ/ቤት ተትቶ ነበር:: ኋላ ግን ከ1923 በኋላ የትምህርት ሚኒስቴር ራሱን የቻለ መሥሪያ ቤት ሆኖ ተቋቋመ:: ከዐፄ ኃይለ ሥላሴ ሥርዓተ ንግሥ



በኋላም በአዲስ አበባም ሆነ በክፍላተ ሀገር በማዕከላዊው መንግሥትና በክፍለ ሀገር ገዥዎች አያሌ ትምህርት ቤቶች ተከፍተዋል::

ከአልጋ ወራሽ ራስ ተፈሪ ዘመን ጀምሮ የታየ አንድ ሌላ ነገር፣ በብዛት ወጣት ኢትዮጵያውያንን ለትምህርት ወደ ውጭ አገር የመላኩ ጉዳይ ነው:: ብዙዎቹ የሄዱት ወደ ፈረንሳይ ሲሆን፣ እንደ መሸጋገሪያ ጣቢያ ያገለግላቸው የነበረው ግን በግብፅ ሀገር እስክንድርያ የሚገኘው ሊሴ ነበር:: ከነፃነት በኋላ ከፍተኛ ሥልጣን የያዙት አያሌ ባለሥልጣኖች በዚህ ዓይነት መንገድ ነበር የሄዱት:: ጥቂቶች ደግሞ ወደ እንግሊዝና አሜሪካ እንዲሁም ወደ ስዊዘርላንድ ሄደዋል:: ባጠቃላይ ከኢጣልያ ወረራ በፊት በመንግሥት ድጋፍም ሆነ በግል ጥረት 200 የሚያህሉ ኢትዮጵያውያን ውጭ ሀገር ተምረዋል::

በሌሎች ኅብረተሰቦች እንደታየው ሁሉ በኢትዮጵያም የዘመናዊ ትምህርት መስፋፋት ሁለት ውጤቶች ነበሩት:: እነሱም ታዳጊውን ቢሮክራሲ የሚሞላ የሠለጠነ የሰው ኃይል ማፍራትና የለውጥ ሐሳቦችን ማስራጨት ናቸው:: ባጭር አነጋገር ዘመናዊ ትምህርት ባለሟሎችና ምሁራንን ያፈራል:: በኢትዮጵያም የሆነው ይኸው ነው:: ባለሟሎቹ ከመንግሥት መዋቅር ጋር በቅርብ የተሳሰሩና በዕለት ተዕለት አስተዳደር ተጠምደው ለምሁራዊ ምርምርና ትንታኔ እምብዛም ጊዜ የሌላቸው ናቸው:: ይህን ሐቅ የሚሸረው ቢኖር ምናልባት የተሰጠው የመንግሥት ኃላፊነት አያሌ መጻሕፍትን ከመድረስ ያላገደው ኅሩይ ወልደ ሥላሴ ነው:: ምሁራኑ ደግሞ ብዙውን ጊዜ ከመንግሥት መዋቅር ጋር የነበራቸው ግንኙነት የያዝ ለቀቅ ነው:: ባለሟሎች ባብዛኛው አገር ቤት የተማሩ ሲሆኑ፣ ምሁራኑ ደግሞ ውጭ የተማሩ ወይ የኖሩ ናቸው:: ባለሟሎቹ በመንግሥቱ መዋቅር ቋሚ ስፍራ ቢያገኙም እስከ ጣልያን ወረራ ድረስ ለሚኒስትርነት ማዕረግ መብቃት የቻሉት ከሁለት ሦስት አይበልጡም:: አብዛኛውን ጊዜ የተማሩ ኢትዮጵያውያን የቢሮክራሲያዊ እድገት ጣራ የዋና ዲሬክተርነት ማዕረግ ነበር::

ምሁራኑ ያገራቸውን ኋላ ቀርነት በመተቸት ከዐድዋ ድል በኋላ ሰፍኖ የነበረውን የማን አለብኝነና ምን ጎደለብኝ ስሜት ባዶነት አሳይተዋል:: የተረጋገጠው የፖለቲካ ነፃነት ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ መሠረት ካልተሰጠው አስተማማኝ አለመሆኑን ጠቁመዋል:: ስለሆነም የሚከተሉት የማሻሻያ እርምጃዎች እንዲወሰዱ አበክረው መክረዋል፣ ቁርጥ ግብር፣ የሃይማኖት እርነት፣ ያረጀውን ፍትሐ ነገሥት በዘመናዊ የፍትሕ ሥርዓት መተካት፣ አለቅጥ የተንዛዛውን የአማርኛ ሥርዓተ ፊደል ማቀላጠፍ፣ ማዕከላዊና አንድ ወጥ የጉምሩክ አስተዳደር መመሥረትና ወታደራዊና የገንዘብ ማሻሻያ እርምጃዎች መውሰድ ናቸው:: በተለይ ምሁራኑ ያተኮሩባቸው ሁለት ዐበይት ነጥቦች ግን የአስከፊው የገባር ሥርዓት መወገድና የትምህርት መስፋፋት ናቸው:: ምሁራኑን የሚያስተባብር አንድ መፈክር ቢኖር ትምህርት ነው:: ቀጥሎ ደግሞ የገባሩን የሰቆቃው ኑሮ ያልገለጸና ከመከራው እንዲገላገልም ሐሳብ ያልሰነዘረ ምሁር በጣም ጥቂት ነው:: ምሁራኑ እንደ አርአያ ይመለከቷት የነበረው በጥቂት ዓመታት ውስጥ እንደ ኢትዮጵያ ፊውዳል ከነበረ ኅብረተ ሰብ ወደ ኢንዱስትሪ ባለቤትነት የተለወጠችውን ጃፓንን ነበር:: ስለዚህም ምሁራኑ አንዳንዴ ናፋቂ ጃፓን (ወይም «ጃፓናይዘርስ») የሚል ቅጥያ ተሰጥቷቸዋል:: ተክለ ሐዋርያት ያረቀቀው የ1923 ሕገ መንግሥትም ባብዛኛው በ1881 የታወጀውን የሜይጂ ጃፓን ሕገ መንግሥትን የተመረኮዘ ነው::

የምሁራኑ ትልቅ ድክመት የተደራጀ ነፃ ኃይል ለመሆን አለመቻላቸው ነው። የለውጥ ሐሳቦቻቸውን ሥራ ላይ ለማዋል ያላቸው አማራጭ አንዱን ተራማጅ አስተሳሰብ ያለውን ልዑል መጠጋት ብቻ ነበር። ይህም ሁኔታ ነው ላጭር ጊዜም ቢሆን አንዳንዶቹን የኢያሱ አጋር ያደረጋቸው። ተክለ ሐዋርያትም፣ ገብረ ሕይወትም መጀመሪያ ተስፋቸውን በኢያሱ ላይ ጥለው ነበር። ተክለ ሐዋርያት የኢያሱ ዋና አማካሪ ለመሆን ከበቃ በኋላ ሰው ሁሉ በወጣቱ ልዑል ላይ ፊቱን ሲያዞር እርሱም ሠልፉን አስተካከሏል። ገብረ ሕይወትም "አፄ ምኒልክና ኢትዮጵያ" የተሰኘ ድርሰቱን በተለይ ለኢያሱ ብሎ የጻፈው የለውጥ ንድፍ ለመሆኑ የመጨረሻው አንቀጽ ያረጋግጥልናል።

ኢያሱ ከዙፋን ሲወርድ ምሁራኑ ዐይናቸውን ወደ ሌላው ወጣት ልዑል ወደ ራስ ተፈሪ አዞሩ። ተፈሪም መጀመሪያ ብዙ አላሳፈራቸውም። እንዲያውም ተፈሪ በአልጋ ወራሽነት ዘመኑና በኋላም አፄ ኃይለ ሥላሴ ከሆነ በኋላ የወሰዳቸው የለውጥ እርምጃዎች በቀጥታ ከገብረ ሕይወት መጽሐፍ የተወሰዱ ይመስላሉ። ተክለ ሐዋርያትም ያዘጋጀውን ትንሽ የአስተዳደር ማኑዋል ለማስረዳት የልጅ ኢያሱን ጆሮ ለማግኘት ያልተቻገረውን ያህል በአፄ ኃይለ ሥላሴ ያገሪቱን የመጀመሪያ ሕገመንግሥት እንዲያረቅ ታዘዘ። የሆነ ሆኖ የምሁራኑና የተፈሪ ኃይለ ሥላሴ ወዳጅነት የፍቅር ሳይሆን የጥቅም ጋብቻ ነበር። ምሁራኑ ተፈሪን ሊጠቀሙበት ከቻሉት ይልቅ እሱ ሥልጣኑን ለማደላደል ተጠቅምባቸዋል። እንዲህ ያለ ጋብቻ በመጨረሻው ፍች እንደሆነም የኃይለ ሥላሴና የተክለ ሐዋርያት የኋላ አለመጣጣም አንድ ጉልህ ማስረጃ ነው።

# የፖለቲካ ሁኔታዎች

## ዘመነ መደላደል /1888-1898/

ከዐድዋ ድል በኋላ ያሉት ዐሥር ዓመታት ምኒልክ በአገር ውስጥም ሆነ ካገር ውጭ የገነነበት ወቅት ነበር። ድሉ በተገኘ በሁለት ዓመት ውስጥ ቀደም ብሎ የጀመረውን የግዛት ማስፋፋት ሂደት አጠናቋል። በአገር ውስጥ ይህ ነው የሚባል የሥልጣን ተቀናቃኝ አልነበረውም። በውጭው ዓለምም በኢጣልያ ላይ ያገኘው ድል ስመ ጥር አድርጎታል። አንዱ የውጭ አገር ታዛቢ ምኒልክን የጀርመንን አንድነት ከመሠረተውና በ19ኛው መቶ ዓመት ታላቅ የአውሮጳ ፖለቲካ ሰው ከሆነው ከቢዝማርክ ጋር አወዳድሮታል። ፈረንጆች በግልም ሆነ በኦፊሲየል የሱን ሞገስ አግኝተው ጥቅማቸውን ለማራመድ ወደ አዲስ አበባ ይጎርፉ ጀመር። ይህ መደላደልና መዝናናት ግን በ1898 መናጋት ጀመረ። በዚያን ዓመት ምኒልክን ከሰባት ዓመት በኋላ ለሞት ያበቃው በሽታ የመጀመሪያ ምልክት አሳየ። ለተንኮሉ ደግሞ በዚያው ዓመት በብዙ ሰዎች ሕሊና አልጋውን ይወርሳል እየተባለ ይታሰብ የነበረው ራስ መኰንን ሞተ። አሁን ከምኒልክ በኋላ ማን ነው የሚነግሠው የሚለው ጥያቄ አፍጦ መጣ። አከታትለውም ሦስቱ መንግሥታት (እንግሊዝ፣ ፈረንሳይ፣ ኢጣልያ) በኢትዮጵያ ላይ ስምምነት ሲፈራረሙ ያገሪቱ የወደፊት ነፃ ህልውና አጠያያቂ ሆነ።





3.15 ዳግማዊ አፄ ምኒልክ

የምሁራኑ ትልቅ ድክመት የተደራጀ ነፃ ኃይል ለመሆን አለመቻላቸው ነው:: የለውጥ ሐሳቦቻቸውን ሥራ ላይ ለማዋል ያላቸው አማራጭ አንዱን ተራማጅ አስተሳሰብ ያለውን ልዑል መጠጋት ብቻ ነበር:: ይህም ሁኔታ ነው ላጭር ጊዜም ቢሆን አንዳንዶቹን የኢያሱ አጋር ያደረጋቸው:: ተክለ ሐዋርያትም፣ ገብረ ሕይወትም መጀመሪያ ተስፋቸውን በኢያሱ ላይ ጥለው ነበር:: ተክለ ሐዋርያት የኢያሱ ዋና አማካሪ ለመሆን ከበቃ በኋላ ሰው ሁሉ በወጣቱ ልዑል ላይ ፊቱን ሲያዞር እርሱም ሠልፉን አስተካክሏል:: ገብረ ሕይወትም "አፄ ምኒልክና ኢትዮጵያ" የተሰኘ ድርሰቱን በተለይ ለኢያሱ ብሎ የጻፈው የለውጥ ንድፍ ለመሆኑ የመጨረሻው አንቀጽ ያረጋግጥልናል::

ኢያሱ ከዙፋን ሲወርድ ምሁራኑ ዐይናቸውን ወደ ሌላው ወጣት ልዑል ወደ ራስ ተፈሪ አዞሩ:: ተፈሪም መጀመሪያ ብዙ አላሳፈራቸውም:: እንዲያውም ተፈሪ በአልጋ ወራሽነት ዘመኑና በኋላም አፄ ኃይለ ሥላሴ ከሆነ በኋላ የወሰዳቸው የለውጥ እርምጃዎች በቀጥታ ከገብረ ሕይወት መጽሐፍ የተወሰዱ ይመስላሉ:: ተክለ ሐዋርያትም ያዘጋጀውን ትንሽ የአስተዳደር ማኑዋል ለማስረዳት የልጅ ኢያሱን ጆሮ ለማግኘት ያልተቸገረውን ያህል በአፄ ኃይለ ሥላሴ ያገሪቱን የመጀመሪያ ሕገመንግሥት እንዲያረቅ ታዘዘ:: የሆነ ሆኖ የምሁራኑና የተፈሪ ኃይለ ሥላሴ ወዳጅነት የፍቅር ሳይሆን የጥቅም ጋብቻ ነበር:: ምሁራኑ ተፈሪን ሊጠቀሙበት ከቻሉት ይልቅ እሱ ሥልጣኑን ለማደላደል ተጠቅሞባቸዋል:: እንዲህ ያለ ጋብቻ በመጨረሻው ፍች እንደሆነም የኃይለ ሥላሴና የተክለ ሐዋርያት የኋላ አለመጣጣም አንድ ጉልህ ማስረጃ ነው::

## የፖለቲካ ሁኔታዎች


### ዘመነ መደላደል /1888-1898/

ከዐድዋ ድል በኋላ ያሉት ዐሥር ዓመታት ምኒልክ በአገር ውስጥም ሆነ ካገር ውጭ የገነነበት ወቅት ነበር:: ድሉ በተገኘ በሁለት ዓመት ውስጥ ቀደም ብሎ የጀመረውን የግዛት ማስፋፋት ሂደት አጠናቋል:: በአገር ውስጥ ይህ ነው የሚባል የሥልጣን ተቀናቃኝ አልነበረውም:: በውጭው ዓለምም በኢጣልያ ላይ ያገኘው ድል ስመ ጥር አድርጎታል:: አንዱ የውጭ አገር ታዛቢ ምኒልክን የጀርመንን አንድነት ከመሠረተውና በ19ኛው መቶ ዓመት ታላቅ የአውሮጳ ፖለቲካ ሰው ከሆነው ከቢዝማርክ ጋር አወዳድሮታል:: ፈረንጆች በግልም ሆነ በአፊሲየል የሱን ሞገስ አግኝተው ጥቅማቸውን ለማራመድ ወደ አዲስ አበባ ይጎርፉ ጀመር:: ይህ መደላደልና መዝናናት ግን በ1898 መናጋት ጀመረ:: በዚያን ዓመት ምኒልክን ከሰባት ዓመት በኋላ ለሞት ያበቃው በሽታ የመጀመሪያ ምልክት አሳየ:: ለተንኰሉ ደግሞ በዚያው ዓመት በብዙ ሰዎች ሕሊና አልጋውን ይወርሳል እየተባለ ይታሰብ የነበረው ራስ መኰንን ሞተ:: አሁን ከምኒልክ በኋላ ማን ነው የሚነግሠው የሚለው ጥያቄ አፍጦ መጣ:: አከታትለውም ሦስቱ መንግሥታት (እንግሊዝ፣ ፈረንሳይ፣ ኢጣልያ) በኢትዮጵያ ላይ ስምምነት ሲፈራረሙ ያገሪቱ የወደፊት ነፃ ህልውና አጠያያቂ ሆነ::





3.15 ዳግማዊ አፄ ምኒልክ



3.16 ራስ መኰንን ወልደ ሚካኤል፣ የሐረር ገዥ በ1897 ወደ ኢትዮጵያ ከመጣው የጀርመን ልኡካን ቡድን ጋር

በዐድዋ ማግስት የውጭ መንግሥታት የኢትዮጵያን ነፃነት በሁለት ዓይነት መንገድ ዐውቀው ነበር፤ አዲስ አበባ ውስጥ ሌጋሲዮናቸውን በመክፈትና አዋሳኝ ቅኝ ግዛት ያላቸው ደግሞ ድንበር በመካለል:: የዐድዋ ድል በተረጋገጠ በዓመቱ ኢጣልያ፣ ፈረንሣይና እንግሊዝ በዚያው ቅደም ተከተል በተንጣለለ ግቢ ውስጥ ሌጋሲዮናቸውን መሠረቱ:: እንደ እድል ሆኖ ሦስቱም የዲፕሎማሲ ሙያ በተካኑ ሚኒስትሮች (በዛሬው አጠራር አምባሳደሮች) ተወክለው ነበር፤ ፌዴሪኮ ቺኮዲኮላ ለጣልያኖች፣ ሌኦንስ ላጋርድ ለፈረንሳዮች እና ጆን ሀሪንግተን ለእንግሊዞች:: በ1896 ደግሞ በማያሻማ መንገድ የንግድ ተልእኮ ይዞ የመጣው የአሜሪካ ልዑካን ቡድን በተለይ ከነፃነት ወዲህ ጥብቅ እየሆነ ለመጣው የሁለቱ ሀገሮች ወዳጅነት መሠረቱን ጣለ:: ይህ በሆነ በሁለት ዓመት ደግሞ ጀርመኖች ብቅ አሉ:: ሦስቱ ኃያላን ጥቅማችን ሊነካ ነው ብለው እጅግ የደነገጡት በዚህ



ወቅት ነው:: የ1899ኙን የጥቅም ማስከበር ውል ለመፈራረም የተጣደፉትም በዚህ ምክንያት ነው::

በኢትዮጵያና በአካባቢ ቅኝ ግዛቶች መካከል ያለውን ድንበር በሕግ ለመከለል አጥብቀው የፈለጉት ከምኒልክ ይልቅ ያካባቢው ቅኝ ገዥዎች ናቸው:: ምክንያቱም የድኅረ ዐድዋ ኢትዮጵያን ከፍተኛ የመስፋፋት ችሎታ ለመግታት ያለው አመች መንገድ ይኸ ሆኖ ስላገኙት ነው:: በዚህ ዓይነት መጀመሪያ የተከለለው ድንበር በመጋቢት 12፣ 1889 በኢትዮጵያና በፈረንሳይ ሶማሊላንድ መካከል ነው:: ከሁለት ወር ተኩል በኋላ ኢትዮጵያንና የእንግሊዝ ሶማሊላንድን የሚያዋስነው መሥመር ተከለለ:: ከድንበር ስምምነቱ ጋር ተያይዞ ሁለቱ ወገኖች ንግድን ለማስፋፋትና በማህዲስት ሱዳን ላይ የጦር መሣሪያ ማዕቀብ ለመጫንም ተስማምተው ነበር:: ከዚያም በሐምሌ 4፣ 1892 ከኢጣልያ ጋር በተደረገ ስምምነት የኤርትራ ከኢትዮጵያ መገንጠል ሕጋዊነት አገኘ::

ከሁሉም ረጅም የነበረውና ከሱዳን ጋር የሚያዋስነው ድንበር ውል ከረጅም ድርድር በኋላ በግንቦት 8፣ 1894 ተፈረመ:: ድርድሩ ያተኰረው በሦስት ቁልፍ ቦታዎች ላይ ነበር፤ መተማ (ወይም በሱዳኖች አጠራር ጋላባት)፣ በወርቅ ማዕድን ሀብቱ የታወቀው የቤኒ ሻንጉል ግዛትና ኢትዮጵያ ከፍተኛውን የግዛት መስፋፋት ያሳየችበት የባሮ ሸለቆ:: በውሉ መሠረት እንግሊዝ ለሱዳን ይገባል ያለቻቸውን አንዳንድ ግዛቶች ከማስመለስም አልፋ ጋምቤላን በንግድ ጣቢያነት ለመቆርቆርና ብጣና ሐይቅ ውሀ ላይ ያላትን የቅድሚያ መብትም ለማስከበር ችላለች:: ጥቂት ዓመታት ካለፉ በኋላ የኬንያ (በዚያን ጊዜ አጠራር የእንግሊዝ ምሥራቅ አፍሪቃ) እና የኢጣልያ ሶሚሊላንድ ወሰን በ1900 ሲፈረሙ፣ ኢትዮጵያ ዘመናዊ ቅርጿን ለማግኘት በቃች::

እነዚህ በዐሥር ዓመታት ውስጥ የተጠናቀቁት የድንበር ስምምነቶች የኢትዮጵያን የሃያኛው መቶ ዓመት የፖለቲካ ሕይወት የወሰኑ ናቸው:: በውሉቹ አማካይነትም ኢትዮጵያ ከሞላ ጐደል ዘመናዊ መልኳን ለመያዝ በቃች:: ይሁንና ስምምነቶቹ ባፈጻጸም ላይ አንዳንድ ችግሮች ማስከተላቸው አልቀረም:: መጀመሪያ ነገር ጠረጴዛ ዙሪያ ተቀምጦ ካርታ ዘርግቶ ድንበር መካለል አንድ ነገር ነው:: በቦታው ተገኝቶ ድንበሩን በምልክት መለየት ደግሞ ሌላ:: አብዛኞዎቹ ድንበሮች ካርታ ላይ በመሥመር ተከለሉ እንጂ መሬት ላይ በቅጡ አልተለዩም:: በተለይም ኢትዮጵያን ከሱዳንና ኤርትራ ጋር የሚያዋስነው ረጅም ድንበር ባብዛኛው በምልክት ያልተለየ ነበር:: ከእንግሊዝ ሶማሊላንድ ጋር ያለውን ድንበር ለመለየት ሙከራ የተደረገውም በ1920ዎቹ አጋማሽ ላይ ሲሆን እሱም በተዘዋዋሪ መንገድ ለወልወል ግጭት መነሾ ሆኗል:: ሁለተኛ በዳር አገር ጠንካራ አስተዳደር ለመመሥረት ባለመቻሉ፣ ድንበር መከለል ባብዛኛው ከካርታ ሥራ ልምምድ እምብዛም ያልተሻለ ነበር ማለት ይቻላል:: በተለይም በደቡብና በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ድንበር ዘሎ መውረርና መዝረፍ የተለመደ ነገር ነበር:: ባንድ በኩልም በድንበሩ አካባቢ የሚገኙትን ሕዝቦች የግጦሽ ፍላጎትና ብሔረ ሰባዊ አንድነት ከቁጥር ያላስገባ ድንበር ከበሬታ ያገኛል ብሎ መጠበቅ ዘበት ነው:: ይሁን እንጂ ያካባቢው ቅኝ ገዥዎች እንዲህ ዓይነቱን ድንበር መጣስ በቸልታ የሚያዩት አልነበረም:: የአካባቢው ሕዝብ በወረራውና በዝርፊያው መጎሳቆሉ አሳዝኗቸው ሳይሆን የጦር መሣሪያው መዛመት ከቀጠለ ቅኝ ግዛታዊ አስተዳደራችንን ያናጋብናል በሚል ሥጋት የኢትዮጵያ መንግሥት



3.16 ራስ መኰንን ወልደ ሚካኤል፣ የሐረር ገዥ በ1897 ወደ ኢትዮጵያ ከመጣው የጀርመን ልኡካን ቡድን ጋር

በዐድዋ ማግስት የውጭ መንግሥታት የኢትዮጵያን ነፃነት በሁለት ዓይነት መንገድ ዐውቀው ነበር፤ አዲስ አበባ ውስጥ ሌጋሲዮናቸውን በመክፈትና አዋሳኝ ቅኝ ግዛት ያላቸው ደግሞ ድንበር በመካለል:: የዐድዋ ድል በተረጋገጠ በዓመቱ ኢጣልያ፣ ፈረንሣይና እንግሊዝ በዚያው ቅደም ተከተል በተንጣለለ ግቢ ውስጥ ሌጋሲዮናቸውን መሠረቱ:: እንደ እድል ሆኖ ሦስቱም የዲፕሎማሲ ሙያ በተካኑ ሚኒስትሮች (በዛሬው አጠራር አምባሳደሮች) ተወክለው ነበር፤ ፌዴሪኮ ቺኮዲኮላ ለጣልያኖች፣ ሌኦንስ ላጋርድ ለፈረንሳዮች እና ጆን ሀሪንግተን ለእንግሊዞች:: በ1896 ደግሞ በማያሻማ መንገድ የንግድ ተልእኮ ይዞ የመጣው የአሜሪካ ልዑካን ቡድን በተለይ ከነፃነት ወዲህ ጥብቅ እየሆነ ለመጣው የሁለቱ ሀገሮች ወዳጅነት መሠረቱን ጣለ:: ይህ በሆነ በሁለት ዓመት ደግሞ ጀርመኖች ብቅ አሉ:: ሦስቱ ኃያላን ጥቅማችን ሊነካ ነው ብለው እጅግ የደነገጡት በዚህ



ወቅት ነው:: የ1899ኙን የጥቅም ማስከበር ውል ለመፈራረም የተጣደፉትም በዚህ ምክንያት ነው::

በኢትዮጵያና በአካባቢ ቅኝ ግዛቶች መካከል ያለውን ድንበር በሕግ ለመከለል አጥብቀው የፈለጉት ከምኒልክ ይልቅ ያካባቢው ቅኝ ገዥዎች ናቸው:: ምክንያቱም የድኅረ ዐድዋ ኢትዮጵያን ከፍተኛ የመስፋፋት ችሎታ ለመግታት ያለው አመች መንገድ ይኸ ሆኖ ስላገኙት ነው:: በዚህ ዓይነት መጀመሪያ የተከለለው ድንበር በመጋቢት 12፣ 1889 በኢትዮጵያና በፈረንሳይ ሶማሊላንድ መካከል ነው:: ከሁለት ወር ተኩል በኋላ ኢትዮጵያንና የእንግሊዝ ሶማሊላንድን የሚያዋስነው መሥመር ተከለለ:: ከድንበር ስምምነቱ ጋር ተያይዞ ሁለቱ ወገኖች ንግድን ለማስፋፋትና በማህዲስት ሱዳን ላይ የጦር መሣሪያ ማዕቀብ ለመጫንም ተስማምተው ነበር:: ከዚያም በሐምሌ 4፣ 1892 ከኢጣልያ ጋር በተደረገ ስምምነት የኤርትራ ከኢትዮጵያ መገንጠል ሕጋዊነት አገኘ::

ከሁሉም ረጅም የነበረውና ከሱዳን ጋር የሚያዋስነው ድንበር ውል ከረጅም ድርድር በኋላ በግንቦት 8፣ 1894 ተፈረመ:: ድርድሩ ያተኰረው በሦስት ቁልፍ ቦታዎች ላይ ነበር፤ መተማ (ወይም በሱዳኖች አጠራር ጋላባት)፣ በወርቅ ማዕድን ሀብቱ የታወቀው የቤኒ ሻንጉል ግዛትና ኢትዮጵያ ከፍተኛውን የግዛት መስፋፋት ያሳየችበት የባሮ ሸለቆ:: በውሉ መሠረት እንግሊዝ ለሱዳን ይገባል ያለቻቸውን አንዳንድ ግዛቶች ከማስመለስም አልፋ ጋምቤላን በንግድ ጣቢያነት ለመቆርቆርና በጣና ሐይቅ ውሀ ላይ ያላትን የቅድሚያ መብትም ለማስከበር ችላለች:: ጥቂት ዓመታት ካለፉ በኋላ የኬንያ (በዚያን ጊዜ አጠራር የእንግሊዝ ምሥራቅ አፍሪቃ) እና የኢጣልያ ሶማሊላንድ ወሰን በ1900 ሲፈረም፣ ኢትዮጵያ ዘመናዊ ቅርጿን ለማግኘት በቃች::

እነዚህ በዐሥር ዓመታት ውስጥ የተጠናቀቁት የድንበር ስምምነቶች የኢትዮጵያን የሃያኛው መቶ ዓመት የፖለቲካ ሕይወት የወሰኑ ናቸው:: በውሎቹ አማካይነትም ኢትዮጵያ ከሞላ ጐደል ዘመናዊ መልኳን ለመያዝ በቃች:: ይሁንና ስምምነቶቹ ባፈጻጸም ላይ አንዳንድ ችግሮች ማስከተላቸው አልቀረም:: መጀመሪያ ነገር ጠረጴዛ ዙሪያ ተቀምጦ ካርታ ዘርግቶ ድንበር መካለል አንድ ነገር ነው:: በቦታው ተገኝቶ ድንበሩን በምልክት መለየት ደግሞ ሌላ:: አብዛኛዎቹ ድንበሮች ካርታ ላይ በመሥመር ተከለሉ እንጂ መሬት ላይ በቅጡ አልተለዩም:: በተለይም ኢትዮጵያን ከሱዳንና ኤርትራ ጋር የሚያዋስነው ረጅም ድንበር ባብዛኛው በምልክት ያልተለየ ነበር:: ከእንግሊዝ ሶማሊላንድ ጋር ያለውን ድንበር ለመለየት ሙከራ የተደረገውም በ1920ዎቹ አጋማሽ ላይ ሲሆን እሱም በተዘዋዋሪ መንገድ ለወልወል ግጭት መነሻ ሆኗል:: ሁለተኛ በዳር አገር ጠንካራ አስተዳደር ለመመሥረት ባለመቻሉ፣ ድንበር መከለል ባብዛኛው ከካርታ ሥራ ልምምድ እምብዛም ያልተሻለ ነበር ማለት ይቻላል:: በተለይም በደቡብና በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ድንበር ዘሎ መውረርና መዝረፍ የተለመደ ነገር ነበር:: ባንድ በኩልም በድንበሩ አካባቢ የሚገኙትን ሕዝቦች የግጦሽ ፍላጎትና ብሔረ ሰባዊ አንድነት ከቁጥር ያላስገባ ድንበር ከበሬታ ያገኛል ብሎ መጠበቅ ዘበት ነው:: ይሁን እንጂ ያካባቢው ቅኝ ገዥዎች እንዲህ ዓይነቱን ድንበር መጣስ በቸልታ የሚያዩት አልነበረም:: የአካባቢው ሕዝብ በወረራውና በዝርፊያው መንሳቀሉ አሳዝኗቸው ሳይሆን የጦር መሣሪያው መዛመት ከቀጠለ ቅኝ ግዛታዊ አስተዳደራችንን ያናጋብናል በሚል ሥጋት የኢትዮጵያ መንግሥት

የዳር አገር ዜጎቹን እንዲቆጣጠር አቤቱታቸውንና ከዚያም አልፎ የጦር መሣሪያ ማዕቀባቸውን ቀጠሉ።

## የሥልጣን ትግል /1900-1923/

### የወራሴ መንግሥት ጥያቄ

ከምኒልክ በኋላ ኢትዮጵያ ምን ትሆን ይሆን፤ ማንስ ይገዛት ይሆን፤ የሚለው ጥያቄ ኢትዮጵያውያንንም ሆነ ፈረንጆችን ያሳሰበ ጥያቄ ነበር። ቀደም ብለን እንደጠቀስነው ሦስቱ አጎራባች ቅኝ ገዥዎች (እንግሊዝ፤ ፈረንሳይና ኢጣልያ) አደጋውን ለመከላከል በ1899 ስምምነት ላይ ደርሰዋል። ከስምምነቱ ዓይነተኛ ዓላማዎች አንዱ በመቅድሙ እንደተገለጸው «በኢትዮጵያ ያለው ሁኔታ (በማይፈልጉት አቅጣጫ) ከተለወጠ የሚወስዱትን እርምጃ ለማቀናጀት» ነበር። በስምምነቱ ተከታታይ አንቀጾችም በሀገሪቱ ያላቸውን ጥቅም የሚያስከብሩበትን ሕጋዊ መሠረት ደንግገዋል።

ምኒልክም ቢሆን እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል የሚል አመለካከት አልነበረውም። ሌሎች ግፊቶች ባይታጡም፤ በ1900 የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶችን ያቋቋመበት አንዱ ምክንያት ለመንግሥት ድርጅታዊ መሠረትና ቀጣይነት ለመስጠት ከነበረው ፍላጎት ይመስላል። እርግጥ ነው የመጀመሪያዎቹ ሚኒስትሮች በመሠረቱ አዲስ አውሮጳዊ ካባ የደረቡ የቤተ መንግሥት ባለሟሎች ነበሩ ማለት ይቻላል። ከሚኒስትሮቹ ያንዳንዶቹን ስምና ማዕረግ ዘርዝረን ብናይ በዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት አመሠራረት ላይ እንዳየነው የንጉሠ ነገሥቱ ፍላጎት አሁንም ባህልና ዘመናዊ ሥልጣኔን ለማስታረቅ እንደነበረ እንረዳለን።

| | |
|---|---|
| አፈ ንጉሥ ነሲቡ መስቀሉ | የፍርድ ሚኒስትር |
| ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ዲነግዴ | የጦር ሚኒስትር |
| ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ወ/አረጋይ | የጽሕፈት ሚኒስትር |
| በጅሮንድ ሙሉጌታ ይገዙ | የገንዘብ ሚኒስትር |
| ነጋድራስ ኃይለ ጊዮርጊስ ወልደ ሚካኤል | የንግድና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር |
| አዛዥ መታፈሪያ መልክ ጼዴቅ | የግቢ ሚኒስትር |

ከዚህ ዝርዝር እንደምናየው ከአዲሶቹ ሚኒስትሮች የሚጠበቀው ከሞላ ጎደል የቀድሞ ሥራቸውን እንዲሠሩ እንደነበረ ነው። ቀደም ብለን እንደጠቀስነው የትምህርት ጉዳይ ከአቡነ ጉያ እንዳይወጣ ተደርጓል። በውጭ ግንኙነት ረገድም ዋናው ሥልጣን የንጉሠ ነገሥቱ እንደሆነ በማያሻማ መንገድ ተደንግጓል። የሚኒስትሩ ተግባር ከቆንስላ ሥራና በውጭ ቋንቋ የተጻፉ ጽሑፎችን ከማስተርጐም ያላለፈ ነበር።

የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶቹ ተግባራት ተብለው ከተዘረዘሩትም አንዳንዶቹ ባገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ ሥራ ላይ ሊውሉ የሚችሉ ዓይነት አልነበሩም። ለምሳሌ የአገር ግዛት ሚኒስቴር የሕዝብ ቆጠራ የማካሄድና ልደት፤ ጋብቻና ሞትን የመመዝገብ ሥልጣን ተሰጥቶት ነበር። የጦር ሚኒስቴር



የጦር ሥልጠና ለመስጠት፤ የእርሻ ሚኒስቴርም በእርሻ ትጋት ላሳዩት ገበሬዎች ሽልማት ሲሰጥ በሰነፉት ላይ ደግሞ መቀጮ ለመጣል ደንብ ወጥቶላቸው ነበር። የገንዘብ ሚኒስቴርን ደንብ ስንመለከት ደግሞ በመንግሥት ግምጃ ቤትና በንጉሠ ነገሥቱ የግል ሀብት መካከል ግልጽ ልዩነት ለማድረግ ሙከራ ተደርጓል። እንደ እውነቱ ከሆነ ግን ይህ ሁኔታ እንኳን በ1900፤ በ1928 በኢትዮጵያና በኢጣልያ ጦርነት ዋዜማም ሥራ ላይ ውሎ አልተገኘም። አብዛኛዎቹ እንዲህ ያሉት የተራቀቁ ተግባራት እውን ይፈጸማሉ ተብሎ ሳይሆን ለፈረንጅ ጆሮ እንዲጥም ተብለው የተደነገጉ ይመስላል። ዋናው ዓላማ ኢትዮጵያ እንደ አውሮጳ መተዳደር ጀምራለች ተብሎ እንዲታሰብ መሆኑን ለእርሻ ሚኒስቴር በወጣው ደንብ ውስጥ «እንደ ኤሮፓ አገር ሥርዐት» ብሎ አንቀጹን ሲደመድም ማየት እንችላለን።

ይህ ሁሉ ሆኖ ግን የሚኒስቴራዊ አስተዳደር መመሥረት በመጠኑም ቢሆን ዘላቂ እርባና እንዳለው መዘንጋት የለበትም። በርግጥም የመንግሥት አስተዳደር ከነገሥታት መምጣትና መሄድ ባሻገር ራሱን የቻለ ቀጣይነት እንዲኖረው አነስተኛም ቢሆን አስተዋፅኦ አድርጓል። የዘመናዊ ቢሮክራሲ ልደትና እድገት መሠረቱ ይኸው የሚኒስትሮች መሥሪያ ቤት መቋቋም ነው። ባንድ በኩል እንደ ምኒልክ ያለ ጠንካራ ንጉሠ ነገሥት ከመድረኩ ሲታጣ፤ የሚኒስትሮችም ሥልጣን ባንፃሩ እያደገ መሄዱ አልቀረም። ይህ ሁኔታ በተለይም አብዛኛውን ጊዜውን ከመናገሻ ከተማው ውጪ ያሳልፍ በነበረው በኢያሱ ዘመነ መንግሥት ገሃድ ወጣ። እንደ ነጋድራስ ኃይለ ጊዮርጊስ ወልደ ሚካኤል ያለ ሰው መግነንና በገቢር የጠቅላይ ሚኒስትርነት ሥራ መሥራት በቀጥታ ከዚህ ሁኔታ የመነጨ ነው። የሚኒስትሮች እንዲህ ማየልና መበልፀግም ነው በ1910 በጃንሜዳ የተከሠተውን ሕዝባዊ አድማ ያስነሳባቸውና ኋላም ከሥራቸው ለመባረር ያበቃቸው።

በመሠረቱ የሚኒስትሮች መሾም በልደት ሳይሆን በአገልግሎት ለመኳንንትነት የበቃ የአዲስ መደብ መከሰትን ነው ያበሰረው። ኃይለ ጊዮርጊስ በከፈተው ፈለግ ኋላ ሌሎችም ጠንካራ ሚኒስትሮች ሊበቅሉ በቁ። እንዲህ ከመኳንንት ዘር ተወልደው ሳይሆን በሙያቸውና በአገልግሎታቸው ለመኳንንትነት ከበቁ መሐል የሚከተሉትን መጥቀስ ይቻላል፤ በኢጣልያ ወረራ ወቅት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የነበረው ኅሩይ ወልደ ሥላሴ፤ ከነፃነት በኋላ ደግሞ በጸሐፌ ትእዛዝነት በጠቅላይ ሚኒስትርነትና በሚኒስትርነት ያገለገሉት ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስና ወንድማማቾቹ መኰንን፤ አክሊሉና አካለወርቅ ሀብተወልድ።

ምኒልክ ሥልጣን ለማረካከብ የወሰደው እርምጃ ሚኒስትሮችን በመሾም ብቻ አልቆመም። በግንቦት 10፤ 1901 የልጁ የሸዋረጋና የወሎው ራስ ሚካኤል ጋብቻ ፍሬ የሆነው ኢያሱ አልጋ ወራሹ እንዲሆን መምረጡን በሚከተሉት ቃላት ዐወጀ፤

> ... እኔ ቴዎድሮስ የሞቱ ጊዜ ከሳቸው ጋራ የነበረው ሰው ሁሉ ያንዱን አገር አንዱ እደርባለሁ እንዱን ገድዬ እኔ ጌታ እሆናለሁ እያለ ሁሉም ሳይረባ ተላልቆ ቀረ።
>
> ከዚህም በኋላ ያዩ ዮሐንስ ሰው የትነውን የምታውቁት ነው፤ ባገር በሽታ ሳይገባበት ሌላ የባዕድ

ጦር ሳይነሣበት በምቀኝነት እርስ በርሱ እንደተላለቀ አይታችኋል።

አሁንም ልጆቼ ወዳጆቼ አንዱ ባንዱ ምቀኝነት ይቅር፣ ያንዱን አገር አንዱ እኔ እደርባለሁ እንዳትሉ። እኔ እስካሁን በፍቅር እንዳኖርኋችሁ እኖንተም ተስማምታችት በፍቅር እንድትኖሩ አለምናችኋለሁ።

እናንተ አንድ ልብ ከሆናችሁ በምቀኝነት እርስ በርሳችሁ ተዋግታችሁ ካላለቃችሁ በቀር አገራችንን ኢትዮጵያን ለሌላ ለባዕድ አትሰጧትም ክፉም ነገር አገራችንን አያገኛትም።

ይህንን ምክር ለናንተ መስጠቴ እኔማ በእግዚአብሔር ቸርነት ይህንን ያህል ዘመን ገዝቼ የለምን። ነገር ግን ሰው ነኝና እንግዲህ እስንት ያህል ዘመን እቆያለሁ ስል ነው።

አሁንም እኔ እንደተመኘሁት እግዚአብሔር የተጨመረበትና ፈቃዱ ሁኖ ልጄን (የልጅ ልጄን ኢያሱን ለማለት ነው) ቢአቆምላችሁ ከልጄ ጋር ሁናችት አገራችሁን ጠብቁ አደራ ብያችኋለሁ። (አፈወርቅ፣ 113-115)

አልጋ ወራሹ ገና ለአካለ መጠን ያልደረሰ ሎርቃ በመሆኑም የሸዋ መሳፍንት ተወላጅ የሆነውን ራስ ተሰማ ናደውን የራስ ቢትወደድነት ማዕረግ ሰጥቶ ለኢያሱ ሞግዚት አርጎ ሾመው። የትግሬና የሸዋን ንጉሣዊ ቤተሰቦች ለማስተሳሰር ይረዳል በሚል ስሜትም ኢያሱ የራስ መንገሻ ዮሐንስን የሰባት ዓመት ሕፃን ልጅ ሮማነወርቅን እንዲያገባ ተደርጎ ነበር። ጋብቻው ግን ለስሙ ነው እንጂ ለብዙ ቁም ነገር የበቃ አልነበረም። ሮማነወርቅ ለጣይቱም ዝምድና ስለነበራት ጋብቻው የንግሥቲቱንም ፍላጎት ለማርካት ተብሎ ሳይሆን አይቀርም።

ምኒልክ በታመመባቸው የመጀመሪያዎቹ ዓመታት የእቴጌ ጣይቱ ሥልጣን እያደገ መጥቶ ብዙዎቹን የሸዋ መኳንንት ሥጋት ላይ ጣላቸው። ወትሮውንም ቢሆን ጣይቱ ጠንካራ ገጸ ባሕርይ ያላትና በባሏ በምኒልክ ዘመነ መንግሥት ለተከናወኑት ዐበይት ተግባራት ግንባር ቀደም አስተዋፅኦ ማድረግ የቻለች ንግሥት ናት። የአዲስ አበባ ዋና መሥራች ጣይቱ ናት። የጣልያኖችን መሰሪነት ከማለዳው ተገንዝባ ኋላም የውጫሌን ውል በይፋ በማፍረስ ግንኙነቱን ለማቋረጥ ያመነታ የነበረውን ምኒልክን ያተጋቸው እሷው ነች። በዐድዋ ጦርነት ጊዜ የሠራዊቱን መንፈስ በማበረታታትም ሆነ የጦር መላ በመምታት የተጫወተችው ሚና ከትውልድ ትውልድ ሲተላለፍ የመጣ ወግ ሆኗል። እንዲህ ያለች ጠንካራ ሴት ንጉሠ ነገሥቱ በሕመም ከሥልጣን ሲገለል ከወትሮውም የበለጠ የጎላ ሚና እንደምትጫወት የሚጠበቅ ነው። በርግጥም ያልጋ ቁራኛ የሆነውን ባለቤቷን ወክላ በመሰለትና በሚስማማት መንገድ ሹም ሽር ማድረግ ጀመረች። የሹም ሽሩ ሰለባ ከሆኑትም መካከል የወሎጋው ገዥ ደጃች ደምስ፣ የዐድዋው ደጃች ገብረ ሥላሴ ባርያ ጋብር፣ ዋግ ሹም አባተ ቧ ያለውና ነጋድራስ ኃይለ ጊዮርጊስ ወልደ ሚካኤል ይገኙበታል። ኃይለ ጊዮርጊስ



ከመሸርም አልፎ የመንግሥት ገንዘብ አባክኗል ተብሎ በእግር ብረት እስከመታሰርም ደርሶ ነበር።



3.17 ልጅ ኢያሱ ከአባቱ ከራስ ሚካኤል ጋር

ይህ የጣይቱ እየገነነች መምጣት የሸዋን መኳንንት ክፉኛ አስደነገጠ። ትውልዷ ከጉንደር በመሆኑ የምትወስዳቸው እርምጃዎች በሙሉ ማዕከላዊነትን ያጣውን የሰሜኑን የኢትዮጵያ ክፍል በሸዋ ኪሳራ እንደገና ለመጠገን የሚደረግ ሆኖ ተተረጐመ። በተለይም ለእንዲህ ዓይነቱ ትርጓሜ ክብደት የሰጠው ጣይቱ የተካነችበት ቁልፍ የሆኑ የፖለቲካ ቤተ ሰቦችን በጋብቻ የማስተሳሰሩ ፖሊሲ ነበር። የፖለቲካ ጋብቻ ለኢትዮጵያ ታሪክ እንግዳ ነገር ባይሆንም እንደ ጣይቱ ከፍተኛ ደረጃ ያደረሰው ሰው የለም ተብሎ ይታመናል። እንዲህ ካመቻቸቻቸው ጋብቻ ምናልባት ዋነኛው የወንድሟ የራስ ወሌ ብጡል ልጅ የሆነው የራስ ጉግሣ ወሌና የዘውዲቱ ምኒልክ ጋብቻ ነው። በዚህም የተነሣ የጉግሣም ሆነ የራሷ የፖለቲካ እድል እንዲሠምር፣ ጣይቱ ለምኒልክ አልጋ ወራሽነት ያጨችው ኢያሱን ሳይሆን ዘውዲቱን ነበር።

በእቴጌይቱ ላይ የነበረው ማጉረምረም እየበረታ መጥቶ በየካቲት 1902 ይፋ ወጣ። ንግሥቲቱን ከሥልጣን ለማግለል የተቀነባበረ እድማ ተነሣ። ከበስተኋላ ሆነው እድማውን የሚያቀነባብሩት የጦር ሚኒስትሩ ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስና የሞግዚትነት ሥልጣኑ አደጋ ላይ የወደቀው ራስ ተሰማ ናደው ነበሩ። ተቃውሞውን በይፋ ይመሩ የነበሩት በጣይቱ የተገሸሙት እነ ደጃች

ጦር ሳይነሣበት በምቀኝነት እርስ በርሱ እንደተላለቀ አይታችኋል።

> አሁንም ልጆቼ ወዳጆቼ አንዱ ባንዱ ምቀኝነት ይቅር፣ ያንዱን አገር አንዱ እኔ እደርባለሁ እንዳትሉ። እኔ እስካሁን በፍቅር እንዳኖርኋችሁ እየንተም ተስማምታችሁ በፍቅር እንድትኖሩ እለምናችኋለሁ።
>
> እናንተ አንድ ልብ ከሆናችሁ በምቀኝነት እርስ በርሳችሁ ተዋግታችሁ ካላለቃችሁ በቀር አገራችንን ኢትዮጵያን ለሌላ ለባዕድ አትሰጧትም ክፉም ነገር አገራችንን አያገኛትም።
>
> ይህንን ምክር ለናንተ መስጠቱ እኔማ በእግዚአብሔር ቸርነት ይህንን ያህል ዘመን ገዝቼ የለምን። ነገር ግን ሰው ነኝና እንግዲህ እስንት ያህል ዘመን እቆያለሁ ስል ነው።
>
> አሁንም እኔ እንደተመኘሁት እግዚአብሔር የተጨመረበትና ፈቃዱ ሁኖ ልጄን (የልጅ ልጄን ኢያሱን ለማለት ነው) ቢአቆምላችሁ ከልጄ ጋር ሁናችሁ አገራችሁን ጠብቁ አደራ ብያችኋለሁ። (አፈወርቅ፣ 113-115)

አልጋ ወራሹ ገና ለአካለ መጠን ያልደረሰ ጮርቃ በመሆኑም የሸዋ መሳፍንት ተወላጅ የሆነውን ራስ ተሰማ ናደውን የራስ ቢትወደድነት ማዕረግ ሰጥቶ ለኢያሱ ሞግዚት አርጎ ሾመው። የትግሬና የሸዋን ንጉሣዊ ቤተሰቦች ለማስተሳሰር ይረዳል በሚል ስሜትም ኢያሱ የራስ መንገሻ ዮሐንስን የሰባት ዓመት ሕፃን ልጅ ሮማነወርቅን እንዲያገባ ተደርጎ ነበር። ጋብቻው ግን ለስሙ ነው እንጂ ለብዙ ቁም ነገር የበቃ አልነበረም። ሮማነወርቅ ለጣይቱም ዝምድና ስለነበራት ጋብቻው የንግሥቲቱንም ፍላጎት ለማርካት ተብሎ ሳይሆን አይቀርም።

ምኒልክ በታመመባቸው የመጀመሪያዎቹ ዓመታት የእቴጌ ጣይቱ ሥልጣን እያደገ መጥቶ ብዙዎቹን የሸዋ መኳንንት ሥጋት ላይ ጣላቸው። ወትሮውንም ቢሆን ጣይቱ ጠንካራ ገጸ ባሕርይ ያላትና በባሏ በምኒልክ ዘመነ መንግሥት ለተከናወኑት ዐበይት ተግባራት ግንባር ቀደም አስተዋፅኦ ማድረግ የቻለች ንግሥት ናት። የአዲስ አበባ ዋና መሥራች ጣይቱ ናት። የጣልያኖችን መሰሪነት ከማስዳው ተገንዝባ ኋላም የውጫሌን ውል በይፋ በማፍረስ ግንኙነቱን ለማቋረጥ ያመነታ የነበረውን ምኒልክን ያተጋችው እሷው ነች። በዐድዋ ጦርነት ጊዜ የሠራዊቱን መንፈስ በማበረታታትም ሆነ የጦር መላ በመምታት የተጫወተችው ሚና ከትውልድ ትውልድ ሲተላለፍ የመጣ ወግ ሆኗል። እንዲህ ያለች ጠንካራ ሴት ንጉሠ ነገሥቱ በሕመም ከሥልጣን ሲገለል ከወትሮውም የበለጠ የጎላ ሚና እንደምትጫወት የሚጠበቅ ነው። በርግጥም ያልጋ ቁራኛ የሆነውን ባለቤቷን ወክላ በመለሳትና በሚስማማት መንገድ ሹም ሽር ማድረግ ጀመረች። የሹም ሽሩ ሰለባ ከሆኑትም መካከል የወለጋው ገዥ ደጃች ደምስ፣ የዐድዋው ደጃች ገብረ ሥላሴ ባርያ ጋብር፣ ዋግ ሹም አባተ ቧ ያለውና ነጋድራስ ኃይለ ጊዮርጊስ ወልደ ሚካኤል ይገኙበታል። ኃይለ ጊዮርጊስ



ከመሻርም አልፎ የመንግሥት ገንዘብ አባክኗል ተብሎ በእግር ብረት እስከመታሰርም ደርሶ ነበር።



3.17 ልጅ ኢያሱ ከአባቱ ከራስ ሚካኤል ጋር

ይህ የጣይቱ እየገነነች መምጣት የሸዋን መኳንንት ክፉኛ አስደነገጠ። ትውልዷ ከጐንደር በመሆኑ የምትወስዳቸው እርምጃዎች በሙሉ ማዕከላዊነትን የጣውን የሰሜኑን የኢትዮጵያ ክፍል በሸዋ ኪሳራ እንደገና ለመጠገን የሚደረግ ሆኖ ተተረጐመ። በተለይም ለእንዲህ ዓይነቱ ትርጓሜ ክብደት የሰጠው ጣይቱ የተካነችበት ቁልፍ የሆኑ የፖለቲካ ቤተ ሰቦችን በጋብቻ የማስተሳሰሩ ፖሊሲ ነበር። የፖለቲካ ጋብቻ ለኢትዮጵያ ታሪክ እንግዳ ነገር ባይሆንም እንደ ጣይቱ ከፍተኛ ደረጃ ያደረሰው ሰው የለም ተብሎ ይታመናል። እንዲህ ካመቻቸቻቸው ጋብቻ ምናልባት ዋነኛው የወንድሟ የራስ ወሌ ብጡል ልጅ የሆነው የራስ ጉግሣ ወሌና የዘውዲቱ ምኒልክ ጋብቻ ነው። በዚህም የተነሣ የጉግሣም ሆነ የራሷ የፖለቲካ እድል እንዲሠምር፣ ጣይቱ ለምኒልክ አልጋ ወራሽነት ያጨችው ኢያሱን ሳይሆን ዘውዲቱን ነበር።

በእቴጌይቱ ላይ የነበረው ማጉረምረም እየበረታ መጥቶ በየካቲት 1902 ይፋ ወጣ። ንግሥቲቱን ከሥልጣን ለማግለል የተቀነባበረ አድማ ተነሣ። ከበስተኋላ ሆነው አድማውን የሚያቀነባብሩት የጦር ሚኒስትሩ ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስና የሞግዚትነት ሥልጣኑ አደጋ ላይ የወደቀው ራስ ተሰማ ናደው ነበሩ። ተቃውሞውን በይፋ ይመሩ የነበሩት በጣይቱ የተጎሸሙት እነ ደጃች

ደምስ፣ ደጃች ገብረ ሥላሴና ቀኛዝማች ወሰኔ ትርፌ ነበሩ:: ለተቃውሞው ሰፋ ያለ ሕዝባዊ መልክ የሰጠው ደግሞ መሀል ሰፋሪ እየተባለ ይጠራ የነበረው



3.18 እቴጌ ጣይቱ ብጡል

የንጉሡ ነገሥቱ ጦር ተሳትፎ ነው:: ይህ ጦር በከፊል የመደበኛ ጦርነት ባሕርይ ከመያዙም በላይ በቤተ መንግሥት አካባቢ የተመደበ በመሆኑም በፖለቲካ ውስጥ የመግባት ዝንባሌ ነበረው:: በ20ኛው መቶ ዓመት መጀመሪያ ላይ በተከሠቱት የፖለቲካ ውዝግቦች ውስጥ ካንዴም ሁለቴ በመሳተፍ ወሳኝ ሚና ለመጫወት ችሏል::

በዘመኑ የፖለቲካ ውዝግቦች ይታይ የነበረው ሌላ ተደጋጋሚ ሁኔታ ደግሞ የእቡኑ የዳኝነትና የገላጋይነት ሚና ነው:: የእቴጌይቱ ባላጋራዎች እቴጌይቱን ከሥልጣን ለማግለል በሚያደርጉት ጥረት የአቡን ማቴዎስን ቡራኬ ለማግኘት ሲሉ ተከለ ሃይማኖት አደባባይ ተሰብስበው ያሳለፉትን ውሳኔ (ማለትም ጣይቱ ከሥልጣን ተገልላ ባሏን በማስታመም ብቻ እንድትወሰን የሚለውን) በአቡኑ በኩል ለማስተላለፍ ሞከሩ:: ሆኖም ጣይቱ የአቡኑን ሽምግልና በበጎ ዐይን አልተመለከተችውም:: በበኩሏ ለአዲስ አበባ አድባራትና ለውጭ አገር ሌጋሲዮኖች የስሞታ ደብዳቤ ጽፋ እርዳታቸውን ተማጠነች:: ለአድባራቱ በጻፈችው ደብዳቤ እሷ ውድ ባለቤቷን ለማስታመም ቀና ደፋ ስትል ቤተ ክርስቲያን የምትስምበት ጊዜ እንኳን አጥታ እያለ፣ አድመኞች እንዴት



እንደተነሡባት ስተዛዝና ገለጸች:: ለሌጋሲዮኖች የጻፈችው ደብዳቤም ረቂቅ ዲፕሎማሲን የተንተራሰ ነበር:: ለምሳሌ ለእንግሊዙ ሚኒስትር የጻፈችው ይህን ይመስል ነበር፣



3.19 ደጃች ገብረ ሥላሴ ባርያ ጋብር፣ የዐድዋ ገዥ

> እኔም በመሬቱም በምኑም ብንጣላ ለሀገሬ ስል ነው እንጂ እናንተን ለማስቀየም አይደለም:: ይህንንም አገሬን መውደዱን እናንተም አትጠሉትም:: ነገር ግን አሁን ንጉሡ ሲታመሙ ጊዜ ሕዝቡ እመንግሥት ሥራ አይግቡብን ብሎ ለአቡኑ ማቴዎስ ላከብኝ:: እኔም እሺ አልገባም ሽኝታችሁ አገሬን ስደዱኝ ብዬ ወደ ሕዝቡ ልኬአለሁ:: ይህም ደንብ በናንተም በአውሮፓ አገር ያለ ነው:: መንግሥቱን ሲለቅ ወደ አርስቱ መሄድ:: እንስድም ያሉኝ እንደሆነ ግን ለመንግሥትህ አስታውቅልኝ:: እንደ አውሮፓ ሥርዓት እናድራለን ብለዋል:: ይህ ከአውሮፓ ሥርዓት የወጣ ነው:: (መርስዔ ኃዘን፣ ምኒልክ፣ 56)

ደምስ፣ ደጃች ገብረ ሥላሴና ቀኛዝማች ወሰኔ ትርፌ ነበሩ:: ለተቃውሞው ሰፋ ያለ ሕዝባዊ መልክ የሰጠው ደግሞ መሀል ሰፋሪ እየተባለ ይጠራ የነበረው



3.18 እቴጌ ጣይቱ ብጡል

የንጉሠ ነገሥቱ ጦር ተሳትፎ ነው:: ይህ ጦር በከፊል የመደበኛ ጦርነት ባሕርይ ከመያዙም በላይ በቤተ መንግሥት አካባቢ የተመደበ በመሆኑም በፖለቲካ ውስጥ የመግባት ዝንባሌ ነበረው:: በ20ኛው መቶ ዓመት መጀመሪያ ላይ በተከሠቱት የፖለቲካ ውዝግቦች ውስጥ ካንዴም ሁለቴ በመሳተፍ ወሳኝ ሚና ለመጫወት ችሏል::

በዘመኑ የፖለቲካ ውዝግቦች ይታይ የነበረው ሌላ ተደጋጋሚ ሁኔታ ደግሞ የአቡኑ የዳኝነትና የገላጋይነት ሚና ነው:: የእቴጌይቱ ባላጋራዎች እቴጌይቱን ከሥልጣን ለማግለል በሚያደርጉት ጥረት የአቡነ ማቴዎስን ቡራኬ ለማግኘት ሲሉ ተክለ ሃይማኖት አደባባይ ተሰብስበው ያሳለፉትን ውሳኔ (ማለትም ጣይቱ ከሥልጣን ተገልላ ባሏን በማስታመም ብቻ እንድትወሰን የሚለውን) በአቡኑ በኩል ለማስተላለፍ ሞከሩ:: ሆኖም ጣይቱ የአቡኑን ሽምግልና በበጎ ዐይን አልተመለከተችውም:: በበኩሏ ለአዲስ አበባ አድባራትና ለውጭ አገር ሌጋሲዮኖች የስሞታ ደብዳቤ ጽፋ እርዳታቸውን ተማጠነች:: ለአድባራቱ በጻፈችው ደብዳቤ እሷ ውድ ባለቤቷን ለማስታመም ቀና ደፋ ስትል ቤተ ክርስቲያን የምትስምበት ጊዜ እንኳን አጥታ እያለ፣ አድመኞች እንዴት



እንደተነሡባት ስተዛዝና ገለጸች:: ለሌጋሲዮኖች የጻፈችው ደብዳቤም ረቂቅ ዲፕሎማሲን የተንተራሰ ነበር:: ለምሳሌ ለእንግሊዙ ሚኒስትር የጻፈችው ይህን ይመስል ነበር፤



3.19 ደጃች ገብረ ሥላሴ ባርያ ጋብር፣ የዐድዋ ገዥ

> እኔም በመሬቱም በምንም ብንጣላ ለሀገሬ ስል ነው እንጂ እናንተን ለማስቀየም አይደለም:: ይህንንም አገሬን መውደዴን እናንተም አትጠሉትም:: ነገር ግን አሁን ንጉሡ ሲታመሙ ጊዜ ሕዝቡ እመንግሥት ሥራ አይግቡብን ብሎ ለአቡነ ማቴዎስ ላከብኝ:: እኔም እሺ አልገባም ሸኙታችሁ አገሬን ስደዱኝ ብዬ ወደ ሕዝቡ ልኬአለሁ:: ይህም ደንብ በናንተም በአውሮፖ አገር ያለ ነው:: መንግሥቱን ሲለቅ ወደ እርስቱ መሄድ:: እንሰድም ያሉኝ እንደሆነ ግን ለመንግሥትህ አስታውቅልኝ:: እንደ አውሮፖ ሥርዓት እናድራለን ብለዋል:: ይህ ከአውሮፖ ሥርዓት የወጣ ነው:: (መርስዔ ኃዘን፣ ምኒልክ፣ 56)



3.20 አቡነ ማቴዎስ፣ ለ38 ዓመታት የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት

ምንም እንኳን ጣይቱ ለሌጋሲዮኖች የላከችው አቤቱታ እንዲህ በዲፕሎማሲያዊ ቋንቋ የተቀመመ ቢሆንም ዞሮ ዞሮ ብዙም አልበጃትም። ሌጋሲዮኖቹ በውስጥ ጉዳይ ጣልቃ አንገባም ብለው ሲመልሱ ባላጋራዎቿ ደግሞ «ይኸው ባዕድ መንግሥታት ባገራችን ጉዳይ ገብተው እንዲዳኙ ጋበዘች» ብለው ሌላ ወንጀል አገኙባት። በመጨረሻ ጣይቱ ተሸንፋ ቤተ መንግሥቱን ለቃ ወደምትወደው ወደ እንጦጦ ማርያም ቤተ ክርስቲያን እንድትሄድና በዚያ በግዞት መልክ ማለት ይቻላል እስከ ሞተችበት 1910 ድረስ እንድትቆይ ተገደደች።

ከዚያ በኋላ የቀረው የሠራችውን ማፍረስ፣ የሻረችውን መመለስ ነው። በዚህ ረገድ ከዋና ተጠቃሚዎቹ አንዱ በጣይቱ ዘመን ተግዞ የነበረው አሁን ግን ራስ ተብሎ አርሲና ከምባታ ላይ የተሾመው ዋግሹም አባተ ቧያለው ነው። ለጣይቱ ተቆርቋሪው ያንገራገሩትም ብዙ ሊገፉበት አልቻሉም። የዘመዷ የደጃች እያሌው ብሩ አመፅ በቀላሉ ተቀጨ። የወንድሟ ልጅና ዙፋኑን ተልማለት የነበረው ጉግሣ ወሌ እግር ጥሎት አጉል ጊዜ አዲስ አበባ ተገኘ። ባላጋራዎቿም ይህን አጋጣሚ ተጠቅመው በሌላ ነገር ወንጀለውት አሠሩት። በቦታውም የከፋ ገዥ የነበረው ራስ ወልደ ጊዮርጊስ አቦዬ የበጌምድር ገዥ ሆኖ ተሾመ። ብርቱ ተቃውሞ የተጠበቀው የየጁ ገዥ ከነበረውና በሠራዊቱ ብርታት ከታወቀው ከጣይቱ ወንድም ከራስ ወሌ ብጡል ነበር። በርግጥም በራስ ወሌና የኢያሱ አባት ስለሆነም የጣይቱ ተፃራሪ በነበረው በወሎው ራስ ሚካኤል መካከል ለተወሰነ ጊዜ አደገኛ ፍጥጫ ነበር። ውትሮም በድንበር ይጋጩ የነበሩት ሁለቱ



ንጋፉ የምኒልክ አዝማቾች አሁን ደግሞ የሥልጣን ትግል ታክሎበት ከከባድ ደም መፋሰስ አፋፍ ደርሰው ነበር። እንደራሴው ራስ ተሰማም ለሚካኤል አጋር ሚሆን ዐሥር ሺ ጦር በደጃች ልዑልሰገድ አጥናፍሰገድ አዝማችነት ልኮ ነበር። ያኖም ጣይቱ በነራስ ተሰማ ጉትጎታ ይመስላል ለሁለቱ ባላንጣዎች በጻፈችው ልብ የሚነካ ደብዳቤ አማካይነት ጠቡን ለማብረድ ችላለች። ይህም የእቴጌይቱ የመጨረሻ በጎ የፖለቲካ ተግባር ሆነ። ለወንድሟ ግን ብዙም አልበጀውም። ከ1903 መጀመሪያ ላይ አዲስ አበባ መጥቶ እጁን ቢሰጥም የተረፈው ከምህረትና አርቅ ይልቅ እሥራት ነበር። እስከ ሰገሌ ጦርነት (1909) ድረስም አንኮበር በእስር ቆየ።

## ዘመነ ኢያሱ

ጣይቱ ከሥልጣን ስትገለል፣ ለወጣቱ አልጋ ወራሽ ለኢያሱ በሱና በዙፋኑ መካከል አንድ ትልቅ መሰናክል ተወገደ ማለት ነው። ባመቱ ሚያዝያ 1903 እንደራሴው ቢትወደድ ራስ ተሰማ ሲሞት ደግሞ ወጣቱን ልዑል ሃይ የሚለው ጠፋ። ሙሉ ሥልጣን ከመጨበጥ ያገደው እየመነመነ የሄደው ግን አልሞት ብሎ ያስቸገረው የምኒልክ ገላ ብቻ ሆነ። ምኒልክ የመጨረሻ ትንፋሹን እስኪተነፍስ ገና ሁለት ዓመት መቆየት ነበረበት። ይሁን እንጂ ኢያሱ ንጉሠ ነገሥት ባይባልም የሥልጣን ዘመኑ ከ1903 እስከ 1909 ነው።

ገና በጅምሩ ግን ካልተጠበቀ አቅጣጫ የኢያሱን ሥልጣን የሚቀናቀን ኃይል መጣ። ከጣይቱ ውድቀት በኋላ በድል አድራጊነት ስሜት ወደ ተከለከለባት ወደ አዲስ አበባ የመጣው ራስ አባተ ዙፋኑን ለመጨበጥ ያሰባል የሚል ወሬ ተናኘ። ይህንንም ለማድረግ ባንድ ወገን ራስ ተሰማን የሚተካ እሱ የሚመራው የሞግዚቶች ጉባኤ የማቋቋም ሐሳብ አለው ሲባል፣ በሌላ በኩል ደግሞ ዘውዲቱን አግብቶ እሷ ስትነግሥ በሷ ስም ለመግዛት ይሻል የሚልም ሐሜት ነበር። ነገሩ የፈነዳው ቤተ መንግሥት ያለውን መሣሪያ ለመያዝ ወደዚያው ለመግባት ሲሞክር ነው። በፊታውራሪ ገብረ ማርያም የሚመሩት የግቢ ዘበኞች አናስገባም ብለው ከፍተኛ ውጥረት ከተፈጠረ በኋላ፣ አቡኑና እጨጌው በመሀል ሲገቡ ነው ደም ሳይፈስ ነገሩ የበረደውና አባተም ወደ ግዛቱ ወደ ከምባታ ሲመለስ የተስማማው። ለኢያሱ አባት ለራስ ሚካኤል ግን ይህ በቂ አልነበረም። የልጁን ሕጋዊ ሥልጣን ተቀናቃኝ እየበዛበት ቢያስቸግረው ይህን ችግር ሳንዴም ለሁሌም ልፍታው ብሎ ይመስላል ስምንት ሺ ሠራዊት እየመራ አዲስ አበባ መጣ። ከዚያም አባተን ከከምባታ አስጠርቶ እስከ ሰገሌ ጦርነት በመቅደላ ታስሮ እንዲቆይ አደረገው።

በዚህ ሁሉ መሀል ፊት ለፊት ከመጋፈጥ ማድፈጥን የመረጠው የፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ አቋም እየተጠናከረ መጣ። አባተ ያጣውን ከምባታን ከመደረቡም በላይ የሸዋ መኳንንት መሪ ሆኖ ብቅ አለ። የኢያሱ አመራር መኳንንቱን ሥጋት ላይ በጣለበት ወቅትም መጀመሪያ የኢያሱን ከሥልጣን መውረድ በማስተባበር፣ ኋላም አባቱ ራስ ሚካኤል ልጁን ወደ ሥልጣን ለመመለስ ያደረገውን ሙከራ ሰገሌ ላይ በማክሸፍ ቁልፍ ሚና ሲጫወት እናገኘዋለን።



3.20 አቡነ ማቴዎስ፣ ለ38 ዓመታት የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት

ምንም እንኳን ጣይቱ ለሌጋሲዮኖች የላከችው አቤቱታ እንዲህ በዲፕሎማሲያዊ ቋንቋ የተቀመመ ቢሆንም ዞሮ ዞሮ ብዙም አልበጃትም። ሌጋሲዮኖቹ በውስጥ ጉዳይ ጣልቃ አንገባም ብለው ሲመልሱ ባላጋራዎቿ ደግሞ «ይኸው ባዕድ መንግሥታት ባገራችን ጉዳይ ገብተው እንዲዳኙ ጋበዘች» ብለው ሌላ ወንጀል አገኙባት። በመጨረሻ ጣይቱ ተሸንፋ ቤተ መንግሥቱን ለቃ ወደምትወደው ወደ እንጦጦ ማርያም ቤተ ክርስቲያን እንድትሄድና በዚያ በግዞት መልክ ማለት ይቻላል እስከ ሞተችበት 1910 ድረስ እንድትቆይ ተገደደች።

ከዚያ በኋላ የቀረው የሠራችውን ማፍረስ፣ የሻረችውን መመለስ ነው። በዚህ ረገድ ከዋና ተጠቃሚዎቹ አንዱ በጣይቱ ዘመን ተግዞ የነበረው አሁን ግን ራስ ተብሎ አርሲና ከምባታ ላይ የተሾመው ዋግሹም አባተ ቧያለው ነው። ለጣይቱ ተቆርቋሪው ያንገራገሩትም ብዙ ሊገፉበት አልቻሉም። የዘመዷ የደጃች አያሌው ብሩ አመፅ በቀላሉ ተቀጨ። የወንድሟ ልጅና ዙፋኑን ተልማለት የነበረው ጉግሣ ወሌ እግር ጥሎት አጉል ጊዜ አዲስ አበባ ተገኘ። ባላጋራዎቿም ይህን አጋጣሚ ተጠቅመው በሌላ ነገር ወንጅለውት አሠሩት። በቦታውም የከፋ ገዥ የነበረው ራስ ወልደ ጊዮርጊስ አቦዬ የበጌምድር ገዥ ሆኖ ተሾመ። ብርቱ ተቃውሞ የተጠበቀው የየጁ ገዥ ከነበረውና በሠራዊቱ ብርታት ከታወቀው ከጣይቱ ወንድም ከራስ ወሌ ብጡል ነበር። በርግጥም በራስ ወሌና የኢያሱ አባት ስለሆነም የጣይቱ ተፃራሪ በነበረው በወሎው ራስ ሚካኤል መካከል ለተወሰነ ጊዜ አደገኛ ፍጥጫ ነበር። ወትሮም በድንበር ይጋጩ የነበሩት ሁለቱ



አንጋፋ የምኒልክ አዝማቾች አሁን ደግሞ የሥልጣን ትግል ታክሎበት ከከባድ የደም መፋሰስ አፋፍ ደርሰው ነበር። እንደራሴው ራስ ተሰማም ለሚካኤል አጋር የሚሆን ዐሥር ሺ ጦር በደጃች ልዑልሰገድ አጥናፍሰገድ አዝማችነት ልኮ ነበር። ሆኖም ጣይቱ በነራስ ተሰማ ጉትጎታ ይመስላል ለሁለቱ ባላንጣዎች በጻፈችው ልብ የሚነካ ደብዳቤ አማካይነት ጠቡን ለማብረድ ችላለች። ይህም የእቴጌይቱ የመጨረሻ በጎ የፖለቲካ ተግባር ሆነ። ለወንድሟ ግን ብዙም አልበጀውም። በ1903 መጀመሪያ ላይ አዲስ አበባ መጥቶ እጁን ቢሰጥም የተረፈው ከምህረትና እርቅ ይልቅ እሥራት ነበር። እስከ ሰገሌ ጦርነት (1909) ድረስም አንኮበር በእስር ቆየ።

## ዘመነ ኢያሱ

ጣይቱ ከሥልጣን ስትገለል፣ ለወጣቱ አልጋ ወራሽ ለኢያሱ በሱና በዙፋኑ መካከል አንድ ትልቅ መሰናክል ተወገደ ማለት ነው። ባመቱ ሚያዝያ 1903 እንደራሴው ቢትወደድ ራስ ተሰማ ሲሞት ደግሞ ወጣቱን ልዑል ሃይ የሚለው ጠፋ። ሙሉ ሥልጣን ከመጨበጥ ያገደው እየመነመነ የሄደው ግን አልሞት ብሎ ያስቸገረው የምኒልክ ገላ ብቻ ሆነ። ምኒልክ የመጨረሻ ትንፋሹን እስኪተነፍስ ገና ሁለት ዓመት መቆየት ነበረበት። ይሁን እንጂ ኢያሱ ንጉሠ ነገሥት ባይባልም የሥልጣን ዘመኑ ከ1903 እስከ 1909 ነው።

ገና በጅምሩ ግን ካልተጠበቀ አቅጣጫ የኢያሱን ሥልጣን የሚቀናቀን ኃይል መጣ። ከጣይቱ ውድቀት በኋላ በድል አድራጊነት ስሜት ወደ ተከለከለባት ወደ አዲስ አበባ የመጣው ራስ አባተ ዙፋኑን ለመጨበጥ ያስባል የሚል ወሬ ተናኘ። ይህንንም ለማድረግ ባንድ ወገን ራስ ተሰማን የሚተካ እሱ የሚመራው የሞግዚቶች ጉባኤ የማቋቋም ሐሳብ አለው ሲባል፣ በሌላ በኩል ደግሞ ዘውዲቱን አግብቶ እሷ ስትነግሥ በሷ ስም ለመግዛት ይሻል የሚልም ሐሜት ነበር። ነገሩ የፈነዳው ቤተ መንግሥት ያለውን መሣሪያ ለመያዝ ወደዚያው ለመግባት ሲሞክር ነው። በፊታውራሪ ገብረ ማርያም የሚመሩት የግቢ ዘበኞች አናስገባም ብለው ከፍተኛ ውጥረት ከተፈጠረ በኋላ፣ አቡኑና እጨጌው በመሀል ሲገቡ ነው ደም ሳይፈስ ነገሩ የበረደውና አባተም ወደ ግዛቱ ወደ ከምባታ ሲመለስ የተስማማው። ለኢያሱ አባት ለራስ ሚካኤል ግን ይህ በቂ አልነበረም። የልጁን ሕጋዊ ሥልጣን ተቀናቃኝ እየበዛበት ቢያስቸግረው ይህን ችግር ሳንዴም ለሁሌም ልፍታው ብሎ ይመስላል ስምንት ሺ ሠራዊት እየመራ አዲስ አበባ መጣ። ከዚያም አባተን ከከምባታ አስጠርቶ እስከ ሰገሌ ጦርነት በመቅደላ ታስሮ እንዲቆይ አደረገው።

በዚህ ሁሉ መሀል ፊት ለፊት ከመጋፈጥ ማድፈጥን የመረጠው የፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ አቋም እየተጠናከረ መጣ። አባተ ያጣውን ከምባታን ከመደረቡም በላይ የሸዋ መኳንንት መሪ ሆኖ ብቅ አለ። የኢያሱ አመራር መኳንንቱን ሥጋት ላይ በጣለበት ወቅትም መጀመሪያ የኢያሱን ከሥልጣን መውረድ በማስተባበር፣ ኋላም አባቱ ራስ ሚካኤል ልጁን ወደ ሥልጣን ለመመለስ ያደረገውን ሙከራ ሰገሌ ላይ በማክሸፍ ቁልፍ ሚና ሲጫወት እናገኘዋለን።

የኢያሱ ዘመነ መንግሥት በእንቆቅልሽ የተመላ ዘመን ነው። አፍ ሞልቶ በክፉም በበጎ ማውሳቱ ያዳግታልና። እድሉ ሆኖ የኢያሱ ዘመን አጭር ከመሆኑም በላይ ከሱ በኋላ ሥልጣን የጨበጠው ተፈሪ በተቃራኒው ለረጅም ዘመን ኢትዮጵያን ከመግዛቱም በላይ ባላንጣው ኢያሱ በደግ እንዲነሣ የማይሻ ነበር። ስለሆነም በአያሌ የታሪክ መጻሕፍት ተደጋግሞ የሚወሳው የኢያሱ መስለምና አገር የማስለም ሙከራ፣ ቧልትና ጨዋታ መውደዱና፣ የማይበርድ የፍትወት ስሜቱ ነው። ባንጻሩ በዘመኑ ያከናወናቸው በጎ ተግባራት መጠቀሳቸው ቀርቶ መታወቃቸውም ያጠራጥራል። ከመጻሕፍቱ ይልቅ ፊደል ያልቆጠረው ሕዝብ ለኢያሱ አዎንታዊ አመለካከት አለው። መልከ ቀናነቱ፣ የንግግር ችሎታው፣ እስፖርተኛነቱ፣ ይህ ሁሉ የሕዝብን ሕሊና የሚማርክ ነበር። በመንግሥት ሥራ ላይ በዋል ፈሰስ ቢመስልም ከእድሜ ለጋነት የመጣ ነው ብሎ ሕዝቡ ሊፈርድለት ዝግጁ ነበር።

ኢያሱ በአጭር የሥልጣን ዘመኑ ማኅበራዊና ኤኮኖሚያዊ አለኝታን በማጠናከራቸው ተራማጅ ሊባሉ የሚችሉ አንዳንድ እርምጃዎችን ወስዷል። ላይ ከተጠቀሰው የግል ንብረትን የማስከበርና ዐሥራትን በወቅቱ የመሰብሰብ ደንብ በተጨማሪ፣ ከሳሽና ተከሳሽ አብረው እንዲማቅቁ ያደርግ የነበረውን የቁራኛ ሥርዓት ለመሻር እርምጃ ወስዷል። እንዲሁም ከፍትሕ ይልቅ ለቂም መወጫና ደካማ ማጥቂያነት የሚያገለግለውን የሌባ ሻይ ሥርዓት መልክ ለማስያዝ ሞክሯል። የመንግሥት ሒሳብ ኦዲት በማስደረግ አላግባብ የመንግሥት ገንዘብ ባባከኑት ላይ እርምጃ በመውሰድም ኢያሱ የመጀመሪያው የኢትዮጵያ መሪ ሳይሆን አይቀርም። የሚያሳዝነው ግን አንዳንዴ በዚሁ ሳቢያ የጠላውን ሰው በሐሰት እያስወነጀለ ማሰሩ ነው። በመሠረቱ የኢያሱ ገጽ ባሕርይም ሆነ ፖሊሲዎች መለዮ ውስጠ ተቃርኖና ቀጣይነት ማጣት ነበር። ባንድ ወገን የተጠቃ እንባ አድራቂ ሆኖ የጂሌ ኦሮሞን ሕዝብ በዘረፉት በአፋሮች ላይ ሲዘምት እናየዋለን። በዚያው ዓመት ደግሞ ለዘለዓለም በስሙ ላይ ጥቁር ነጥብ የጣለውን የጊሚራ ዘመቻ ሲመራና እልፍ አእላፍ ዜጎቹን ለባርነትና ሞት ሲዳርግ እናገኘዋለን። «ጥርንቡሌ» የተባለውን የከተማ ዘበኛ ያቋቋመው አርቆ አሳቢ መሪ ሰዓት እላፊ እየጣሰ ከነሱው ጋር ሲታኩስ ይገኛል።

ይህ ሁሉ እንደ ዋዛ በታለፈ ነበር። ለኢያሱ መጥፊያው የሆነው በጊሚራ ላይ መዝመቱ ወይ ከጥርንቡሌ ጋር መታኮሱ ሳይሆን ከዐድዋ በኋላ የተደላደለውን ፖለቲካዊና ዲፕሎማሲያዊ ስምምነት ማናጋቱ ነው። በምኒልክ ዘመን ግርማና ሞገስ ያገኙት መኳንንትማ ቀሌያቸው ነው የተገፈፈው። ንጉሣቸውን አጅበው አገር መዞሩን እንደ ትልቅ ወግ የሚቆጥሩትን እነዚህን መኳንንት አርፈው እንዲቀመጡ በሚከተሉት ቅስም ሰባሪ ቃላት አገዳቸው፤

> እኔ ጎልማሶችን አስከትዬ አገር ለመጉብኘትና
> ያልቀናውን አገር ለማቅናት በተነሣሁ ጊዜ ያለፈቃዴ
> መከተል የለባችሁም። ወፍራችኋል፣ ሸምግላችኋል።
> በዘመናችሁ አባቴን ተከትላችሁ አገር አቅንታችኋል።
> አሁን ግን ሽሽታችሁ አታመልጡም፣አባራችሁ
> አትጨብጡምና ተመልሳችሁ በየሥራችሁ ጠንክሩ።
> (መርስዔ ኀዘን፣ «ምኒልክ»፣ 103)





3.21 ከሳሽና ተከሳሽ አብሮ የሚታገትበት የቁራኛ ሥርዓት

በቀና ትርጓሜ ኢያሱ የሚለው እናንት በተራችሁ ሠርታችኋል፤ አሁን ደግሞ ዘመናዊት ኢትዮጵያን የመገንባቱ ተራ የኛ የወጣቶቹ ነው ማለቱ ነው ሊባል ይችል ይሆናል። መኳንንቱ ግን በዚህ መልክ አላዩለትም። ያውም ይኸ ለስለስ ባለ አንደበት በይፋ ተናገረ የሚባለው ነው። በሌላ ወቅት ግን «የአባቴ ሙከቶች» እያለ ያፌዝባቸው እንደነበር ይነገራል።

ኢያሱ ትዕግሥት ያጣው በመኳንንቱ ላይ ብቻ ሳይሆን በራሱ በምኒልክም ይመስላል። የንጉሠ ነገሥቱ በሞትና ሕይወት መካከል ተንጠልጥሎ መቆየት የኢያሱን የፖለቲካ እድልም እንዲሁ በእንጥልጥል እንዲቀር አደረገው። በ1905 አጋማሽ ላይ በኢያሱና በግቢ ዘበኞች መካከል የተፈጠረው ግጭት መንሥኤም ይኸው የኢያሱ ትዕግሥት ማጣት ይመስላል። ከምኒልክ ሌላ ጌታ የማያውቁት ዘበኞች ቀደም ሲል ራስ አባተን ግቢ አናስገባም እንዳሉ ሁሉ፣ አሁንም ኢያሱ ምኒልክን ወደ እንኰበር ለማስወሰድ ሐሳብ አለው ማለትን ሰምተው እኛ ሳንሞት ንጉሣችን ከግቢ አይወጡም ብለው በኢያሱ ላይ በሩን ዘጉበት። ኢያሱም ግቢውን ከቦ ዘበኞቹ ከውጭ ምንም ስንቅ እንዳያገኙ አደረገ። አምስት ሰዓት የቆየ ተኩስም ተከፍቶ አሥራ ሰባት ያህል ሰዎች ሞቱ። በመጨረሻ አቡነ ማቴዎስ በነገሩ ገብተው ዘበኞቹ እጃቸውን እንዲሰጡ ተደረጉ። መሪያቸው ፊታውራሪ ገብረ ማርያም በጌምድር፣ ሌሎቹ ሹማምንት ደግሞ

የኢያሱ ዘመነ መንግሥት በእንቆቅልሽ የተመላ ዘመን ነው:: አፍ ሞልቶ በክፉም በበጎ ማውሳቱ ያዳግታልና:: እድሉ ሆኖ የኢያሱ ዘመን አጭር ከመሆኑም በላይ ከሱ በኋላ ሥልጣን የጨበጠው ተፈሪ በተቃራኒው ለረጅም ዘመን ኢትዮጵያን ከመግዛቱም በላይ ባሳንጣው ኢያሱ በደግ እንዲነሣ የማይሻ ነበር:: ስለሆነም በአያሌ የታሪክ መጻሕፍት ተደጋግሞ የሚወሳው የኢያሱ መስለምና አገር የማስለም ሙከራ፣ ቧልትና ጨዋታ መውደዱና፣ የማይበርድ የፍትወት ስሜቱ ነው:: ባንፃሩ በዘመኑ ያከናወናቸው በጎ ተግባራት መጠቀሳቸው ቀርቶ መታወቃቸውም ያጠራጥራል:: ከመጻሕፍቱ ይልቅ ፊደል ያልቆጠረው ሕዝብ ለኢያሱ አዎንታዊ አመለካከት አለው:: መልከ ቀናነቱ፣ የንግግር ችሎታው፣ እስፖርተኛነቱ፣ ይህ ሁሉ የሕዝብን ሕሊና የሚማርክ ነበር:: በመንግሥት ሥራ ላይ በዋል ፈሰስ ቢመስልም ከእድሜ ለጋነት የመጣ ነው ብሉ ሕዝቡ ሲፈርድለት ዝግጁ ነበር::

ኢያሱ በአጭር የሥልጣን ዘመኑ ማኅበራዊና ኤኮኖሚያዊ አለኝታን በማጠናከራቸው ተራማጅ ሊባሉ የሚችሉ አንዳንድ እርምጃዎችን ወስዷል:: ላይ ከተጠቀሰው የግል ንብረትን የማስከበርና ዐሥራትን በወቅቱ የመሰብሰብ ደንብ በተጨማሪ፣ ከሳሽና ተከሳሽ አብረው እንዲማቅቁ ያደርግ የነበረውን የቁራኛ ሥርዓት ለመሻር እርምጃ ወስዷል:: እንዲሁም ከፍትሕ ይልቅ ለቂም መወጫና ደካማ ማጥቂያነት የሚያገለግለውን የሌባ ሻይ ሥርዓት መልክ ለማስያዝ ሞክሯል:: የመንግሥት ሒሳብ ኦዲት በማስደረግ አላግባብ የመንግሥት ገንዘብ ባባከኑት ላይ እርምጃ በመውሰድም ኢያሱ የመጀመሪያው የኢትዮጵያ መሪ ሳይሆን አይቀርም:: የሚያሳዝነው ግን አንዳንዴ በዚሁ ሳቢያ የጠላውን ሰው በሐሰት እያስወነጀለ ማሰሩ ነው:: በመሠረቱ የኢያሱ ገጸ ባሕርይም ሆነ ፖሊሲዎች መለዮ ውስጠ ተቃርኖና ቀጣይነት ማጣት ነበር:: ባንድ ወገን የተጠቃ እንባ አድራቂ ሆኖ የጂሌ ኦሮሞን ሕዝብ በዘረፉት በአፋሮች ላይ ሲዘምት እናየዋለን:: በዚያው ዓመት ደግሞ ለዘለዓለም በስሙ ላይ ጥቁር ነጥብ የጣለውን የጊሚራ ዘመቻ ሲመራና እልፍ አእላፍ ዜጎቹን ለባርነትና ሞት ሲዳርግ እናገኘዋለን:: «ጥርንቡሌ» የተባለውን የከተማ ዘበኛ ያቋቋመው አርቆ አሳቢ መሪ ሰዓት እላፊ እየጣሰ ከነሱው ጋር ሲታኩስ ይገኛል::

ይህ ሁሉ እንደ ዋዛ በታለፈ ነበር:: ለኢያሱ መጥፊያው የሆነው በጊሚራ ላይ መዝመቱ ወይ ከጥርንቡሌ ጋር መታኩሱ ሳይሆን ከዐድዋ በኋላ የተደላደለውን ፖለቲካዊና ዲፕሎማሲያዊ ስምምነት ማናጋቱ ነው:: በምኒልክ ዘመን ግርማና ሞገስ ያገኙት መኳንንትማ ቆሌያቸው ነው የተገፈፈው:: ንጉሣቸውን አጅበው አገር መዞሩን እንደ ትልቅ ወግ የሚቆጥሩትን እነዚህን መኳንንት አርፈው እንዲቀመጡ በሚከተሉት ቅስም ሰባሪ ቃላት አገዳቸው፤

> **እኔ ጎልማሶችን አስከትዬ አገር ለመጐብኘትና ያልቀናውን አገር ለማቅናት በተነሣሁ ጊዜ ያለፈቃዱ መከተል የለባችሁም:: ወፍራችኋል፣ ሸምግላችኋል:: በዘመናችሁ አባቴን ተከትላችሁ አገር አቅንታችኋል:: አሁን ግን ሽሽታችሁ አታመልጡም፣አባራችሁ አትጨብጡምና ተመልሳችሁ በየሥራችሁ ጠንክሩ::**
> **(መርስዔ ኃዘን፣ «ምኒልክ»፣ 103)**





3.21 ከሳሽና ተከሳሽ አብሮ የሚታገትበት የቁራኛ ሥርዓት

በቀና ትርጓሜ ኢያሱ የሚለው እናንት በተራችሁ ሠርታችኋል፤ አሁን ደግሞ ዘመናዊት ኢትዮጵያን የመገንባቱ ተራ የኛ የወጣቶቹ ነው ማለቱ ነው ሊባል ይችል ይሆናል:: መኳንንቱ ግን በዚህ መልክ አላዩለትም:: ያውም ይኸ ለስለስ ባለ አንደበት በይፋ ተናገረ የሚባለው ነው:: በሌላ ወቅት ግን «የአባቴ ሙክቶች» እያለ ያፌዝባቸው እንደነበር ይነገራል::

ኢያሱ ትዕግሥት ያጣው በመኳንንቱ ላይ ብቻ ሳይሆን በራሱ በምኒልክም ይመስላል:: የንጉሠ ነገሥቱ በሞትና ሕይወት መካከል ተንጠልጥሎ መቆየት የኢያሱን የፖለቲካ እድልም እንዲሁ በእንጥልጥል እንዲቀር አደረገው:: በ1905 አጋማሽ ላይ በኢያሱና በግቢ ዘበኞች መካከል የተፈጠረው ግጭት መንሥኤም ይኸው የኢያሱ ትዕግሥት ማጣት ይመስላል:: ከምኒልክ ሌላ ጌታ የማያውቁት ዘበኞች ቀደም ሲል ራስ አባተን ግቢ እናስገባም እንዳሉ ሁሉ፣ አሁንም ኢያሱ ምኒልክን ወደ እንኰበር ለማስወሰድ ሐሳብ አለው ማለትን ሰምተው እኛ ሳንሞት ንጉሣችን ከግቢ አይወጡም ብለው በኢያሱ ላይ በሩን ዘጉበት:: ኢያሱም ግቢውን ከቦ ዘበኞቹ ከውጭ ምንም ስንቅ እንዳያገኙ አደረገ:: አምስት ሰዓት የቆየ ተኩስም ተከፍቶ አሥራ ሰባት ያህል ሰዎች ሞቱ:: በመጨረሻ አቡነ ማቴዎስ በነገሩ ገብቶ ዘበኞቹ እጃቸውን እንዲሰጡ ተደረጉ:: መሪያቸው ፊታውራሪ ገብረ ማርያም በጌምድር፣ ሌሎቹ ሹማምንት ደግሞ



3.22 ሌባ ሻይ፣ ተጠርጣሪውን ለማደን በዝግጅት ላይ

ጎጃምና አንኰበር ታሰሩ:: ኢያሱም ለድሉ ማሳረጊያ ባሻ (ኋላ ደጃዝማች) ተሰማ ገዝሙን አዲስ የግቢ ዘበኞች አለቃ አርጎ ሾመ::

ኢያሱ የፈተነው መኳንንቱን ብቻ ሳይሆን ለዘመናት የቆየውን የኦርቶዶክስ ክርስትና እምነትን የበላይነት ጭምር ነበር:: ጠላቶቹ ኢያሱን በሕዝብ ዘንድ ለማስጠላት አመቺ መሣሪያ ሆኖ ያገኙትም ይህንኑ ነው:: ኢያሱ ከክርስቲያን ቤተ ሰቦች ጋር በጋብቻ እንዳልተሳሰረ ሁሉ፣ ተጋኖ የሚወራው ሙስሊም ሴቶችን ማግባቱ ሆነ:: እንደ ቀጨኔ መድኃኔዓለም ያሉትን አብያተ ክርስቲያን እንዳልተከለና እንደ ደብረ ሊባኖስ ገዳም ላሉት እንዳልቸረ ሁሉ፣ ጉድ ተብሎ የሚነገረው መስጊዶች ማሠራቱ ነበር:: በ1909 በኢያሱ ላይ የቀረበው ዋና ክስ መናፍቅነት ሆነ:: ክሱ አልመስል ላላቸው ተጠራጣሪዎች ማስተማመኛ ውም «ድሮውንስ ከሙሐመድ ዓሊ ልጅ (ራስ ሚካኤል ከመጠመቁ በፊት የሚታወቅበት ስም) ምን ይጠበቃል» የሚል ነበር::

ክሱ ግን ሐቀኛ መሠረት አልነበረውም:: የአገር ውስጥም ሆነ የውጭ መረጃዎች እንደሚያረጋግጡልን የኢያሱ ጥረት ክርስትናን በእስልምና ለመተካት ሳይሆን ያለፈውን አድልዎ የተመላበት ሥርዓት ሽሮ ሙስሊሞች በገዛ አገራቸው እንደባይተዋር መቆጠራቸውን ለማቆም ነበር:: የኢያሱ ችግር ፖሊሲውን በግልጽ አለማብራራቱና በአፈጻጸሙም ላይ ከዘዴ ይልቅ ማንአለብኝነት መምረጡ ላይ ነው:: በሃይማኖት ፖሊሲው ኢያሱን የሚተካከል ዘመናዊ የኢትዮጵያ መሪ ለማሰብ ያዳግታል:: አርቆ አሳቢው ቴዎድሮስ እንኳ የሙስሊሞች ነገር (በተለይ የወሎ ሙስሊሞች ነገር) ሲመጣ አስተሳሰቡ ጭፍን ነበር:: ዮሐንስም ቢሆን በፖለቲካው ሆደ ሰፊና ፌዴራላዊ እንዳልነበረ ሁሉ በኦርቶዶክስ ክርስትና ጥያቄም ሆነ በሙስሊሞች ጉዳይ ሲበዛ ግትር መሆኑን



አይተናል:: ምኒልክም ግዛት ማስፋቱን እንጂ ለግዛቱ ፍትሐዊ አስተዳደር በመመሥረቱ ላይ ይህን ያህል አልተጋም::

ከዚህ ሁሉ አኳያ ሲታይ የኢያሱ የሃይማኖት ፖሊሲ የብዙ ብሔረ ሰቦችና የሁለቱ ታላላቅ እምነቶች አገር የሆነችውን ኢትዮጵያ ፍትሕ በተሞላበት አንድነት ላይ ለመመሥረት የተደረገ የመጀመሪያ ሙከራ ተብሎ ሊገመገም ይችላል:: በኢያሱና በባላጋራዎቹ መካከል የነበረው የአስተሳሰብ ልዩነት ምን ያህል የጎላ እንደሆነ የምናየው መስከረም 16 1909 በኢያሱ ላይ የቀረቡትን ክሶች ስናይ ነው:: ከነዚህ ክሶች አንዱ ባንድ ወገን የኢያሱን አዲስ ፖሊሲ ሲጠቁም በሌላ ወገን ደግሞ ባላጋራዎቹ የዳር አገር ዜጋዎችን ከመርገጥና ከማስገበር በቀር ሌላ ስልት እንደማያውቁ የሚያሳይ ነው:: «እሳቸው ግን» ይላል ክሱ፣ «እስላም ያረደውን እየበሉ አገር ለማስፋትና ሰው ለማባበል ነው እያሉ የሚያታልሉት ይህ ሱማሌና እስላም ከዚህ በፊት ለጃንሆይ የገበረ የቀቀለ ዜጋቸው ነው::» (ማኅተመ ሥላሴ፣ 514)

ስለዚህ የመናፍቅነቱ ክስ የመነጨው ለሃይማኖት ከመጨነቅ ሳይሆን ለተፈጠረው የፖለቲካ ሥጋት ርእዮተ ዓለማዊ ሽፋን ሆኖ ለማገልገል ካለው አመቺነት ነው ማለት ይቻላል:: ለሸዋ መኳንንት የኢያሱ አደገኛነት የፖለቲካ የበላይነታቸውን ከመፈታተኑ ላይ ነበር:: በምኒልክ ጊዜ እንዳልተከበሩ እንዳልተፈሩ ሁሉ በዘመነ ኢያሱ ያጋጠማቸው ውርደትና ንቀት ነበር:: ብዙ የሸዋ መኳንንት «ሚስትህ መጥታ ትየኝ፣» የሚል ትርጉሙ የማያሻማ የኢያሱ ትእዛዝ እየደረሳቸው ሚስቶቻቸውን ኢያሱ ግቢ ድረስ ሸኝተው ይመለሱ ነበር ይባላል:: በመጨረሻ ኢያሱ የሚወደውን አጋዴንን ሲጎበኝ አዲስ አበባ እሱን ከሥልጣን ለማውረድ እየተዶለተ ስለሆነ ቶሎ እንዲመለስ ቢነገረውም «የሸዋን መኳንንት አንጋልዬ በአፉ ላይ ብሸናበት እንኳ የሚናገረኝ የለም» ብሎ በንቀት መመለሱ ይነገራል:: (መርስዔ ኃዘን፣ «ኢያሱ»፣ 43)

ይህ የሸዋን መኳንንት የማዳከሙ የኢያሱ ፖሊሲ ከፍተኛ ደረጃ የደረሰው በግንቦት 1906 አባቱን ራስ ሚካኤልን የወሎና የትግሬ ንጉሥ አስኝቶ ሲያነግሥ ነው:: እራሱ «ልጅ» ወይ «አቤቶ» እንጂ ንጉሥም ሆነ ንጉሠ ነገሥት ያልተባለው ኢያሱ ለአባቱ ከፍተኛውን ማዕረግ ሲሰጥ፣ የፖለቲካ ሕይወቱን የግማሽ ወሎ አባ ወራ ሆኖ የጀመረው ሚካኤል ምን ያህል ረጅም መንገድ እንደተጓዘ የሚያመለክት እርምጃ ነበር:: ሰሜን ኢትዮጵያን በቀጥታ፣ የተቀረውን ደግሞ በልጁ አማካይነት በተዘዋዋሪ ለመቆጣጠር የበቃው ሚካኤል ባጭሩ ያገሪቱ ገናና መስፍን ሆነ:: በደሴ የተከናወነው ሥርዓት ንግሥም የሚካኤልን ገናናነትና የወሎንም ማዕከላዊነት አጉልቶ ለማሳየት የታቀደ ይመስላል:: የአፄ ዮሐንስ ጳጳስ በነበረው በአቡነ ጴጥሮስ የተመራው የንግሥ በዓል ደማቅ ከመሆኑም በላይ ኢያሱን ወክለውም የግቢው ሚኒስትር ሊጋባ ወልደ ገብርኤል በሻህና የገንዘብ ሚኒስትሩ በጅሮንድ ይገዙ በሀብቱ ተገኝተው ነበር:: ለበዓሉ ሞገስና ከፍተኛውን ክብር ለመስጠትም ኢያሱ ከምኒልክ ቤተ መንግሥት ለአባቱ የላከውን ዘውድ፣ ሉልና የሥርዓት ንግሥ ልብስ ይዘው ሄደዋል::

ሌላው ኢያሱ የሸዋን መኳንንት ያስቀየመበት መንገድ በሚያደርገው ሹም ሽር ነበር:: ይህ ፖሊሲ ለብዙ የቀድሞ መኳንንት የሚበጅ አልነበረም:: ለምሳሌ የጦር ሚኒስትሩ ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ የሚኒስትሮች ምክር ቤት



3.22 ሌባ ሻይ፣ ተጠርጣሪውን ለማደን በዝግጅት ላይ

ጎጃምና አንኮበር ታሰሩ:: ኢያሱም ለድሉ ማሳረጊያ ባሻ (ኋላ ደጃዝማች) ተሰማ ገዝሙን አዲስ የግቢ ዘበኞች አለቃ አርጎ ሾመ::

ኢያሱ የፈተነው መኳንንቱን ብቻ ሳይሆን ለዘመናት የቆየውን የኦርቶዶክስ ክርስትና እምነትን የበላይነት ጭምር ነበር:: ጠላቶቹ ኢያሱን በሕዝብ ዘንድ ለማስጠላት አመቺ መሣሪያ ሆኖ ያገኙትም ይህንኑ ነው:: ኢያሱ ከክርስቲያን ቤተ ሰቦች ጋር በጋብቻ እንዳልተሳሰረ ሁሉ፣ ተጋኖ የሚወራው ሙስሊም ሴቶችን ማግባቱ ሆነ:: እንደ ቀጨኔ መድኃኔዓለም ያሉትን አብያተ ክርስቲያን እንዳልተከለና እንደ ደብረ ሊባኖስ ገዳም ላሉት እንዳልቻረ ሁሉ፣ ጉድ ተብሎ የሚነገረው መስጊዶች ማሠራቱ ነበር:: በ1909 በኢያሱ ላይ የቀረበው ዋና ክስ መናፍቅነት ሆነ:: ክሱ አልመስል ላላቸው ተጠራጣሪዎች ማስተማመኛ ውም «ድሮውንስ ከሙሐመድ ዓሊ ልጅ (ራስ ሚካኤል ከመጠመቁ በፊት የሚታወቅበት ስም) ምን ይጠበቃል» የሚል ነበር::

ክሱ ግን ሐቀኛ መሠረት አልነበረውም:: የአገር ውስጥም ሆነ የውጭ መረጃዎች እንደሚያረጋግጡልን የኢያሱ ጥረት ክርስትናን በእስልምና ለመተካት ሳይሆን ያለፈውን አድልዎ የተመላበት ሥርዓት ሸሮ ሙስሊሞች በገዛ አገራቸው እንደባይተዋር መቆጠራቸውን ለማቆም ነበር:: የኢያሱ ችግር ፖሊሲውን በግልጽ አለማብራራቱና በአፈጻጸሙም ላይ ከዘዴ ይልቅ ማንአለብኝነት መምረጡ ላይ ነው:: በሃይማኖት ፖሊሲው ኢያሱን የሚተካከል ዘመናዊ የኢትዮጵያ መሪ ለማሰብ ያዳግታል:: አርቆ አሳቢው ቴዎድሮስ እንኳ የሙስሊሞች ነገር (በተለይ የወሎ ሙስሊሞች ነገር) ሲመጣ አስተሳሰቡ ጭፍን ነበር:: ዮሐንስም ቢሆን በፖለቲካው ሆደ ሰፊና ፌዴራላዊ እንዳልነበረ ሁሉ በኦርቶዶክስ ክርስትና ጥያቄም ሆነ በሙስሊሞች ጉዳይ ሲበዛ ግትር መሆኑን



አይተናል:: ምኒልክም ግዛት ማስፋቱን እንጂ ለግዛቱ ፍትሐዊ አስተዳደር በመመሥረቱ ላይ ይህን ያህል አልተጋም::

ከዚህ ሁሉ አኳያ ሲታይ የኢያሱ የሃይማኖት ፖሊሲ የብዙ ብሔረ ሰቦችና የሁለቱ ታላላቅ እምነቶች አገር የሆነችውን ኢትዮጵያ ፍትሕ በተሞላበት አንድነት ላይ ለመመሥረት የተደረገ የመጀመሪያ ሙከራ ተብሎ ሊገመገም ይችላል:: በኢያሱና በባላጋራዎቹ መካከል የነበረው የአስተሳሰብ ልዩነት ምን ያህል የጎላ እንደሆነ የምናየው መስከረም 16 1909 በኢያሱ ላይ የቀረቡትን ክሶች ስናይ ነው:: ከነዚህ ክሶች አንዱ ባንድ ወገን የኢያሱን አዲስ ፖሊሲ ሲጠቁም በሌላ ወገን ደግሞ ባላጋራዎቹ የዳር አገር ዜጋዎችን ከመርገጥና ከማስገበር በቀር ሌላ ስልት እንደማያውቁ የሚያሳይ ነው:: «እሳቸው ግን» ይላል ክሱ፣ «እስላም ያረደውን እየበሉ አገር ለማስፋትና ሰው ለማባበል ነው እያሉ የሚያታልሉት ይህ ሱማሌና እስላም ከዚህ በፊት ለጃንሆይ የገበረ የቀቀለ ዜጋቸው ነው::» (ማኅተመ ሥላሴ፣ 514)

ስለዚህ የመናፍቅነቱ ክስ የመነጨው ለሃይማኖት ከመጨነቅ ሳይሆን ለተፈጠረው የፖለቲካ ሥጋት ርእዮተ ዓለማዊ ሽፋን ሆኖ ለማገልገል ካለው አመቺነት ነው ማለት ይቻላል:: ለሸዋ መኳንንት የኢያሱ አደገኛነት የፖለቲካ የበላይነታቸውን ከመፈታተኑ ላይ ነበር:: በምኒልክ ጊዜ እንዳልተከበሩ እንዳልተፈሩ ሁሉ በዘመነ ኢያሱ ያጋጠማቸው ውርደትና ንቀት ነበር:: ብዙ የሸዋ መኳንንት «ሚስትህ መጥታ ትየኝ፣» የሚል ትርጉሙ የማያሻማ የኢያሱ ትእዛዝ እየደረሳቸው ሚስቶቻቸውን ኢያሱ ግቢ ድረስ ሸኝተው ይመለሱ ነበር ይባላል:: በመጨረሻ ኢያሱ የሚወደውን አጋዴንን ሲሾበኝ አዲስ አበባ እሱን ከሥልጣን ለማውረድ እየተዶለተ ስለሆነ ቶሎ እንዲመለስ ቢነገረውም «የሸዋን መኳንንት አንጋልዬ በአፉ ላይ ብሸናበት እንኳ የሚናገረኝ የለም» ብሎ በንቀት መመለስ ይነገራል:: (መርስዔ ኃዘን፣ «ኢያሱ»፣ 43)

ይህ የሸዋን መኳንንት የማዳከሙ የኢያሱ ፖሊሲ ከፍተኛ ደረጃ የደረሰው በግንቦት 1906 አባቱን ራስ ሚካኤልን የወሎና የትግሬ ንጉሥ አስኝቶ ሲያነግሥ ነው:: እራሱ «ልጅ» ወይ «አቤቶ» እንጂ ንጉሥም ሆነ ንጉሠ ነገሥት ያልተባለው ኢያሱ ለአባቱ ከፍተኛውን ማዕረግ ሲሰጥ፣ የፖለቲካ ሕይወቱን የግማሽ ወሎ አባ ወራ ሆኖ የጀመረው ሚካኤል ምን ያህል ረጅም መንገድ እንደተጓዘ የሚያመለክት እርምጃ ነበር:: ሰሜን ኢትዮጵያን በቀጥታ፣ የተቀረውን ደግሞ በልጁ አማካይነት በተዘዋዋሪ ለመቆጣጠር የበቃው ሚካኤል ባጭሩ ያገሩቱ ገናና መስፍን ሆነ:: በደሴ የተከናወነው ሥርዓተ ንግሥም የሚካኤልን ገናናነትና የወሎንም ማዕከላዊነት አጉልቶ ለማሳየት የታቀደ ይመስላል:: የአፄ ዮሐንስ ጳጳስ በነበረው በአቡነ ጴጥሮስ የተመራው የንግሥ በዓል ደማቅ ከመሆኑም በላይ ኢያሱን ወክለውም የግቢው ሚኒስትር ሊጋባ ወልደ ገብርኤል በሻህና የገንዘብ ሚኒስትሩ በጅሮንድ ይገዙ በሀብቱ ተገኝተው ነበር:: ለበዓሉ ሞገስና ከፍተኛውን ክብር ለመስጠትም ኢያሱ ከምኒልክ ቤተ መንግሥት ለአባቱ የላከውን ዘውድ፣ ሉልና የሥርዓተ ንግሥ ልብስ ይዘው ሄደዋል::

ሌላው ኢያሱ የሸዋን መኳንንት ያስቀየመበት መንገድ በሚያደርገው ሹም ሽር ነበር:: ይህ ፖሊሲ ለብዙ የቀድሞ መኳንንት የሚበጅ አልነበረም:: ለምሳሌ የጦር ሚኒስትሩ ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ የሚኒስትሮች ምክር ቤት

ሊቀመንበርነትን ለታዳጊውና ለኢያሱ ባለው ቅርበት ለቢትወደድነት ማዕረግ ለበቃው ለነጋድራስ ኃይለ ጊዮርጊስ መልቀቅ ነበረበት። ደጃች ተፈሪ መኰንንም ትልቅ የገቢ ምንጩ የነበረውን የሐረርና ድሬዳዋ ጉምሩክ የኢያሱ ወዳጅ ለነበረው ይድልቢ መተው ነበረበት። ይድልቢ በዚህም አላበቃም፤ ተጠሪነቱ በቀጥታ ለኢያሱ ሆኖ ቀድሞ የሰዮና የጉሬ ገዥዎች መፋለሚያ መድረክ የነበረው የጋምቤላ ግዛት ገዥ ሆነ። ባጠቃላይ በኢያሱ ሹም ሽር ብዙ ሰዎች አኩርፈው እሱን ከሥልጣን ለማውረድ ማድባት ጀመሩ። የሀብተ ጊዮርጊስና የተፈሪ ኀብረት (ምንም እንኳ ዘላቂ ባይሆን) የመነጨውም ከዚህ ሁኔታ ነው።

በመጨረሻም ኢያሱ ዐይናቸውን በኢትዮጵያ ላይ ለተከሉት ሦስት ኃያላን መንግሥታት (እንግሊዝ፣ፈረንሳይና ኢጣልያ) ከፍተኛ አደጋ ፈጠረ። የኢትዮጵያ ነፃነት እኒህን መንግሥታት ምንጊዜም እንዳባነናቸው ነበር። ምክንያቱም ባዋሳኝ ቅኝ ግዛቶቻቸው ያላቸውን ሥልጣን ሊሸረሽረው ይችላል የሚል ሥጋት ስለነበራቸው ነው። ስለዚህም ነው በ1899 ባደረጉት ስምምነት እንደምናየው እርምጃቸውን አቀናብረው አትዮጵያን በነሱ ተጽዕኖ ሥር ለማቆየት የወሰኑት። ምኒልክም ቢሆን የኢትዮጵያ ነፃነት ፍጹም አለመሆኑን የተረዳ ይመስላል። ስለሆነም ከሦስቱ መንግሥታት ጋር አንድ ዓይነት ዲፕሎማሲያዊ መቻቻል ደረጃ ላይ ደርሶ ነበር ማለት ይቻላል። በዚህ ሁኔታ ነው የኢያሱ የውጭ ፖሊሲ ይህን ዲፕሎማሲዊ ሚዛን የሚያናጋ ሆኖ የታየው።

ሦስቱ መንግሥታት ይህ አደጋ ቁልጭ ብሎ የወጣላቸው ኢያሱ በተለይ በኦጋዴን በሚከተለው ፖሊሲ ነበር። መቼም ኢያሱ ለዚያ አካባቢ የተለየ ፍቅር የነበረው ይመስላል። በማግኒት እንደሚሳብ ሁሉ ተሽከርክሮ ተሽከርክሮ የሚመለሰው እዚያው ነበር። ጠላቶቹ ከሥልጣን ያወረዱትም እዚያው በነበረበት ወቅት ነው። ተጨማሪ መረጃዎች ቢያስፈልጉም የኢያሱ ጥረት በሃይማኖት ፖሊሲው እንዳየነው ሁሉ እስከዚያን ጊዜ ድረስ ዕጣው የዘረፋ ዒላማነት ብቻ የነበረውን የሱማሌ ሕዝብ በኢትዮጵያዊነቱ የሚገባውን ከበሬታ ለመስጠት የፈለገ ነው የሚመስለው። በዐጻፋው ሱማሌዎች ኢያሱን በልዩ ፍቅር እንደሚመለከቱት ከሥልጣን መውረዱን በሰሙበት ወቅት በቁጣ ሐረር ከተማ ላይ ሲዘምቱ ግልፅ ሊሆን ነው። ኢያሱ የሶማሌዎችን አለኝታ ለማጠናከር ከወሰዳቸው እርምጃዎች አንዱ ዐብደላ ሰዴቅ የተባለውን የአገሬውን ሰው የኦጋዴን ገዥ አድርጎ መሾሙ ነው። የአካባቢውን ቅኝ ገዥዎች ያስበረገጋቸው ግን ይህ ሳይሆን አንዛዛቸውን ከመሠረቱበት ጊዜ ጀምሮ ለዐሥራ አምስት ዓመታት ያህል በተለይ በእንግሊዞችና በጣልያኖች ላይ የብሔራዊ አርነት ጦርነት ዐውጆ ለነበረው የሶማሌ መሪ ለሰይድ ሙሐመድ ዐብዱሌ ሐሰን የሞራልና የማቴሪያል ድጋፍ መስጠቱ ነው።

በሰላሙም ጊዜ እንኳ ቢሆን ይህ የኢያሱ ፖሊሲ ቅኝ ገዥዎቹን ማስደንገጡ ግልጽ ነው። ይህ ሁሉ የአንደኛው የዓለም ጦርነት እየተካሄደ እያለ መሆኑ ደግሞ ከማስደንገጥም አልፎ ክፋኛ የሚያቃዠ ነበር። በቅኝ ገዥዎቹ ዐይን ኢያሱ እነሱ በአውሮጳና መካከለኛው ምሥራቅ ከጀርመንና ከቱርክ ጋር ሲተናነቁ በአፍሪቃ ቅኝ ዜጎቻቸውን የሚያሸፍት ሠይጣን ሆኖ ታያቸው። ባንፃሩም ጀርመንና ቱርክ (በተለይም ቱርክ) የኢያሱን እስራቴጂካዊ ጠቃሚነት





3.23 ነጋድራስ (ኋላ ቢትወደድ) ኃይለ ጊዮርጊስ ወልደ ሚካኤል፤ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትርና «ጠቅላይ ሚኒስትር»

ተገንዝበው ወደነሱ ካምፕ እንዲገባ ማባበል ጀመሩ። ምንም እንኳ ኢያሱ ጭልጥ ብሎ ወደዚያ ካምፕ ባይገባም ያሳየው ምልክት ሦስቱ አጎራባች ቅኝ ገዥዎች ሳይውሉ ሳያድሩ እሱን ከሥልጣን ለማስወገድ እንዲተባበሩ ለማድረግ በቂ ነበር።

እንግዲህ ኢያሱን ከሥልጣን ያስወገደው የውስጥና የውጭ ኃይሎች ኅብረት የተፈጠረው በዚህ መንገድ ነበር። ውስጥ ውስጡን ሲብላላ የነበረውን ተቃውሞ ይፋ እንዲወጣ ያደረገው በጳጉሜ 1908 ሦስቱ አጎራባች ቅኝ ገዥዎች (በዓለም ጦርነቱ ወቅት ደግሞ እንዳጋጣሚ በቃል ኪዳን የተሳሰሩት አገሮች) የኢያሱን የጠላትነት እርምጃ አስመልክተው የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ ሲጽፉ ነው። ከዚያም አልፈው ከኢያሱ የውስጥ ባላጋራዎች ጋር ኢያሱን ከሥልጣን ለማውረድ ከተስማሙ በኋላ የኢያሱን መስለም የሚያሳዩ ፎቶግራፎችና ሰነዶች በማዘጋጀት ለአድማው መሳካት ቀጥተኛ አስተዋፅኦ አድርገዋል።

ሊቀመንበርነትን ለታዳጊውና ለኢያሱ ባለው ቅርበት ለቢትወደድነት ማዕረግ ለበቃው ለነጋድራስ ኃይለ ጊዮርጊስ መልቀቅ ነበረበት:: ደጃች ተፈሪ መኰንንም ትልቅ የገቢ ምንጩ የነበረውን የሐረርና ድሬዳዋ ጉምሩክ የኢያሱ ወዳጅ ለነበረው ይድልቢ መተው ነበረበት:: ይድልቢ በዚህም አላበቃም፤ ተጠሪነቱ በቀጥታ ለኢያሱ ሆኖ ቀድሞ የሰዮና የጉሬ ገዥዎች መፋለሚያ መድረክ የነበረው የጋምቤላ ግዛት ገዥ ሆነ:: ባጠቃላይ በኢያሱ ሹም ሽር ብዙ ሰዎች አኩርፈው እሱን ከሥልጣን ለማውረድ ማድባት ጀመሩ:: የሀብተ ጊዮርጊስና የተፈሪ ኅብረት (ምንም እንኳ ዘላቂ ባይሆን) የመነጨውም ከዚህ ሁኔታ ነው::

በመጨረሻም ኢያሱ ዐይናቸውን በኢትዮጵያ ላይ ለተከሉት ሦስት ኃያላን መንግሥታት (እንግሊዝ፣ፈረንሳይና ኢጣልያ) ከፍተኛ አደጋ ፈጠረ:: የኢትዮጵያ ነፃነት እነዚህን መንግሥታት ምንጊዜም እንዳባነናቸው ነበር:: ምክንያቱም ባዋሳኝ ቅኝ ግዛቶቻቸው ያላቸውን ሥልጣን ሊሸረሽረው ይችላል የሚል ሥጋት ስለነበራቸው ነው:: ስለዚህም ነው በ1899 ባደረጉት ስምምነት እንደምናየው እርምጃቸውን አቀናብረው አትዮጵያን በነሱ ተጽዕኖ ሥር ለማቆየት የወሰኑት:: ምኒልክም ቢሆን የኢትዮጵያ ነፃነት ፍጹም አለመሆኑን የተረዳ ይመስላል:: ስለሆነም ከሦስቱ መንግሥታት ጋር አንድ ዓይነት ዲፕሎማሲያዊ መቻቻል ደረጃ ላይ ደርሶ ነበር ማለት ይቻላል:: በዚህ ሁኔታ ነው የኢያሱ የውጭ ፖሊሲ ይህን ዲፕሎማሲዊ ሚዛን የሚያናጋ ሆኖ የታየው::

ሦስቱ መንግሥታት ይህ አደጋ ቁልጭ ብሎ የወጣላቸው ኢያሱ በተለይ በኦጋዴን በሚከተለው ፖሊሲ ነበር:: መቼም ኢያሱ ለዚያ አካባቢ የተለየ ፍቅር የነበረው ይመስላል:: በማግኒት እንደሚሳብ ሁሉ ተሽከርክሮ ተሽከርክሮ የሚመለሰው እዚያው ነበር:: ጠላቶቹ ከሥልጣን ያወረዱትም እዚያው በነበረበት ወቅት ነው:: ተጨማሪ መረጃዎች ቢያስፈልጉም የኢያሱ ጥረት ብሄይማኖት ፖሊሲው እንዳየነው ሁሉ እስከዚያን ጊዜ ድረስ ዕጣው የዘረፋ ዒላማነት ብቻ የነበረውን የሱማሌ ሕዝብ በኢትዮጵያዊነቱ የሚገባውን ክበሬታ ለመስጠት የፈለገ ነው የሚመስለው:: በዐጸፋው ሱማሌዎች ኢያሱን በልዩ ፍቅር እንደሚመለከቱት ከሥልጣን መውረዱን በሰሙበት ወቅት በቁጣ ሐረር ከተማ ላይ ሲዘምቱ ግልፅ ሊሆን ነው:: ኢያሱ የሶማሌዎችን አለኝታ ለማጠናከር ከወሰዳቸው እርምጃዎች አንዱ ዐብደላ ሰዴቅ የተባለውን የአገሬውን ሰው የኦጋዴን ገዥ አድርጎ መሾሙ ነው:: የአካባቢውን ቅኝ ገዥዎች ያስበረገጋቸው ግን ይህ ሳይሆን አገዛዛቸውን ከመሠረቱበት ጊዜ ጀምሮ ለዐሥራ አምስት ዓመታት ያህል በተለይ በእንግሊዞችና በጣልያኖች ላይ የብሔራዊ አርነት ጦርነት ዐውጆ ለነበረው የሶማሌ መሪ ለሰይድ ሙሐመድ ዐብዱሌ ሐሰን የሞራልና የማቴሪያል ድጋፍ መስጠቱ ነው::

በሰላሙም ጊዜ እንኳ ቢሆን ይህ የኢያሱ ፖሊሲ ቅኝ ገዥዎቹን ማስደንገጡ ግልጽ ነው:: ይህ ሁሉ የአንደኛው የዓለም ጦርነት እየተካሄደ እያለ መሆኑ ደግሞ ከማስደንገጥም አልፎ ክፉኛ የሚያቃዥ ነበር:: በቅኝ ገዥዎቹ ዐይን ኢያሱ እነሱ በአውሮጳና መካከለኛው ምሥራቅ ከጀርመንና ከቱርክ ጋር ሲተናነቁ በአፍሪቃ ቅኝ ዜጎቻቸውን የሚያሸፍት ሠይጣን ሆኖ ታያቸው:: ባንፃሩም ጀርመንና ቱርክ (በተለይም ቱርክ) የኢያሱን እስራቴጂካዊ ጠቃሚነት





3.23 ነጋድራስ (ኋላ ቢትወደድ) ኃይለ ጊዮርጊስ ወልደ ሚካኤል፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትርና «ጠቅላይ ሚኒስትር»

ተገንዝበው ወደነሱ ካምፕ እንዲገባ ማባበል ጀመሩ:: ምንም እንኳ ኢያሱ ጭልጥ ብሎ ወደዚያ ካምፕ ባይገባም ያሳየው ምልክት ሦስቱ አጎራባች ቅኝ ገዥዎች ሳይውሉ ሳያድሩ እሱን ከሥልጣን ለማስወገድ እንዲተባበሩ ለማድረግ በቂ ነበር::

እንግዲህ ኢያሱን ከሥልጣን ያስወገደው የውስጥና የውጭ ኃይሎች ኅብረት የተፈጠረው በዚህ መንገድ ነበር:: ውስጥ ውስጡን ሲብላላ የነበረውን ተቃውሞ ይፋ እንዲወጣ ያደረገው በጳጉሜ 1908 ሦስቱ አጎራባች ቅኝ ገዥዎች (በዓለም ጦርነቱ ወቅት ደግሞ እንዳጋጣሚ በቃል ኪዳን የተሳሰሩት አገሮች) የኢያሱን የጠላትነት እርምጃ አስመልክተው የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ ሲጽፉ ነው:: ከዚያም አልፈው ከኢያሱ የውስጥ ባላጋራዎች ጋር ኢያሱን ከሥልጣን ለማውረድ ከተስማሙ በኋላ የኢያሱን መስለም የሚያሳዩ ፎቶግራፎችና ሰነዶች በማዘጋጀት ለአድማው መሳካት ቀጥተኛ አስተዋፅኦ አድርገዋል::



3.24 ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ምኒልክ

እንደተለመደውም መሀል ሰፋሪዎች ለአድማው ሕዝባዊ ገፅታ ሰጥተውታል፡፡ ዋናው ክስ መናፍቅነት በመሆኑም የአድማው መንፈሳዊ መሪ እጨጌው ወልደ ጊዮርጊስ ነበር፡፡ አድመኞቹ የሚሰባሰቡት በእጨጌው ቤት ሲሆን ሌላው አቀነባባሪ ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ነበር፡፡ የኢያሱ ዕጣ አሳዛኝነት ይበልጥ የሚታየው ግን ያቀረባቸውና የሸለማቸው ሁሉ በቀውጢው ጊዜ ሲከዱት ነው፡፡ ከነዚህም መካከል ሊጋባ በየነ ወንድምአገኘሁ፣ በጅሮንድ ይገዙ በሀብቱ፣ የኢያሱን እንት ወይዘሮ ስሂንን እስከማግባት የደረሰውና በኢያሱ ዘመን ከፍተኛውን ሥልጣን የያዘው ቢትወደድ ኃይለ ጊዮርጊስና የኢያሱ አማካሪ ነበረው ምሁር ተክለ ሐዋርያት ተክለ ማርያም ይገኙበታል፡፡

ኢያሱን ለማውገዝ ያልቸኰለው አቡነ ማቴዎስ ብቻ ነው፡፡ አድመኞቹ ለኢያሱ ከገቡበት ቃለ መሐላ እንዲፈታቸው ሲጠይቁት ኢያሱ ለመስለሙ ተጨባጭ ማስረጃ የለም ብሎ አንገራገረ፡፡ የኋላ ኋላ ግን የእጨጌው ግፊት ቢበዛበት አድመኞቹን ከግዝቱ ፈታቸው፡፡ ከዚያ በኋላ እንዳጋጣሚ ሆኖ በዕለተ መስቀል ሰለመ የተባለው ኢያሱ ከሥልጣኑ እንዲወርድ ተወስኖ የምኒልክ ልጅ ዘውዲቱ ዙፋኑን ስትወርስ ደጃች ተፈሪ መኰንን ደግሞ አልጋ ወራሽ ተባለ፡፡ ይህ ሁሉ የሆነው ለጥቂት ደቂቃዎች ዓላማ የሌለው ተኩስ ከማስተጋባቱ በስተቀር በአጭር ጊዜና ያለብዙ ውዝግብ ነበር፡፡

ኢያሱ ከሥልጣን መውረዱን እንደሰማ፣ ከነበረበት ከጅጅጋ ወደ አዲስ አበባ ገሠገሠ፡፡ ነገር ግን ሚኤሶ ላይ 15000 የሸዋ ጦር ጠብቆ ጦርነት ገጠመው፡፡ ኢያሱ ተሸንፎ ወደ አፋር በረሃ መሸሽ ነበረበት፡፡ ለሚከተሉት አምስት ዓመታትም ከቦታ ቦታ ሲባረር ኖረ፡፡ እንደተጠበቀው ለአዲስ አበባው ውሳኔ ዋና ተቃውሞ የመጣው ከኢያሱ ሳይሆን ከአባቱ ከንጉሥ ሚካኤል ነው፡፡ «የጠፋ ልጄን አፋልገኝ» ብሎ 80000 ጦር እየመራ በሸዋ ላይ ዘመተ፡፡ በሸዋ በኩልም ቁጥሩ 120000 የሚደርስ ጦር ከቶ ነበረ፡፡ የመጀመሪያው ውጊያ ቶራ መስክ ላይ በጥቅምት 7፣ 1909 ተደርጎ የወሎ ጦር ሲያሸንፍ የሸዋው መሪ ራስ ሉልሰገድ አጥናፍሰገድም ውጊያው ላይ ወደቀ፡፡ ይህ የመጀመሪያ ድልና የሸዋው ጦር ዋና እስትራቴጂስት የፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ የሽንገላ ቃላትና ገጸ በረከት ሚካኤልን አዘናጋው፡፡ ከዐድዋ ጦርነት በኋላ ብዙ ደም የፈሰሰበት ከፍተኛው ውጊያ ሰገሌ ላይ ጥቅምት 17 ተደረገ፡፡ የሸዋ ጦር የከበባ ስልት ተጠቅሞ የወሎን ጦር ባላሰበበት በደጀኑ ሲያጠቃው ተበተነ፡፡ ንጉሥ ሚካኤልም ተማረከ፡፡ የሥልጣን ዝውውሩም በደም ታነጸ፡፡



## በፍጹማዊ ሥልጣን ጎዳና /1909-1923/

ዘውዲቱን ንግሥተ ነገሥት፣ ተፈሪን አልጋ ወራሽ ያደረገው የፖለቲካ ለውጥ ኢያሱን ከሥልጣን ያወረዱትን ሁለቱንም ዋና ኃይሎች ለማስደሰት ተብሎ የታቀደ ይመስላል፡፡ ንግሥቲቱ የሸዋ መኳንንት፣ አልጋ ወራሹ የሌጋሲዮኖቹ ምርጫ ነበሩ፡፡ ዘውዲቱን ለዙፋን ያበቃት ዋነኛው መለኪያ የምኒልክ ልጅ መሆኗ ነው፡፡ የሸዋ መኳንንት ምርጫ የሆነችውም እንደ ኢያሱ (ወይም ወደፊት እንደተፈሪ) ፖለቲካ ሥጋት ላይ የሚጥላቸው እርምጃ አትወስድም ብለው በመተማመን ነው፡፡ ተፈሪ እንደ ዘውዲቱ የንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ዘርያ በመሆኑ ለዙፋኑ እኩል ብቃት ቢኖረውም አልጋ ወራሽነቱን ያገኘው በዘር ቆጠራ ብቻ ሳይሆን የሌጋሲዮኖቹ ወዳጅ በመሆኑና በመጠኑም አውሮጳ ቀመስ ትምህርት ስለነበረው ነው፡፡ እያደርም ይህ ከፈረንጆች ጋር ያለው ወዳጅነት የፖለቲካ ሥልጣን መሠረቱን ለማጠናከር ረድቶታል፡፡ ባንፃሩ ግን በመሳፍንቱና መኳንንቱ ዘንድ በአፍቃሬ ፈረንጅነት፣በካቶሊክነትና አገርን በመሸጥ ሲያሳማውና ሲያስወነጅለው ቆይቷል፡፡

የ1909ኙ የፖለቲካ ውሳኔ በተጨማሪም የእንግዳነት፣የተገላቢጦሽነትና የአደናጋሪነት ባሕሪ ነበረው፡፡ እንግዳነቱ ከዚያ በፊት ንጉሡ ዘውድ ሲጭን ወይም ንግሥቲቱ ዘውድ ስትጭን አልጋ ወራሹን መሰየም የተለመደ ስላልነበረ ነው፡፡ ቀደም ባለው የኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ እድሜያቸው ለጋ በሆነ ልጆቻቸው ወይ ነገሥታት ስም የመንግሥት ሥልጣን የሚያንቀሳቅሱ እቴጌዎች ነበሩ፡፡ ለምሳሌም በ16ኛው መቶ ዓመት መጀመሪያ በልብነ ድንግል ስም ትገዛ የነበረችውን ንግሥት እሌኒና በ18ኛው መቶ ዓመት በዳግማዊ ኢያሱ አድያም ሰገድ ስም ሥልጣን የነበራትን እቴጌ ምንትዋብን መጥቀስ ይቻላል፡፡ በቅርቡ ከላይ ያየነው የጣይቱ ሙከራም የነዚህን የቀድሞ እቴጌዎች ታሪክ ለመድገም ነበር፡፡ አሁን የምናየው ግን በተገላቢጦሽ እናቱ ልትሆን የምትችለው ዘውዲቱ ለስሙ ንግሥት ተብላ፣ ልጇ ሊሆን የሚችለው ተፈሪ ግን በአልጋ ወራሽነት ሙሉ ሥልጣን በእጁ መጠቅለሉን ነው፡፡

የነገሩ ችግር እምብርትም እዚህ ላይ ነው፡፡ አደናጋሪነቱም ይኸው ነው፡፡ ዘውዲቱ ንግሥት፣ ተፈሪ አልጋ ወራሽ ተብለው ይሰየሙ እንጂ የሥልጣን ገደባቸውና የሥራ ድርሻቸው በውል አልታወቀም ነበር፡፡ አንዳንድ አስተዋይ



3.24 ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ምኒልክ

እንደተለመደውም መሀል ሰፋሪዎች ለአድማው ሕዝባዊ ገፅታ ሰጥተውታል። ዋናው ክስ መናፍቅነት በመሆኑም የአድማው መንፈሳዊ መሪ እጨጌው ወልደ ጊዮርጊስ ነበር። አድመኞቹ የሚሰባሰቡት በእጨጌው ቤት ሲሆን ሌላው አቀነባባሪ ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ነበር። የኢያሱ ዕጣ አሳዛኝነት ይበልጥ የሚታየው ግን ያቀረባቸውና የሸለማቸው ሁሉ በቀውጢው ጊዜ ሲከዱት ነው። ከነዚህም መካከል ሊጋባ በየነ ወንድምአገኘሁ፣ በጅሮንድ ይገዙ በህብቴ፣ የኢያሱን እኅት ወይዘሮ ስሂንን እስከማግባት የደረሰውና በኢያሱ ዘመን ከፍተኛውን ሥልጣን የያዘው ቢትወደድ ኃይለ ጊዮርጊስና የኢያሱ አማካሪ ነበረው ምሁር ተክለ ሐዋርያት ተክለ ማርያም ይገኙበታል።

ኢያሱን ለማውገዝ ያልቸኮለው አቡነ ማቴዎስ ብቻ ነው። አድመኞቹ ለኢያሱ ከገቡበት ቃለ መሐላ እንዲፈታቸው ሲጠይቁት ኢያሱ ለመስለሙ ተጨባጭ ማስረጃ የለም ብሎ አንገራገረ። የኋላ ኋላ ግን የእጨጌው ግፊት ቢበዛበት አድመኞቹን ከግዝቱ ፈታቸው። ከዚያ በኋላ እንዳጋጣሚ ሆኖ በዕለተ መስቀል ሰለመ የተባለው ኢያሱ ከሥልጣኑ እንዲወርድ ተወስኖ የምኒልክ ልጅ ዘውዲቱ ዙፋኑን ስትወርስ ደጃች ተፈሪ መኰንን ደግሞ አልጋ ወራሽ ተባለ። ይህ ሁሉ የሆነው ለጥቂት ደቂቃዎች ዒላማ የሌለው ተኩስ ከማስተጋባቱ በስተቀር በአጭር ጊዜና ያለብዙ ውዝግብ ነበር።

ኢያሱ ከሥልጣን መውረዱን እንደሰማ፣ ከነበረበት ከጅጅጋ ወደ አዲስ አበባ ገሠገሠ። ነገር ግን ሚኤሶ ላይ 15000 የሸዋ ጦር ጠብቆ ጦርነት



ገጠመው። ኢያሱ ተሸንፎ ወደ አፋር በረሃ መሸሽ ነበረበት። ለሚከተሉት አምስት ዓመታትም ከቦታ ቦታ ሲባረር ኖረ። እንደተጠበቀው ለአዲስ አበባው ውሳኔ ዋና ተቃውሞ የመጣው ከኢያሱ ሳይሆን ከአባቱ ከንጉሥ ሚካኤል ነው። «የጠፋ ልጄን አፋልገኝ» ብሎ 80000 ጦር እየመራ በሸዋ ላይ ዘመተ። በሸዋ በኩልም ቁጥሩ 120000 የሚደርስ ጦር ክቶ ነበረ። የመጀመሪያው ውጊያ ቶራ መስክ ላይ በጥቅምት 7፣ 1909 ተደርጎ የወሎ ጦር ሲያሸንፍ የሸዋው መሪ ራስ ሉልሰገድ አጥናፍሰገድም ውጊያው ላይ ወደቀ። ይህ የመጀመሪያ ድልና የሸዋው ጦር ዋና እስትራቴጂስት የፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ የሸንገላ ቃላትና ገጸ በረከት ሚካኤልን አዘናጋው። ከዐድዋ ጦርነት በኋላ ብዙ ደም የፈሰሰበት ከፍተኛው ውጊያ ሰገሌ ላይ ጥቅምት 17 ተደረገ። የሸዋ ጦር የከበባ ስልት ተጠቅሞ የወሎን ጦር ባሳሰበበት በደጀኑ ሲያጠቃው ተበተነ። ንጉሥ ሚካኤልም ተማረከ። የሥልጣን ዝውውሩም በደም ታነጸ።

## በፍጹማዊ ሥልጣን ጎዳና /1909-1923/

ዘውዲቱን ንግሥተ ነገሥት፣ ተፈሪን አልጋ ወራሽ ያደረገው የፖለቲካ ለውጥ ኢያሱን ከሥልጣን ያወረዱትን ሁለቱንም ዋና ኃይሎች ለማስደሰት ተብሎ የታቀደ ይመስላል። ንግሥቲቱ የሸዋ መኳንንት፣ አልጋ ወራሹ የሌጋሲዮኖቹ ምርጫ ነበሩ። ዘውዲቱን ለዙፋን ያበቃት ዋነኛው መለኪያ የምኒልክ ልጅ መሆኗ ነው። የሸዋ መኳንንት ምርጫ የሆነችውም እንደ ኢያሱ (ወይም ወደፊት እንደተፈሪ) ፖለቲካ ሥጋት ላይ የሚጥላቸው እርምጃ አትወስድም ብለው በመተማመን ነው። ተፈሪ እንደ ዘውዲቱ የንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ዝርያ በመሆኑ ለዙፋኑ እኩል ብቃት ቢኖረውም አልጋ ወራሽነቱን ያገኘው በዘር ቆጠራ ብቻ ሳይሆን የሌጋሲዮኖቹ ወዳጅ በመሆኑና በመጠኑም አውሮጳ ቀመስ ትምህርት ስለነበረው ነው። እያደርም ይህ ከፈረንጆች ጋር ያለው ወዳጅነት የፖለቲካ ሥልጣን መሠረቱን ለማጠናከር ረድቶታል። ባንፃሩ ግን በመሳፍንቱና መኳንንቱ ዘንድ በአፍቃሬ ፈረንጅነት፣በካቶሊክነትና አገርን በመሸጥ ሲያሳማውና ሲያስወነጅለው ቆይቷል።

የ1909ኙ የፖለቲካ ውሳኔ በተጨማሪም የእንግዳነት፣የተገላቢጦሽነትና የአደናጋሪነት ባሕሪ ነበረው። እንግዳነቱ ከዚያ በፊት ንጉሡ ዘውድ ሲጭን ወይም ንግሥቲቱ ዘውድ ስትጭን አልጋ ወራሹን መሰየም የተለመደ ስላልነበረ ነው። ቀደም ባለው የኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ እድሜያቸው ለጋ በሆነ ልጆቻቸው ወይ ነገሥታት ስም የመንግሥት ሥልጣን የሚያንቀሳቅሱ እቴጌዎች ነበሩ። ለምሳሌም በ16ኛው መቶ ዓመት መጀመሪያ በልብነ ድንግል ስም ትገዛ የነበረችውን ንግሥት እሌኒና በ18ኛው መቶ ዓመት በዳግማዊ ኢያሱ አድያም ሰገድ ስም ሥልጣን የነበራትን እቴጌ ምንትዋብን መጥቀስ ይቻላል። በቅርቡ ከላይ ያየነው የጣይቱ ሙከራም የነዚህን የቀድሞ እቴጌዎች ታሪክ ለመድገም ነበር። አሁን የምናየው ግን በተገላቢጦሽ እናቱ ልትሆን የምትችለው ዘውዲቱ ለስሙ ንግሥት ተብላ፣ ልጇ ሊሆን የሚችለው ተፈሪ ግን በአልጋ ወራሽነት ሙሉ ሥልጣን በእጁ መጠቅለሉን ነው።

የነገሩ ችግር እምብርትም እዚህ ላይ ነው። አደናጋሪነቱም ይኸው ነው። ዘውዲቱ ንግሥት፣ ተፈሪ አልጋ ወራሽ ተብለው ይሰየሙ እንጂ የሥልጣን ገደባቸውና የሥራ ድርሻቸው በውል አልታወቀም ነበር። አንዳንድ አስተዋይ

ሰዎች ይህ ሁኔታ ወደፊት ችግር ሊፈጥር እንደሚችል አስጠንቅቀው ነበር፤ ግን ሰሚ አላገኙም። ቀስ በቀስ ተፈሪ አልጋ ወራሽ ብቻ ሳይሆን እንደ ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴም መታየት ጀመረ። ኢያሱ ከሥልጣን እንደወረደ የተሰራጩት ሰነዶች በግልጽ የሚነግሩን ተፈሪ አልጋ ወራሽ ብቻ እንደተባለ ነው። እሱ እራሱ ሕይወቱና የኢትዮጵያ እርምጃ በተሰኘው የሕይወት ታሪኩ ግን በተጨማሪ እንደራሴ ተባልኩ ብሎ ያወሳል። ይህ አደናጋሪ ሁኔታ ነው በ1917 በተፈሪ ላይ ከተነሡት ተከታታይ አመፆች አንዱን ያስነሣው። የአድማው መሪ ቀደም ሲል በኢያሱ ላይ ፊቱን ሲያዞር ያየነው ሊጋባ በየነ ሲሆን የነገሩ መነሻም ተፈሪ አልጋ ወራሽ እንጂ እንደራሴ ስላልተባለ ዘውዲቱ በሕይወት እስካለች ድረስ የፖለቲካ ሥልጣን ለመጠቅለል ከመሞከር መታቀብ አለበት የሚል ነው። እንደሌሎቹ ፀረ-ተፈሪ አድማዎች ሁሉ ይኸም ከሸፎ ሊጋባው በአደባባይ ከተገረፈ በኋላ ወደ ሐረር ተግዟል።

ዞሮ ዞሮ ግን ተፈሪን የረዳው እንደራሴ መባል አለመባሉ ሳይሆን ወደ ፖለቲካው መድረክ ይዞ የመጣው አንፃራዊ የፖለቲካ ብስለት ነው። በዘውዲቱና በተፈሪ መካከል የሃያ ዓመት ልዩነት ቢኖርም ከሷ የበለጠ የፖለቲካና የአስተዳደር ልምድ ለማካበት በቅቷል። ምንም እንኳ አንዳንዶቹን ግዛቶች በእንደራሴ ያስተዳደረ ቢሆንም በተከታታይ የጋራሙለታ፣ የሰላሌ፣ የሲዳሞና የሐረር ገዥ ሆኗል። ባንፃሩ የዘውዲቱ የፖለቲካ ልምድ እጅግ ውሱን ነበር። በተከታታይ ቁንጮ ለሆኑ መሳፍንት ከመዳሯ በስተቀር (መጀመሪያ ለአፄ ዮሐንስ ልጅ ለራስ አርአያ ሥላሴ፣ቀጥሎ ለሸዋው መኳንንት ለደጃች ውቤ አጥናፍ ሰገድ፣ በመጨረሻም ለበጌምድሩ ራስ ጉግሣ ወሌ) በራሷ የያዘችው የፖለቲካ ሥልጣን አልነበረም። ኢያሱ ሥልጣን ሲይዝ ደግሞ እንደ ጣውንት ተቆጥራ ይመስላል ሰላሌ ውስጥ ፋሌ በሚባል ቦታ ተዘግታ እንድትቀመጥ ተገደደች። እንዲህ ከፖለቲካ ዓለም ተገላ የቆየችውን ወይዘሮ የ1909 ክሥተቶች ድንገት ወደ ዋናው የፖለቲካ መድረክ አወጧት። በሌላ ወገን፣ ምንም እንኳ አንዳንድ ጸሐፊዎች ተፈሪ ኢያሱን ለመፈንቀል ያደረገውን ሚና ያለቅጥ አጋነው ቢያቀርቡትም ከአድማው ተካፋዮች አንዱ መሆኑ አያጠራጥርም።

ሁለቱ የሥልጣን ተጋሪዎች በፖለቲካ ልምድ ብቻ ሳይሆን ባገኙት የትምህርት እድልም ይለያዩ ነበር። ዘውዲቱ በድሮ ወግ ቅዱሳት መጻሕፍት ከማንበብ የሚዘልቅ ትምህርት አላገኘችም። ተፈሪ ግን ጥቂት ዘመናዊ ቀመስ ትምህርት ነበረው። ይህንንም ለማግኘት የቻለው መጀመሪያ ሐረር አባ እንድርያስ በተባለው የፈረንሳይ ካቶሊክ ሚሲዮናዊ አማካይነት፣ ኋላ ደግሞ በዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት ነው። በተጨማሪም በሥራው ጠባይና በራሱም ዝንባሌ ምክንያት ከፈረንጆች መወዳጀት ያዘወትር በነበረው ባባቱ በራስ መኰንን አማካይነትና ራሱ የሐረር ገዥም በነበረበት ወቅት ከውጭ አገር ሰዎች ጋር በመገናኘት አድማሱን ለማስፋት ችሏል።

የማታ ማታ ግን የሥልጣኑ ፍጥጫ በዘውዲቱና በተፈሪ መካከል ብቻ ሳይሆን ባንድ ወገን በተፈሪና በአጋሮቹ ምሁራንና መኳንንት፣ በሌላ ወገን ደግሞ ዘውዲቱን የቀደሞው ወግና ሥርዓት የመቀጠሉ አለኝታና ምልክት አርገው በሚያዩ ወግ አጥባቂዎች መካከል ነበር። የወግ አጥባቂዎቹ ወገን መሪ መሆኑ የሚነገርለት ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ሲሆን፣ የአቡኑና የእጨጌውም መንፈሳዊ ድጋፍ አልተለየውም ነበር። በወግ አጥባቂዎቹና በተፈሪ መካከል የነበረው ልዩነት በጥቅሉ ሲታይ ኢትዮጵያ በነፃነት ባለችበት ቆማ ትቅር ወይስ



የውጭ ኃያላንን ተጠግታ ወደፊት ትራመድ በሚለው አማራጭ ላይ የሚሽከረከር ነበር። ቀደም ብለን የጠቀስነው የተፈሪና የምሁራኑ አጋርነት የመነጨውም ከዚሁ ሁኔታ ነው።

የተፈሪ ኰከብ ደመቅ ብሎ መብራት የጀመረው በ1916 ነው ማለት ይቻላል። በዚያን ዓመት ኢትዮጵያ የዓለም መንግሥታት ማኅበር አባል በመሆን ዓለም አቀፋዊ ዕውቅና ከማግኘቷም በላይ ተፈሪም ራሱ ከዓለም የተዋወቀበትን ታሪካዊውን የአውሮጳ ጉዞ አደረገ። ተፈሪ ራሱ ይህን ጉዞ ከፍተኛ ግምት ከመስጠቱ የተነሣ በሕይወት ታሪኩ ውስጥ 40 ገጽ ያህል ይሰጠዋል። ምንም እንኳ ለመፈጸም የተለማቸውን ሁሉ (በተለይም የባሕር በር የማግኘቱን ጉዳይ) ከግብ ሊያደርስ ባይችልም፣ ዓለም አቀፋዊ ዝናን አግኝቶ የአውሮጳን ሥልጣኔ ባገሩ ለማስፋፋት በነበረው ፍላጎትም ጸንቶ ነው የተመለሰው። ጉዞው ለሱ ብቻ ሳይሆን እሱን አጅበው ሄደው ለነበሩት አያሌ መኳንንትም ዐይን ገላጭ ነበር።

አልጋ ወራሽ የተባለ ልዑል የጊዜ ጉዳይ ነው እንጂ ንጉሠ ነገሥት መሆኑ የማይቀር ነው። (የአስፋ ወሰን ኃይለ ሥላሴን ክፉ ዕድል ለጊዜው ወደጎን ተወት አርገን ማለት ነው)። ይህ ሁኔታ በራሱ ተፈሪን ለፖለቲካ ሥልጣን የሚያተጋ ነበር። ተፈሪ ግን ይህን የመሰለ አትጊ ሁኔታ የሚያሻው አልነበረም። ዕውነተኛ ስሜቱንና ፍላጎቱን ለመደበቅ ባለው ከፍተኛ የተፈጥሮ ችሎታ እየታገዘ፣ በዝግታ፣ነገር ግን ባለማወላወል፣የዙፋኑን መንገድ ተያያዘው። ሥልጣኑን ለማጠናከር ከረዱት ሁኔታዎች የመጀመሪያው በ1910 የሚኒስትሮች መሾም ነው። ይህ ሁኔታ የተፈጠረውም እንደተለመደው በርእስ ብሔሩ ሹም ሽር ሳይሆን መሀል ሰፋሪዎች እንደገና በተሳተፉበት ሕዝባዊ ስብሰባ ነው።

በዚህ ሁሉ መሀል የተፈሪ ሚና ምን እንደነበር በውል ማወቁ ያስቸግራል። ይሁን እንጂ ሥር ሰደው የነበሩት ሚኒስትሮች በጅምላ ከሥልጣን መውረድ አገሪቱን በፈለገው ባዲስ መንገድ ለመምራት እንደሚያመቻቸው አጠራጣሪ አይደለም። የአድማው ተሳታፊዎች በእቤቱታቸው ተፈሪን እያሞገሱ ማውሳታቸው ተፈሪ ራሱ እንኳን ባይሆን ደጋፊዎቹ ከነገሩ በስተጀርባ እንደነበሩበት ይጠቁማል። ቢሆንም ተፈሪ አድማውን በሁለት ልብ ነበር የተመለከተው። ጥያቄው ለሱ አመቺ በመሆኑና ሕዝባዊ ድጋፍም ስለነበረው ለመቀበል ዝግጁነቱን ቢያሳይም ሕዝቡ እንዲህ በቀጥታ በፖለቲካ መሳተፉ ሳያስደነግጠው አልቀረም። ከጥቂት ወራት በፊት የተከናወነውን የሩሲያ አብዮት እያስታወሰም እንዲህ ዓይነቱ የሕዝብ ስብሰባ ምን ያህል ባገር ላይ ጉዳት ማስከተል እንደሚችል የገለጸላቸውም ለዚህ ነው። ስለዚህ ባጠቃላይ የተፈሪን አመለካከት ስንገመግም ለእንቅስቃሴው ቡራኬውን ባይነፍገውም በውስጡ ያዘለውን አደገኛ አዝማሚያዎች አልወደደውም ነበር።

በመጨረሻ ከጦር ሚኒስትሩ ከፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ በቀር ሚኒስትሮቹ በሙሉ እንዲሻሩ ተወሰነ። የሀብተ ጊዮርጊስን መትረፍ በሁለት መልክ ማየት ይቻላል። ባንድ በኩል ምናልባት እሱው ራሱ የአድማው አንቀሳቃሽ ስለነበረ ይሆናል። በሌላ በኩል ደግሞ አድማውን ያቀነባበሩት ተፈሪና ደጋፊዎቹ ከሆኑም ሀብተ ጊዮርጊስን የመሰለ ብርቱ የጦርና የፖለቲካ ሰው ገና በማሰዳው መተንኰሱ አያዋጣም ከሚል ግምት ይመስላል። ባጠቃላይም ምንም እንኳ ተፈሪና ሀብተ ጊዮርጊስ የሁለት ተፃራሪ ጎራ መሪዎች ቢሆኑም፣ ፊት



3.25 ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ዲነግዴ፣ የጦር ሚኒስትር

ለፊት የተጋጨበት ጊዜ ጥቂት ነው። በመካከላቸው የነበረው ቀዝቃዛ ጦርነት ያከተመው ሀብተ ጊዮርጊስ በታኅሣሥ 3፣ 1919 ሲሞት ነው። ተፈሪም ጊዜ ሳያጠፋ የጦር ሚኒስትሩን 15000 የሚደርሱ ጭፍራዎች መተዳደሪያቸው ከነበረው አገር ጋር በመውረስ ባንዴ የጦር ኃይሉንም ንብረቱንም ለማደርጀት ቻለ።

ተፈሪ ግልጽ ተቃውሞ መጀመሪያ ያጋጠመው ከፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ ሳይሆን ከደጃች ባልቻ አባ ነፍሶ ነው። በፖለቲካ ብልሀት ሳይሆን በጦረኛነቱ የታወቀው ባልቻ አድብቶ ተፈሪን ለመጥለፍ ከመሞከር ይልቅ ፊት ለፊት መጋፈጡን መረጠ። ተፈሪ የንግሥቲቱን ሥልጣን ቀስ በቀስ መገዝገዙ ካስቆጣቸው አንዱ የሆነው ባልቻ፣ በ1912 እነ በጅሮንድ ውብሸት ኃይሌ በተፈሪ ላይ ባነሣሡትና የፖሊሱ አለቃ እቃ ገብሩን ጨምሮ ብዙ መኳንንት በተሳተፉበት አድማ ተካፍሏል የሚል ጥርጣሬ ነበር። አድመኞቹ በተፈሪ ላይ ያቀረቡት ዋና ክስ አገሪቱን እየሸጠ ነው የሚል ሲሆን፣ለዚህም በማስረጃነት ያቀረቡት ለፈረንጆች ይሰጡ የነበሩ የሞኖፖል ውሎች ናቸው። የአድማው





3.26 ደጃች ባልቻ ሳፎ፣ የዐድዋ ጀግናና የተፈሪ መኩንን ቀንደኛ ባላንጣ

መሪዎች ምንም እርምጃ ከመውሰዳቸው በፊት ተይዘው በእስራትና ንብረት መወረስ ሲቀጡ ባልቻ ራሱን ከነገሩ ነፃ ለማውጣት ችሏል። ሆኖም ነገሩ ሞት ሊዘገይ የቀረ ይመስል እንደሚባለው ነበር። በአስተዳደግና በባሕርይ ተፈሪና ባልቻ የሚጣጣሙ አልነበሩም። ከዚያም በላይ ተፈሪ ለአጭር ጊዜ የሲዳሞ ገዥ ነበረበት ወቅት አንዳንድ የባልቻን ጭፍሮች ማስኮብለሉ፣ ሲዳሞን፣ በአፅመ ርስትነት ማለት ይቻላል፣ ይዞ የነበረውን ባልቻን አስቆጥቷል። የማታ ማታ ተፈሪ የቡና ባለፀጋ የሆነውን ግዛት ለመጠቅለል ሐሳብ አለው የሚል ጥርጣሬም ነበር። በዚህ ላይ ተፈሪ ቀስ በቀስ የንግሥት ዘውዲቱን ሥልጣን የሸረሸረ መምጣቱ ባልቻን በእምቢተኝነት እንዲነሣ ገፋፋው።

የቁርጡ ቀን በ1920 መጣ። ታማኝነቱን ለመፈተን ወደ አዲስ አበባ እንዲመጣ ከተፈሪ የተደረገለትን ጥሪ በሰበብ ባስባቡ ሲያዘገይ ከቆየ በኋላ፣ንግሥቲቱ የላከችለት የማግባቢያ ቃል በመጨረሻ ሐሳቡን አስቀይሮት ብልቅ ጦር መርቶ ወደ አዲስ አበባ መጣ። ጦሩን ከከተማው በስተደቡብ በሚገኝ በፉሪ ተራራ ላይ አስፍሮ እሱ ጥቂት ጭፍሮቹን አስከትሉ ወደ ግቢ ሄደ። ሱ በተፈሪ ላይ ያለውን ቅሬታና ጥላቻ በግልጽ ሲያሳይ፣ ተፈሪ ግን ሙግና ዳጁን እያቀረበለት ይህን የጥንት ጦረኛ የሚያርድበትን ቢላዋ ይስል ነበር።



3.25 ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ዲነግዴ፣ የጦር ሚኒስትር

ለፊት የተጋጩበት ጊዜ ጥቂት ነው። በመካከላቸው የነበረው ቀዝቃዛ ጦርነት ያከተመው ሀብተ ጊዮርጊስ በታኅሣሥ 3፣ 1919 ሲሞት ነው። ተፈሪም ጊዜ ሳያጠፋ የጦር ሚኒስትሩን 15000 የሚደርሱ ጭፍራዎች መተዳደሪያቸው ከነበረው አገር ጋር በመውረስ ባንዴ የጦር ኃይሉንም ንብረቱንም ለማደርጀት ቻለ።

ተፈሪ ግልጽ ተቃውሞ መጀመሪያ ያጋጠመው ከፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ ሳይሆን ከደጃች ባልቻ አባ ነፍሶ ነው። በፖለቲካ ብልሀት ሳይሆን በጦረኛነቱ የታወቀው ባልቻ አድብቶ ተፈሪን ለመጥለፍ ከመሞከር ይልቅ ፊት ለፊት መጋፈጡን መረጠ። ተፈሪ የንግሥቲቱን ሥልጣን ቀስ በቀስ መገዝገዙ ካስቆጣቸው አንዱ የሆነው ባልቻ፣ በ1912 እነ በጆሮንድ ውብሸት ኃይሌ በተፈሪ ላይ ባነሣሡትና የፖሊሱ አለቃ አቃ ገብሩን ጨምሮ ብዙ መኳንንት በተሳተፉበት አድማ ተካፍሏል የሚል ጥርጣሬ ነበር። አድመኞቹ በተፈሪ ላይ ያቀረቡት ዋና ክስ አገሪቱን እየሸጠ ነው የሚል ሲሆን፣ለዚህም በማስረጃነት ያቀረቡት ለፈረንጆች ይሰጡ የነበሩ የሞኖፖል ውሎች ናቸው። የአድማው





3.26 ደጃች ባልቻ ሳፎ፣ የዐድዋ ጀግናና የተፈሪ መኩንን ቀንደኛ ባላንጣ

መሪዎች ምንም እርምጃ ከመውሰዳቸው በፊት ተይዘው በእስራትና ንብረት መወረስ ሲቀጡ ባልቻ ራሱን ከነገሩ ነፃ ለማውጣት ችሏል። ሆኖም ነገሩ ሞት ቢዘገይ የቀረ ይመስል እንደሚባለው ነበር። በአስተዳደግና በባሕርይ ተፈሪና ባልቻ የሚጣጣሙ አልነበሩም። ከዚያም በላይ ተፈሪ ለአጭር ጊዜ የሲዳሞ ገዥ በነበረበት ወቅት አንዳንድ የባልቻን ጭፍሮች ማስኮብለሉ፣ ሲዳሞን፣ በእፅመ ርስትነት ማለት ይቻላል፣ ይዞ የነበረውን ባልቻን አስቆጥቷል። የማታ ማታ ተፈሪ የቡና ባለፀጋ የሆነውን ግዛት ለመጠቅለል ሐሳብ አለው የሚል ጥርጣሬም ነበር። በዚህ ላይ ተፈሪ ቀስ በቀስ የንግሥት ዘውዲቱን ሥልጣን እየሸረሸረ መምጣቱ ባልቻን በእምቢተኝነት እንዲነሣ ገፋፋው።

የቁርጡ ቀን በ1920 መጣ። ታማኝነቱን ለመፈተን ወደ አዲስ አበባ እንዲመጣ ከተፈሪ የተደረገለትን ጥሪ በሰበብ ባስባቡ ሲያዘገይ ከቆየ በኋላ፣ንግሥቲቱ የላከችለት የማግባቢያ ቃል በመጨረሻ ሐሳቡን አስቀይሮት ትልቅ ጦር መርቶ ወደ አዲስ አበባ መጣ። ጦሩን ከከተማው በስተደቡብ በሚገኘው በፋሪ ተራራ ላይ አስፍሮ እሱ ጥቂት ጭፍሮቹን አስከትሎ ወደ ግቢ ሄደ። እሱ በተፈሪ ላይ ያለውን ቅሬታና ጥላቻ በግልጽ ሲያሳይ፣ ተፈሪ ግን ጮማና ጠጁን እያቀረበለት ይህን የጥንት ጦረኛ የሚያርድበትን ቢላዋ ይስል ነበር።



3.27 በ1920 በራስ ተፈሪ ላይ ያመፀው ደጃች አባ ውቃው ብሩ

የመታውም መላ ባልቻ ከታማኝ ጭፍሮቹ ጋር ግቢ ሲፈነጥዝ ደጃች ብሩ ወልደ ገብርኤልን የሲዳሞ ገዥ አድርጎ ሹሞ ይህም ፋሬ በሰፈረው የባልቻ ጦር አካባቢ እንዲለፈፍ ማድረግ ነበር። ዐዋጁን ሲሰማ የባልቻ ጦር አብዛኛውን «ቀጥር ጦር» እየተባለ የሚታወቅ የንጉሠ ነገሥቱ ጦር በመሆኑ አዲሱን ገገር ተከትሎ ነጎደ። ከመቅጽበት ባልቻ ያለ ሠራዊት ቀረ። የቀረው ምርጫ እጅ መስጠት ነበር። የደጃች ብሩም ሹመት ለጊዜው ነበር። ከሦስት ዓመት በኋላ ተፈሪ ባለሀብቱን ግዛት ልጁን ልዕልት ተናኘ ወርቅን ሳገባው ለታማኙ ለራስ ደስታ ዳምጠው ሰጠው።

ቀጥሎ እያደገ የመጣውን የተፈሪን ሥልጣን የተፈታተነው የግቢ ዘበኞች አለቃ ደጃች አባ ውቃው ብሩ ነው። በምኒልክ ቤተ መንግሥት ያደገው አባ ውቃው ቀስ በቀስ ዋና መጠሪያ የሆነውን አስፈሪ የቅጽል ስም ያገኘው በአድሜ የሚበልጡትን ልጆች በትግል እያሸነፈ (እየወቃ) በንጉሠ ነገሥቱ ዘንድ ታዋቂነትን ስላገኘ ነው ይባላል። ለምኒልክ ያለው ፍቅርና አክብሮት በሕይወት ብቻ ሳይሆን ከንጉሠ ነገሥቱም ሞት በኋላ ቀጥሏል። በተፈሪ ላይ ሲነሣም






3.28 ራስ ጉግሣ ወሌ፣ የንግሥት ዘውዲቱ ባልና የቤጌምድር ገዥ

ንግሥት ዘውዲቱን ደግፎ ብቻ ሳይሆን ለምኒልክ ዐፅምና መንፈስ ያለው አክብሮት ገፋፍቶትም ጭምር ነው። ከዚህም ቀደም ሲል እንደነፊታውራሪ ገብረ ማርያም ያሉ የምኒልክ ታማኝ ሎሌዎች የንጉሠ ነገሥታችንን ግቢ አናስደፍርም ብለው መጀመሪያ ከራስ አባተ፣ ቀጥሎ ከልጅ ኢያሱ ጋር ያደረጉትን መፋጠጥ ያስታውሰናል። በ1905 ኢያሱ ግቢ አናስገባም ያሉትን ዘበኞች ሲያስርና ሲሸር አባ ውቃውን «የጉልበት ነገር ነው እንጂ የተንኰል ነገር አያውቅም፣ ክርስቲያን ነው» (ኢጥም 400) በማለት ነፃ ለቀቶ ነበር። ኢያሱ ከሥልጣን ከወረደ በኋላ የግቢ ዘበኞች አለቃ ከመሆኑም በላይ የለውጥ ሐዋርያ ሆኖ የሚጠራጠሩትን ለማሳመን በወሎ፣ በጉንደርና በጎጃም ተዘዋውሯል። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ግን በተፈሪና በዘውዲቱ መካከል የተፈጠረው የሥልጣን ሽኩቻ ያለማወላወል ከንግሥቲቱ ጎን እንዲሰለፍ አስገደደው።

የአባ ውቃውን አመፅ ያስነሣው መሀል ሰፋሪዎች ተፈሪ ንጉሥ እንዲባል በ1920 አጋማሽ ላይ የጀመሩት ቅስቀሳ ይመስላል። ከዚህም ሌላ ቀደም ሲል የወግ አጥባቂው ወገን አሁንም እንደ ዋና ጠላት ከሚቆጥራት ከኢጣልያ ጋር ተፈሪ ያደረገው የወዳጅነት ውልም ነገር ሳያባብስ አልቀረም። አንዳንድ መረጃዎች እንደሚጠቁሙትም፣ «ሀብተ ጊዮርጊስ ከሞተ ብሎ ተፈሪ አልጋውን ሊቀማኝ ነው» እያለች ዘውዲቱ የምታሰማው እሮሮ የአባ ውቃውን ልብ




3.27 በ1920 በራስ ተፈሪ ላይ ያመፀው ደጃች አባ ውቃው ብሩ

የመታውም መላ ባልቻ ከታማኝ ጭፍሮቹ ጋር ግቢ ሲፈነጥዝ ደጃች ብሩ ወልደ ገብርኤልን የሲዳሞ ገዥ አድርጎ ሹሞ ይህም ፋሪ በሰፈረው የባልቻ ጦር አካባቢ እንዲለፈፍ ማድረግ ነበር:: ዐዋጁን ሲሰማ የባልቻ ጦር አብዛኛውን «ቁጥር ጦር» እየተባለ የሚታወቅ የንጉሠ ነገሥቱ ጦር በመሆኑ አዲሱን ገዥ ተከትሎ ነጎደ:: ከመቅጽበት ባልቻ ያለ ሠራዊት ቀረ:: የቀረው ምርጫ እጅ መስጠት ነበር:: የደጃች ብሩም ሹመት ለጊዜው ነበር:: ከሦስት ዓመት በኋላ ተፈሪ ባለሀብቱን ግዛት ልጁን ልዕልት ተናኘ ወርቅን ሳገባው ለታማኙ ለራስ ደስታ ዳምጠው ሰጠው::

ቀጥሎ እያደገ የመጣውን የተፈሪን ሥልጣን የተፈታተነው የግቢ ዘበኞች አለቃ ደጃች አባ ውቃው ብሩ ነው:: በምኒልክ ቤተ መንግሥት ያደገው አባ ውቃው ቀስ በቀስ ዋና መጠሪያ የሆነውን አስፈሪ የቅጽል ስም ያገኘው በእድሜ የሚበልጡትን ልጆች በትግል እያሸነፈ (እየወቃ) በንጉሠ ነገሥቱ ዘንድ ታዋቂነትን ስላገኘ ነው ይባላል:: ለምኒልክ ያለው ፍቅርና አክብሮት በሕይወት ብቻ ሳይሆን ከንጉሠ ነገሥቱም ሞት በኋላ ቀጥሏል:: በተፈሪ ላይ ሲነሣም





3.28 ራስ ጉግሣ ወሌ፣ የንግሥት ዘውዲቱ ባልና የቤጌምድር ገዥ

ንግሥት ዘውዲቱን ደግፎ ብቻ ሳይሆን ለምኒልክ ዐፅምና መንፈስ ያለው አክብሮት ገፋፍቶትም ጭምር ነው:: ከዚህም ቀደም ሲል እንደነፈታውራሪ ገብረ ማርያም ያሉ የምኒልክ ታማኝ ሎሌዎች የንጉሠ ነገሥታችንን ግቢ አናስደፍርም ብለው መጀመሪያ ከራስ አባተ፣ ቀጥሎ ከልጅ ኢያሱ ጋር ያደረጉትን መፋጠጥ ያስታውሰናል:: በ1905 ኢያሱ ግቢ አናስገባም ያሉትን ዘበኞች ሲያስርና ሲሽር አባ ውቃውን «የጉልበት ነገር ነው እንጂ የተንኰል ነገር አያውቅም፣ ክርስቲያን ነው» (ኢጥም 400) በማለት ነፃ ለቀት ነበር:: ኢያሱ ከሥልጣን ከወረደ በኋላ የግቢ ዘበኞች አለቃ ከመሆኑም በላይ የለውጥ ሐዋርያ ሆኖ የሚጠራጠሩትን ለማሳመን በወሎ፣ በጐንደርና በጎጃም ተዘዋውሯል:: ከጥቂት ጊዜ በኋላ ግን በተፈሪና በዘውዲቱ መካከል የተፈጠረው የሥልጣን ሽኩቻ ያለማወላወል ከንግሥቲቱ ጎን እንዲሰለፍ አስገደደው::

የአባ ውቃውን አመፅ ያስነሣው መሀል ሰፋሪዎች ተፈሪ ንጉሥ እንዲባል በ1920 አጋማሽ ላይ የጀመሩት ቅስቀሳ ይመስላል:: ከዚህም ሌላ ቀደም ሲል የወግ አጥባቂው ወገን አሁንም እንደ ዋና ጠላት ከሚቆጥራት ከኢጣልያ ጋር ተፈሪ ያደረገው የወዳጅነት ውልም ነገር ሳያባብስ አልቀረም:: አንዳንድ መረጃዎች እንደሚጠቁሙትም፣ «ሀብተ ጊዮርጊስ ከሞተ ብሎ ተፈሪ አልጋውን ሊቀማኝ ነው» እያለች ዘውዲቱ የምታሰማው እሮሮ የአባ ውቃውን ልብ

ነክቶታል:: ይሁንና እርምጃውን የወሰደው በሷ ቆስቋሽነት ወይም አደፋፋሪነት ሳይሆን በራሱ ውሳኔ ይመስላል:: ተቃውሞውን ይፋ ለማድረግ የመረጠው ምሽግም ግቢ ውስጥ የምኒልክ ዐፅም ካረፈበት የምኒልክ መታሰቢያ ቤት ተብሎ ከታወቀው ስፍራ ነው:: የምኒልክን ቅርስ ለማስከበር ታጥቆ ለተነሣ ሰው ከዚያ የተሻለ መድረክ ማሰብም ይቸግራል:: ከተከታዮቹ ጋር በዚያ መሽጎ መሣሪያውን በመጥመድ አንድ ሰው አላስቀርብም አለ:: ተፈሪም ለመተኩስ እንኳ ባይሆን ለማስፈራራት በአገሪቷ ታሪክ የመጀመሪያው የሆነውን ታንክ በመታሰቢያ ቤት ፊት ለፊት ጠመደ:: አባ ውቃው ለግልግል የተላኩ ሽማግሌዎችን ሁሉ እየሰደበና እያሳፈረ መለሰ:: ነገሩ የተፈታው ተፈሪ ዘውዲቱ ጋ ሄዶ እሷን ስለሚስማት ታማኝ አሽከሯን ከመሸገበት እንዲወጣ ሰው እንድትልክበት ሲያግባባት ነው:: አባ ውቃው በርግጥም የላከችበት ንግሥቲቱ መሆኗን ስለተጠራጠረ ለዚሁ ሲባል ወደ መታሰቢያ ቤቱ የስልክ መስመር ተዘርግቶ፣ ንግሥቲቱ ምንም ሥጋት እንደሌለባትና እሱም ወርዶ እጁን እንዲሰጥ ከገዛ አንደበቷ ስለሰማ፤ ድሮውኑም ለንግሥቲቱ ብዬ ነው እንጂ ምን ቸገረኝ ብሎ እጁን ሰጠ:: ተፈሪም እንኳን ብቻ በጀ ገባህልኝ ብሎ ወዲያው ለፍርድ አቀረበው:: የሞት ፍርድ ከተፈረደበት በኋላም ወደ እስራት ተለወጠለት::

በከተማይቱ ለጥቂት ቀናት ሰፍኖ የነበረው ውጥረት ሲረግብ፣ በአባ ውቃው መያዝ የተደፋፈሩት የተፈሪ ደጋፊዎች እንደገና ድምፃቸውን ማሰማት ጀመሩ:: የከተማው ከንቲባና የተፈሪ ቡድን አቀነባባሪ በነበረው በነሲቡ ዛማኑኤል እየተመሩ ተፈሪ ንጉሥ እንዲባል በይፋ ጠየቁ:: የተዋከበችው ንግሥትም ለተፈሪ የንጉሥነት ማዕረግ ከመስጠት ሌላ አማራጭ አልነበራትም:: ንጉሥነቱም እንደተለመደው ባንድ ክፍለ ሀገር ላይ ሳይሆን እንዲያው በደፈናው ስለነበር በጠቅላላው ባገሪቱ ላይ ዋና ባለሥልጣን ለመሆኑ ሕጋዊ ማረጋገጫ ሆነ:: በመስከረም 27፣ 1921 የውጭ አገር መንግሥታት ልዑካን በተገኙበት የተከናወነው የንግሥ በዓልም ከሁለት ዓመት በኋላ (ጥቅምት 23፣ 1923) ለሚደረገው የንጉሠ ነገሥትነት በዓል ማሟሻ ነበር ማለት ይቻላል::

ከዚህ በኋላ በተፈሪና በንጉሠ ነገሥትነቱ ዘውድ መካከል የቀረው ግርዶሽ የበጌምድሩ ገዥና የዘውዲቱ ባል ራስ ጉግሣ ወሌ ነበር:: ጉግሣ ኢያሱን ከሥልጣን ያወረደው የ1909ኙ የፖለቲካ ውሳኔ ተጠቃሚ መሆን ሲገባው ከመጀመሪያዎቹ ተጎጅዎች አንዱ ሆነ:: ዘውዲቱ እንድትነግሥ ሲወሰን፤ ጣይቱ ተልማ እንደነበረችው ሁሉ ጉግሣ በባልነቱ ታላቁን የፖለቲካ ሥልጣን ለመጨበጥ የቻለ መስሎ ነበር:: ነገር ግን ያጋጣሚው አደገኛነት ከሸዋ መኳንንት የተሰወረ አልነበረም:: ስለሆነም ዘውዲቱ ዙፋን ላይ ስትወጣ ከምትወደው ባሏ እንድትለያይ ተደርጎ ጉግሣም ወደ ቀድሞ ግዛቱ ወደ በጌምድር ተመለሰ:: ይህን ተንኰል የጐነጐነው ተፈሪ ነው በሚል እምነትም ጸንቶ ቆየ::

ይሁን እንጂ ጉግሣ በተፈሪ ላይ ያመፀው በግል ቂም ብቻ ተነሣሥቶ አይደለም:: ለግጭቱ ተጨማሪ መንሥኤዎችም ነበሩ:: ቀደም ብለን የጠቀስነው በዘመኑ በወግና በለውጥ መካከል የነበረው ተቃርኖ የተካረረ ደረጃ ደረሰ ሊባል የሚችለው በሁለቱ ሰዎች ግጭት ነው:: ራሱን እንደ ኦርቶዶክስ እምነት ሐቀኛ ጠበቃ አርጎ ያቀረበው ጉግሣ፣ ተፈሪና የሸዋ ተከታዮቹ የውሻ ሥጋ ይበላሉ ብሎ ከሰሳቸው:: ተፈሪ ደግሞ በኢትዮጵያ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ አውሮፕላን በመጠቀም በጉግሣ ሠራዊት ላይ መጀመሪያ የፕሮፖጋንዳ ወረቀቶች፣ ቀጥሎ ቦምብ አዘነበባቸው:: ይህ የአመለካከታቸው ልዩነት አንድ ጉልህ ማስረጃ ነው::




በተጨማሪ ተፈሪ በተለመደ ጥበቡ ጉግሣ በራሱ ግዛት የነበረውን ሥልጣን እየገዘገዘ እንደ ደጃች አያሌው ብሩ (የስሜኑ ገዥ) ያሉትን ዘመዶቹን ሳይቀር አስከድቶ ጉግሣን ብቻውን አስቀረው:: ነገሩን ጠለቅ ብለን ስናየው የሁለቱ ግጭት ኢኮኖሚያዊ መሠረትም ስለነበረው ይዋል ይደር እንጂ መፈንዳቱ የማይቀር ነበር:: ተፈሪ ወደየከፍላተ ሀገሩ የአስተዳደርና የፋይናንስ መረቡን ለመዘርጋት የሚያደርገው ጥረት ዞሮ ዞሮ ለሱ ፀር መሆኑን ስለሚያውቅ ጉግሣ መቃወሙ የማይቀር ነበር:: ለምሳሌም ሁለቱን ካጋጩዋቸው ነገሮች አንዱ የመተማ ጉምሩክ በማን ቁጥጥር ሥር ይሁን የሚለው ጥያቄ ነው::

በተጨማሪም ጉግሣን ለአመፅ በመጐትጐቱ ላይ የጣልያኖችና የጐረቤቶቹ የጐጃሙ ራስ ኃይሉና የትግሬው ራስ ሥዩም ሚና ሳይጠቀስ የሚታለፍ አይደለም:: የጉግሣ ዕጣ የሚያሳዝነው ግን፣ ኃይሉና ሥዩም መጐትጐቱ ላይ እንጂ አብሮ መሰለፉ ላይ አለመኖራቸው ነው:: ቆቅ ስለሆኑ ሃይ ሃይ ብለው አስነሥተው ጦርነት እፍጠ ሲመጣ ገሸሽ አሉ:: ይህንን ሁኔታ ነው የጉግሣ አዝማሪ ምስጋናው አዱኛ ከአንችም ጦርነት በኋላ ልብ በሚነካ ሙሾ የገለፀው፤

ከኛይቱ ወረቀት ያልፈረመ የለም፣
መላው ታጥቆ ገባ ግዴለም ግዴለም፣
ትግሬም ገባ አሉ ሰምቶ በፍጥነት፣
ጎጃምም ገባ አሉ ሰምቶ በፈጥነት፣
የወሌውን ጉግሣ ሞኙን የኔ ጌታ መፈተኛ አርጎት::

ለጦርነቱ ሰበብ የሆነው ጉግሣ ከተፈሪ ለሚመጡለት ትእዛዞች ያሳየው እምቢተኝነትና ዳተኝነት ነው:: በመጀመሪያ ጉግሣ ወረኢሉ መጥቶ እንዲገናኘው (ማለትም ታማኝነቱን እንዲገልጽ) ተፈሪ ተደጋጋሚ ጥሪ ቢያቀርብለትም አሻፈረኝ ብሎ ቀረ:: በመጨረሻም ተፈሪ የጉግሣን እምቢተኝነት ገሃድ ለማውጣት ብሎ በዚያን ወቅት በኢኮኖሚ ችግር ተነሣሥቶ የአፋርን ግዛት በመውረር በመንግሥት ላይ እምቦ የነበረውን የራያና አዘቦ ግዛት ፀጥ እንዲያስደርግ ላከበት:: ጉግሣም አመፀኞቹን ከመቅጣት ይልቅ ከነሱ ጋር መተባበር ጀመረ:: በዚህን ጊዜ ተፈሪ በቂ ምክንያት አግኝቶ በጦር ሚኒስትሩ በደጃች (ኋላ ራስ) ሙሉጌታ ይገዙ የሚመራ ጦር ላከ:: የነገሩ አካሄድ ስላላማራት ባሏን ጉግሣን ከጥፋት ለማዳን ንግሥቲቱ በደብዳቤ ለተፈሪ አሜን ብሎ እንዲገባ መወትወት ጀመረች:: ጉግሣ ግን ጦር በመግጠሙ ስለቆረጠ ፍንክችም አላለም:: የአንችም ጦርነት (ቋና ወይም ዘቢጥም ተብሎ ይታወቃል) በመጋቢት 22፣ 1922 ሆነ:: የተፈሪ ጦር በሠራዊት ብዛትና በጦር መሣሪያም ብልጫ ከማሳየቱም በላይ፣ ከፍተኛ ሥነ ልቡናዊና ቁሳዊ የበላይነት ያረጋገጡለት የጦር አወሮፕላኖችም ነበሩት:: ቢሆንም የጉግሣ ጦር መሪው ከወደቀም በኋላ በልበ ሙሉነት ውጊያውን ቀጠለ:: በመጨረሻ ከመሸነፍ ግን አልዳነም:: ከሁለት ቀን በኋላም የባሏ ፍቅር ከልቧ ያልጠፋው ንግሥት ዘውዲቱ የነበረባት ሕመም በድንጋጤ አገርሽቶባት ይመስላል ሕይወቷ አለፈች:: ተፈሪ ፊት የተደቀነው ፖለቲካዊና ወታደራዊ መሰናክልም እንዲህ ባንድ ጊዜ ተወገደ:: ተፈሪ ኃይለ ሥላሴ ሆነ::



3.29 የአንችም ጦርነት

### የፍጹማዊ አገዛዝ መመሥረት /1923-1928/

የኃይለ ሥላሴ ሥርዓተ ንግሥ ዘውዲቱ በሞተች በሰባተኛው ወር ተከናወነ:: በመሀል ያለው ጊዜ በኢትዮጵያ ታሪክ ታይቶ የማይታወቅና ፍጹማዊ አገዛዝ የሚጠይቀውን የንግሥ በዓል ማዘጋጃ ወቅት ሆነ:: በ1916 ተፈሪ አያሌ ያውሮጳ አገሮችን መጐብኘቱ ለንጉሣዊ አጀብና ለሽብርቅ ያለውን ግምት ከፍ አድርጎታል:: ስለዚህም ለእንዲህ ያለው ወቅት አግባብ አለው ተብሎ ንጉሠ ነገሥቱና እቴጌዋ የሚጓዙበት ሠረገላ ከጀርመን ንጉሣዊ ቤተ ሰብ መጥቶ ነበር:: ልብሱ ሁሉ በወርቅና በሐር ተሽቆጥቁጦ ነበር:: አዲስ አበባም የማሽብረቅ ዘመቻ ተከፍቶባት ሌላ መልክ ያዘች:: አጠያፊ ቤቶችና መንደሮች ተወገዱ፣ ቤተ መንግሥቱም በኤሌክትሪክ ብርሃን ደመቀ:: መንገዶች አስፋልት፣ ፖሊሶችም አዲስ ዩኒፎርም ለበሱ:: አዲስ አበባም ከመለያዎቿ አንዱ የሆነውን የምኒልክን የፈረሰኛ ሐውልት ያገኘችው በዚሁ ጊዜ ነው:: በዓሉ ዓለም አቀፍ ትኩረትን በከፍተኛ ደረጃ የሳበም ነበር:: ኢጣልያን በመወከል የሳቮይ ልዑል፣ እንግሊዝን በመወከል ደግሞ የግሉስተር መስፍን ተገኝተዋል:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስከ ጣልያን ወረራ ድረስ ከኢትዮጵያ ያልተለዩት ጋዜጠኞችም በብዛት መጥተዋል:: ዝነኛው የእንግሊዝ ደራሲ ኤቭሊን ዎውም በበዓሉ ላይ ተገኝቶ ለመጪው ትውልድ ትዝታዎቹን ቀምሞ ለመተው በቃ::

የተፈሪ የፖለቲካ ቁመና መለወጥ የጀመረው ግን ገና ንጉሠ ነገሥት ከመሆኑ በፊት ነው:: በ1921 ንጉሥ ከተባለ ወዲህ ጋዜጦችም የቀድሞ ነፃነታቸው እየኰሰሰ ተፈሪን ማወደስ ጀምረዋል:: ሥርዓተ ንግሡ የተፈጸመበት ጥቅምት 23፣ 1923 የሂደቱ ማሳረጊያ እንጂ መጀመሪያ አልነበረም:: እንደዚህ ፍጹማዊ ሥልጣን ከጨበጠ በኋላ የዘመነ መሳፍንት ቅሪቶችን የማስወገዱን ጉዳይ ሥራዬ ብሎ ተያያዘው:: ቴዎድሮስ አሐዳዊ መንግሥት ለመመሥረት ሞክሮ እንደከሸፈበት አይተናል:: ዮሐንስና ምኒልክም ከዚህ ትምህርት ወስደው ነው ይመስላል ከክልላዊ አገዛዝ ጋር ታርቆ መኖርን መርጠዋል:: የተናቁትንና የተጠሉትን አቀርባለሁ የሚለው ለጊዜው እንግዳ የሆነው የኢያሱ ሙከራም ዙፋኑን እስከማጣት አብቅቶታል:: ከዚህ ሁሉ አንፃር ኃይለ ሥላሴ በታሪክ ከሚታወቅባቸው ነገሮች አንዱ ቴዎድሮስ ያለመውን አሐዳዊ መንግሥት እውን ማድረጉ ነው:: ይህም ሁኔታ ነው ከሕይወት ታሪኩ (ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ) እንደምንረዳው ንጉሠ ነገሥቱ ራሱን እንደ ፀረ ፊውዳል ታጋይ እንዲቆጥር ያደረገው:: ይህም የፊውዳሊዝምን መሠረታዊ ኢኮኖሚያዊ ይዘት ካለማጤን የመጣ አስተሳሰብ ነው:: እንደ እውነቱ ከሆነ ግን ኃይለ ሥላሴ ይታገል የነበረው ፊውዳሊዝምን ለማስወገድ ሳይሆን ባንድ ወገን የንጉሡን ሥልጣን አጠናክሮ በሌላ ወገን ደግሞ የመሳፍንቱን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም አስከብሮ ፊውዳሊዝምን በአዲስ መሠረት ላይ ለማቆም ነው:: በኢትዮጵያ የፍጹማዊ አገዛዝ ዓይነተኛ ባሕርይም ይኸው ሆነ::

ከሁሉም በፊት ግን ይህ አገዛዝ ሕጋዊ መሠረት ያስፈልገው ነበር:: ይህን ያገኘውም በ1923 በታወጀው ሕገ መንግሥት አማካይነት ነው:: ሕገ መንግሥቱ ከመታወጁ አስቀድሞ የነበረው ክርክርም በማዕከላዊነትና በክልላዊነት መካከል የነበረውን ትግል አጉልቶ የሚያሳይ ነው:: ከራስ እምሩ ኃይለ ሥላሴ በስተቀር መሳፍንቱ ክልላዊ ሥልጣን ተከብሮ እንዲቆይ ተሟጋች ነበሩ:: በሌላ በኩል ደግሞ ሚኒስትሮቹና መኳንንቱ የመደብ ጥቅማቸው እየሳባቸው ሹመት በሥራ እንጂ በትውልድ መሆን የለበትም ባዮች ሆኑ:: በመጨረሻ በንጉሠ



ነገሥቱ የቀረበው አስታራቂ ሐሳብ በግልጽ ለማዕከላዊነት ያደላ ሲሆን፣ ለመሳፍንቱ ካሣ እንዲሆን አገልግሎታቸው እየታየ የርስት ጉልት መብታቸው የሚጠበቅላቸው መሆኑን የሚያረጋግጥ ነበር::

የአፄ ኃይለ ሥላሴ ሕገ መንግሥት ማወጅና የምኒልክ ሚኒስትሮችን መሾም በተመሳሳይ አጋጣሚዎች የተከናወኑ ድርጊቶች ናቸው:: እንደ ሚኒስትሮቹ መሾም ሁሉ የሕገ መንግሥቱም መታወጅ ባንድ መልኩ ለፈረንጆች የኢትዮጵያን ዘመናዊነት ለማሳየት ታቅዶ የተደረገ ይመስላል:: ምክንያቱም የሕገ መንግሥቱ አንዳንድ አንቀጾች ለሚኒስትሮች እንደወጡት ደንቦች ሁሉ ሥራ ላይ መዋላቸው አጠራጣሪ ስለነበረ ነው:: ሁለተኛ የሕገ መንግሥቱ አንድ ዓላማ ምኒልክ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶችን ሲያቋቁም እንደነበረው ሁሉ፣ የወራሴ መንግሥትን ጥያቄ ለመፍታት ነው:: የሕገ መንግሥቱ የመጀመሪያዎቹ አንቀጾችም በዚሁ ላይ ያተኰሩ ናቸው:: በዚህም ረገድ ይህንን አወዛጋቢ ጥያቄ ሕጋዊ መፍትሔ ለመስጠት የተደረገው የመጀመሪያ ሙከራ ነበር ማለት ይቻላል:: ቀድሞማ የአልጋ መውረስ ጥያቄ የሚፈታው በሕጋዊ አንቀጽ ሳይሆን ተቀናቃኝ የተባለውን ቤተ ዘመድ ሁሉ በሞት ወይ በእስር በማስወገድ ነበር::

በ1948 እንደገና ታድሶ የወጣው ሕገ መንግሥት ይህን የወራሴ መንግሥት ጥያቄ ከበፊተኛው በበለጠና በተብራራ ሁኔታ ለመፍታት ሞክሯል:: የሚገርመው ነገር ግን ይኸ ሁሉ ጭንቀት መና ሆኖ መቅረቱ ነው:: ምክንያቱም፣ ሁላችንም እንደምናውቀው አፄ ኃይለ ሥላሴ የመጨረሻው «ሰሎሞናዊ» ንጉሥ ሆኖ ቀርቷልና:: ሌላው የሕገ መንግሥቱና እሱም ያቋቋመው ምክር ቤት ሚና ብሔራዊ አንድነትን ለማመቻቸት ነው:: ፓርላማ በአንድነት ትምህርት ቤት የሚመሰል ሆኖ ነው የቀረበው:: ይህንንም ንጉሠ ነገሥቱ የመጀመሪያውን ፓርላማ ሲከፍት ካደረገው ንግግር በግልጽ ለመረዳት እንችላለን::

ሕገ መንግሥቱ ያተኰረበት ዋነኛ ነጥብ በንጉሠ ነገሥቱና በመሳፍንቱ መካከል የሚኖረውን የሥልጣን ሚዛን መደንገጉ ላይ ነው:: የሕዝቡ ጉዳይ ተቀጽላ ነበር:: የሕዝቡን መብትና ግዴታዎች የሚገልጹ አንዳንድ አንቀጾች የገቡትም እንዲህ ዓይነት አንቀጾች የሌሉትን ሕገ መንግሥት ሰው ፊት ማቅረብ ስለማይቻል ይመስላል:: የሕገ መንግሥቱ መግቢያ ይህንን ሁኔታ እንዲህ ሲል ይጠቀማል፤


> እንግዲህ ከዚህ በላይ የተጻፉት ማስረጃዎች ተዘርዝረው የንጉሠ ነገሥቱ ክብሩና ጥቅሙ ኃይሉና የሚገባው መብቱ ለዘሩ የማይፋለስበትን ውሰታ፣ እንደዚሁም ለመሳፍንቱና ላቅኛዎቹ ለመኳንንቶቹ ክብራቸውና ጥቅማቸው ለዘራቸው የሚያልፍበት፣ እንደዚሁም ደግሞ በኛ መካከል ይኸንን ሕግ ስናቆም ሕዝብም የኢትዮጵያ ተወላጅ ስለመሆኑና ኢትዮጵያን ስለመውደዱ የሚገባውን ጥቅምና መብት ማግኘት የሚያስፈልገው ነውና፣ ከዚህ ቀጥሎ ባለው ሕገ መንግሥት ውስጥ የሁሉም ዝርዝሩ ይገኛል:: (ማኅተመ ሥላሴ፣ 763፣ ስርዝ የተጨመረ)

ሁለት ምክር ቤቶች ያሉት ፓርላማ አባሉች አመራረጥም ሕዝቡ ለቀጥተኛ የፖለቲካ ተሳትፎ ገና አልበቃም ከሚል እምነት የመነጨ ነው። የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት አባላት መሳፍንትና መኳንንት ሲሆኑ እነሱም በቀጥታ በንጉሠ ነገሥቱ የሚሰየሙ ናቸው። የሕግ መምሪያ ምክር ቤት አባላትም ቢሆኑ በቀጥታ በሕዝቡ የሚመረጡ ሳይሆኑ ሕዝቡ በመረጣቸው መራሎች የሚሰየሙ (ባለመሬት የሆኑ) ነበሩ። የፓርላማ አባል ለመሆን የሚያስፈልገው የብቃት መመዘኛ ንብረት ተራውን ሰው ብቻ ሳይሆን ሀብታም ነጋዴዎችንም የሚያገል ነው። የሕገ መንግሥቱ ደራሲ በጅሮንድ ተክለ ሐዋርያት ሕገ መንግሥቱ ሲታወጅ ባደረገው የውዳሴ ንግግር ለኢትዮጵያ የሚያስፈልጋት በሕግ የተገደበ ንጉሣዊ አገዛዝ መሆኑን ለማሳየት ይጥራል። ሕገ መንግሥቱም ይህን አረጋግጧል የሚል እምነት ያለው ይመስላል። ዲሞክራሲ ግን ከጥያቄ ውጭ ነበር። ተክለ ሐዋርያት እንዳለው «እንደዚህ ያለው የመንግሥት አኳኋን (ማለትም ዲሞክራሲ) በጣም ላልተማረና ላልሰለጠነ ሕዝብ የሚፈቀድ አይደለም። ለሠለጠኑትም ሕዝቦች እንኳ ደም እያፋሰሰ በጣም አስቸግሮ ይኖራል።» (ማኅተመ ሥላሴ፤ 804)

በሕገ መንግሥቱ፣ ንጉሠ ነገሥቱ ለመሾምና ለመሻር፣ ፍርድ ለመስጠት፣ ጦርነት ለማወጅና ለማቆም፣ መሬትና የክብር ማዕረጎች ለመስጠት ያለው ፍጹማዊ ሥልጣን በማያሻማ ሁኔታ ተረጋግጧል። መሳፍንቱ ቀድሞ ያደርጉ እንደነበረው ከውጭ መንግሥታት ጋር ውል ለመዋዋልም ሆነ ያለ ንጉሠ ነገሥቱ ፈቃድ መሣሪያና ሽልማት ለመቀበል አልተፈቀደላቸውም። ነገሩን ታሪካዊ ድራማ ያጎናጸፈው ይህን የፖለቲካ ሞታቸውን ያረጋገጠውን ሕገ መንግሥት መሳፍንቱ በተራ ተሰልፈው እንዲፈርሙ መደረጋቸው ነው። የፊርማው ስነ ሥርዓት የሚያረጋግጠው ሌላ ነገር ከላይ እንደጠቀስነው ሕገ መንግሥቱ በመሠረቱ በንጉሠ ነገሥቱና በመሳፍንቱ መካከል የተደረገ ውል መሆኑን ነው። መሳፍንቱና መኳንንቱ የመወሰኛውና የመምሪያው ምክር ቤት አባል ሆነው እንዲሠሩ ቢመረጡም፣ድንበር እንዳያልፉ ለንጉሠ ነገሥቱ ታማኝነታቸውን ያረጋገጡ ባለሟሎች የምክር ቤቶቹ ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንት ሆነው ተሰይመውባቸው ነበር። ለምሳሌ የመወሰኛው ምክር ቤት ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንት ሁለቱም ከመሳፍንት ዘር ያልተወለዱናየሥልጣን እድገታቸውን ለንጉሠ ነገሥቱ ባላቸው ታማኝነት ያገኙ ነበሩ፤ የመጀመሪያው ቢትወደድ ወልደ ጻድቅ ጎሹ፣ የሁለተኛው ደግሞ ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ ነበሩ። ጽዳሉ። እነዚህ ሹማምንት እንደነራስ ካሣ ኃይሉ፣ ራስ ኃይሉ ተክለ ሃይማኖትና ራስ ሥዩም መንገሻን የመሳሰሉ መሳፍንት እንዲዳኙ መደረጋቸው መሳፍንቱ ምን ያህል በንጉሠ ነገሥቱ መዳፍ ሥር እንደወደቁ ጉልህ ማስረጃ ነው። በመሠረቱ መሳፍንቱ ከሥልጣን ተቀናቃኝነት ወደ ማዕከላዊው መንግሥት ሥልጣን አስተላላፊ በይነት ተለውጠዋል ማለት ነው። የሕገ መንግሥቱ አርቃቂ በጅሮንድ ተክለ ሐዋርያት ከብዙ ዓመታት በኋላ ትዝታውን በቃለ መጠይቅ ሲያካፍል ይህንኑ እውነታ ነው ያረጋገጠው።

> በዚያን ወቅት የኛ ፍላጎት የፓርላማ አባላት በደንብ እንዲሠሩ ወይ ዘመናዊ ሕግ እንዲያወጡ አልነበረም። እኛ የፈለግነው ሕዝቡ መንግሥት የሚያወጣውን ሕግ እንዲቀበልልን






3.30 ለመጀመሪያው ፖርላማ ንጉሠ ነገሥቱ አፄ ኃይለ ሥላሴ ንግግር ሲያደርግ

ሁለት ምክር ቤቶች ያሉት ፓርላማ አባሎች አመራረጥም ሕዝቡ ለቀጥተኛ የፖለቲካ ተሳትፎ ገና አልበቃም ከሚል እምነት የመነጨ ነው። የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት አባላት መሳፍንትና መኳንንት ሲሆኑ እነሱም በቀጥታ በንጉሠ ነገሥቱ የሚሰየሙ ናቸው። የሕግ መምሪያ ምክር ቤት አባላትም ቢሆኑ በቀጥታ በሕዝቡ የሚመረጡ ሳይሆኑ ሕዝቡ በመረጣቸው መራጮች የሚሰየሙ (ባለመሬት የሆኑ) ነበሩ። የፓርላማ አባል ለመሆን የሚያስፈልገው የብቃት መመዘኛ ንብረት ተራውን ሰው ብቻ ሳይሆን ሀብታም ነጋዴዎችንም የሚያገል ነው። የሕገ መንግሥቱ ደራሲ በጅሮንድ ተክለ ሐዋርያት ሕገ መንግሥቱ ሲታወጅ ባደረገው የውዳሴ ንግግር ለኢትዮጵያ የሚያስፈልጋት በሕግ የተገደበ ንጉሣዊ አገዛዝ መሆኑን ለማሳየት ይጥራል። ሕገ መንግሥቱም ይህን አረጋግጧል የሚል እምነት ያለው ይመስላል። ዲሞክራሲ ግን ከጥያቄ ውጭ ነበር። ተክለ ሐዋርያት እንዳለው «እንደዚህ ያለው የመንግሥት አኳኋን (ማለትም ዲሞክራሲ) በጣም ላልተማረና ላልሰለጠነ ሕዝብ የሚፈቀድ አይደለም። ለሠለጠኑትም ሕዝቦች እንኳ ደም እያፋሰሰ በጣም አስቸግሮ ይኖራል።» (ማኅተመ ሥላሴ፣ 804)

በሕገ መንግሥቱ፣ ንጉሠ ነገሥቱ ለመሾምና ለመሻር፣ ፍርድ ለመስጠት፣ ጦርነት ለማወጅና ለማቆም፣ መሬትና የክብር ማዕረጎች ለመስጠት ያለው ፍጹማዊ ሥልጣን በማያሻማ ሁኔታ ተረጋግጧል። መሳፍንቱ ቀድሞ ያደርጉ እንደነበረው ከውጭ መንግሥታት ጋር ውል ለመዋዋልም ሆነ ያለ ንጉሠ ነገሥቱ ፈቃድ መሣሪያና ሽልማት ለመቀበል አልተፈቀደላቸውም። ነገሩን ታሪካዊ ድራማ ያጎናጸፈው ይህን የፖለቲካ ሞታቸውን ያረጋገጠውን ሕገ መንግሥት መሳፍንቱ በተራ ተሰልፈው እንዲፈርሙ መደረጋቸው ነው። የፊርማው ስነ ሥርዓት የሚያረጋግጠው ሌላ ነገር ከላይ እንደጠቀስነው ሕገ መንግሥቱ በመሠረቱ በንጉሠ ነገሥቱና በመሳፍንቱ መካከል የተደረገ ውል መሆኑን ነው። መሳፍንቱና መኳንንቱ የመወሰኛውና የመምሪያው ምክር ቤት አባል ሆነው እንዲሠሩ ቢመረጡም፣ድንበር እንዳያልፉ ለንጉሠ ነገሥቱ ታማኝነታቸውን ያረጋገጡ ባለሟሎች የምክር ቤቶቹ ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንት ሆነው ተሰይመውባቸው ነበር። ለምሳሌ የመወሰኛው ምክር ቤት ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንት ሁለቱም ከመሳፍንት ዘር ያልተወለዱናየሥልጣን እድገታቸውን ለንጉሠ ነገሥቱ ባላቸው ታማኝነት ያገኙ ነበሩ፣ የመጀመሪያው ቢትወደድ ወልደ ጻድቅ ጎሹ፣ የሁለተኛው ደግሞ ብላቴን ጌታ ሣህሌ ጸዳሉ። እነዚህ ሹማምንት እንደነራስ ካሣ ኃይሉ፣ ራስ ኃይሉ ተክለ ሃይማኖትና ራስ ሥዩም መንገሻን የመሳሰሉ መሳፍንት እንዲዳኙ መደረጋቸው መሳፍንቱ ምን ያህል በንጉሠ ነገሥቱ መዳፍ ሥር እንደወደቁ ጉልህ ማስረጃ ነው። በመሠረቱ መሳፍንቱ ከሥልጣን ተቀናቃኝነት ወደ ማዕከላዊው መንግሥት ሥልጣን አስተላላፊ በይነት ተለውጠዋል ማለት ነው። የሕገ መንግሥቱ አርቃቂ በጅሮንድ ተክለ ሐዋርያት ከብዙ ዓመታት በኋላ ትዝታውን በቃለ መጠይቅ ሲያካፍል ይህንኑ እውነታ ነው ያረጋገጠው።

> በዚያን ወቅት የኛ ፍላጎት የፓርላማ አባላት በደንብ እንዲሠሩ ወይ ዘመናዊ ሕግ እንዲያወጡ አልነበረም። እኛ የፈለግነው ሕዝቡ መንግሥት የሚያወጣውን ሕግ እንዲቀበልልን





3.30 ለመጀመሪያው ፓርላማ ንጉሠ ነገሥቱ አፄ ኃይለ ሥላሴ ንግግር ሲያደርጉ



3.31 የ1923ቱ ሕገ መንግሥት አርቃቂ በጅሮንድ ተክለ ሐዋርያት

ነው። ይህንንም ተቀባይነት ለማግኘት የሚያመቸው መሳፍንቱ መጀመሪያ ተነጋግረውበት ከተቀበሉት ነው። ...(በሌላ አነጋገር) እኛ የፈለግነው የኢትዮጵያን ሕዝብ በመሣፍንቱ አማካይነት ለማነጋገር ነው። ስለዚህ መሣፍንቱን ለዕቅዳችንና ለዓላማችን መሣሪያ አደረግናቸው ማለት ይቻላል። (Markakis፣273)

ይህ ማለት ግን መሳፍንቱ ሁሉ ሳያቅማሙ ላዲሱ ሕገ መንግሥት ተገዥ ሆኑ ማለት አይደለም። ሳልዋጋ አልሞትም ካሉት መሳፍንት መካከል ዋነኛው የጎጃሙ ራስ ኃይሉ ተክለ ሃይማኖት ነው። አባቱ ምንም እንኳ በ1874 በእምባቦ ጦርነት ተሸንፎ ከማዕከላዊ ሥልጣን ተቀናቃኝነት ቢወገድም፣ በግዛቱ ያለውን ክብርና ሥልጣን አስከብሮ ለመቆየት ችሏል። እንግዲህ አሁን ሕገ መንግሥቱ ያዘለው አደጋ እምባቦ እንኳ ያላደረገውን ለማድረግ መቃጣቱ ነው።





3.32 የጎጃሙ ገዥ ራስ ኃይሉ ተክለ ሃይማኖት

ይህም ለኃይሉ የሚዋጥለት አልሆነም። በፖለቲካ ብልጠቱና አመቺ ጋብቻዎች በፈጠሩለት ሁኔታ ታግዞ ግዛቱን ለሠላሳ ዓመታት ያህል ከምላ ጉደል በነፃነት የመራው ኃይሉ፣ በተጨማሪም የገጠሩን ሕዝብ ያለርኅራኄ በመቅረጥና በከተማውም ንግድ በመሪነት በመሳተፍ ብዙ ሀብት ለማካበት በቅቷል። ተፈሪን በብልጠትም ሆነ እርቆ በማሰብ የሚፎካከረው አንድ መስፍን ቢኖር እሱው ኃይሉ ነበር። ስለዚህም ነው የሁለቱ ፍልሚያ «ብልጥ ለብልጥ» የሆነው።

በዚህም ተፈሪ ከነደጃች ባልቻ፣ ደጃች አባ ውቃውና ራስ ጉግሣ ጋር ካደረገው ትግል በዓይነቱ የተለየ ነው። ይሁን እንጂ በዚህ የረቀቀ የፖለቲካ ቁማር የማታ ማታ ኃይለ ሥላሴ ኃይሉ ራሱን ጠልፎ የሚጥልበት ወጥመድ ውስጥ ነው ያስገባው። ኃይሉ ባልጠግብ ባይነት በጎጃም ሕዝብ ላይ የጫነው የቀረጥ ሸክም ተቃውሞ ፈጠረበት። በተለይም ቤተ ክህነትንም ከዚህ የቀረጥ ጫና አለመማሩ ቀሳውስቱን አስቀይሞ ስለነበር ለኃይለ ሥላሴ ፀረ-ኃይሉ ፕሮፖጋንዳ ተስማሚ ሁኔታን ፈጠረለት። በመጨረሻ ለኃይሉ ውድቀት ዋነኛ ምክንያት የሆነው ፍቼ በእስር ላይ የነበረውን ኢያሱን ለማስመለጥ ሲያሴር መገኘቱ ነው። በዚህ ክስ እጁ ተይዞ ለፍርድ ቀርቦ የሞት ፍርድ ተፈረደበት። ኃይለ ሥላሴም እሱ ቢሞት ምን እጠቀማለሁ ብሎ ይመስላል ይልቅስ ሞቱ በእስር ተለውጦ እጅግ የሚያጓጓው የኃይሉ ሀብት ለመንግሥት ውርስ እንዲሆን በየነ።

ይህ የሆነው በ1924 ሲሆን ሁለት ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ንጉሠ ነገሥቱ ፊቱን ወደ ጅማ አባ ጅፋር አዞረ። ኀምሳ ዓመት ያህል ጅማን ሲያስተዳድር የነበረው ዳግማዊ አባ ጅፋር ከዚህ ዓለም በሞት እንደተለየ፣ ጅማ አባ ጅፋር ለምኒልክ በሰላም ከገበረችበት ጊዜ ጀምሮ የነበራትን የውስጥ አስተዳደር ነፃነት ተገፋ በማዕከላዊ መንግሥት ቁጥጥር ሥር ወደቀች። በዚህም



3.31 የ1923ቱ ሕገ መንግሥት አርቃቂ በጅሮንድ ተክለ ሐዋርያት

> ነው:: ይህንንም ተቀባይነት ለማግኘት የሚያመቸው መሳፍንቱ መጀመሪያ ተነጋግረውበት ከተቀበሉት ነው:: ...(በሌላ አነጋገር) እኛ የፈለግነው የኢትዮጵያን ሕዝብ በመሣፍንቱ አማካይነት ለማነጋገር ነው:: ስለዚህ መሣፍንቱን ለዕቅዳችንና ለዓላማችን መሣሪያ አደረግናቸው ማለት ይቻላል:: (Markakis፣273)

ይህ ማለት ግን መሳፍንቱ ሁሉ ሳያቅማሙ ላዲሱ ሕገ መንግሥት ተገዥ ሆኑ ማለት አይደለም:: ሳልዋጋ አልሞትም ካሉት መሳፍንት መካከል ዋነኛው የጎጃሙ ራስ ኃይሉ ተክለ ሃይማኖት ነው:: አባቱ ምንም እንኳ በ1874 በእምባቦ ጦርነት ተሸንፎ ከማዕከላዊ ሥልጣን ተቀናቃኝነት ቢወገድም፣ በግዛቱ ያለውን ክብርና ሥልጣን አስከብሮ ለመቆየት ችሏል:: እንግዲህ አሁን ሕገ መንግሥቱ ያዘለው አደጋ እምባቦ እንኳ ያላደረገውን ለማድረግ መቃጣቱ ነው::





3.32 የጎጃሙ ገዥ ራስ ኃይሉ ተክለ ሃይማኖት

ይህም ለኃይሉ የሚዋጥለት አልሆነም:: በፖለቲካ ብልጠቱና አመቺ ጋብቻዎች በፈጠሩለት ሁኔታ ታግዞ ግዛቱን ለሠላሳ ዓመታት ያህል ከሞላ ጐደል በነፃነት የመራው ኃይሉ፣ በተጨማሪም የገጠሩን ሕዝብ ያስርጎራጌ በመቅረጥና በከተማውም ንግድ በመሪነት በመሳተፍ ብዙ ሀብት ለማካበት በቅቷል:: ተፈሪን በብልጠትም ሆነ አርቆ በማሰብ የሚፎካከረው አንድ መስፍን ቢኖር እሱው ኃይሉ ነበር:: ስለዚህም ነው የሁለቱ ፍልሚያ «ብልጥ ለብልጥ» የሆነው::

በዚህም ተፈሪ ከነደጃች ባልቻ፣ ደጃች አባ ውቃውና ራስ ጉግሣ ጋር ካደረገው ትግል በዓይነቱ የተለየ ነው:: ይሁን እንጂ በዚህ የረቀቀ የፖለቲካ ቁማር የማታ ማታ ኃይለ ሥላሴ ኃይሉ ራሱን ጠልፎ የሚጥልበት ወጥመድ ውስጥ ነው ያስገባው:: ኃይሉ ባልጠግብ ባይነት በጎጃም ሕዝብ ላይ የጫነው የቀረጥ ሸክም ተቃውሞ ፈጠረበት:: በተለይም ቤተ ክህነትንም ከዚህ የቀረጥ ጫና አለመማሩ ቀሳውስቱን አስቀይሞ ስለነበር ለኃይለ ሥላሴ ፀረ-ኃይሉ ፕሮፖጋንዳ ተስማሚ ሁኔታን ፈጠረለት:: በመጨረሻ ለኃይሉ ውድቀት ዋነኛ ምክንያት የሆነው ፍቼ በእስር ላይ የነበረውን ኢያሱን ለማስመለጥ ሲያሴር መገኘቱ ነው:: በዚህ ክስ እጁ ተይዞ ለፍርድ ቀርቦ የሞት ፍርድ ተፈረደበት:: ኃይለ ሥላሴም እሱ ቢሞት ምን እጠቀማለሁ ብሎ ይመስላል ይልቅስ ሞቱ በእስር ተለውጦ እጅግ የሚያጓጓው የኃይሉ ሀብት ለመንግሥት ውርስ እንዲሆን በየነ::

ይህ የሆነው በ1924 ሲሆን ሁለት ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ንጉሠ ነገሥቱ ፊቱን ወደ ጅማ አባ ጅፋር አዞረ:: ኀምሳ ዓመት ያህል ጅማን ሲያስተዳድር የነበረው ዳግማዊ አባ ጅፋር ከዚህ ዓለም በሞት እንደተለየ፣ ጅማ አባ ጅፋር ለምኒልክ በሰላም ከገበረችበት ጊዜ ጀምሮ የነበራትን የውስጥ አስተዳደር ነፃነት ተገፋ በማዕከላዊ መንግሥት ቁጥጥር ሥር ወደቀች:: በዚህም



3.33 የትግሬው ገዥ ደጃች (ኋላ ራስ) ሥዩም መንገሻ

ግዛቶችን በማዕከላዊ መንግሥት ቁጥጥር ሥር የማድረጉ ሂደት ተጠናቀቀ ማለት ይቻላል። አብዛኛው የደቡብ ክፍል ቀደም ሲል በምኒልክ የግዛት ማስፋፋት ዘመን ከሸዋ የሄዱ አገረ ገዦች ተሹመውበታል። በሰሜኑ በኩል ወሎ ከሰገሌ በኋላ ቀስ በቀስ ወደ ማዕከሉ እየተሳበች መጥታ በመጨረሻ አስፋ ወሰን ኃይለ ሥላሴ ገዥ ሆኖ ሲሾምባት የቤተ መንግሥት ማድቤት ሆናለች። ከአንችም ጦርነት በኋላ ደግሞ በጌምድር ለኃይለ ሥላሴ ባለው ታማኝነት ለታወቀው ለራስ ካሣ ኃይሉ ተሰጥታለች፤ እሱም ሥልጣኑን ለልጁ ለወንድወሰን አስተላልፏል። ራስ ኃይሉ ተክለ ሃይማኖት እላይ እንዳየነው ለእስራት ሲበቃም ጎጃም ላይ ሌላ የንጉሠ ነገሥቱ የቅርብ ዘመድና ወዳጅ የሆነው ራስ እምሩ ኃይለ ሥላሴ ተሾመባት።

ከዚህም ባሻገር፤ የድኅረ 1933ቱን ሁኔታ የሚያበስር የጠቅላይ ግዛት አወቃቀር በሙከራ ላይ ነበር። ይኸውም «ሞዴል አውራጃዎች» ተብለው በታወቁት እንደ ጨርጨር ባሉ ሥፍራዎች የተጀመረው ነው። ጨርጨር በተከታታይ ተራማጅ ተብለው ለሚታወቁ አስተዳዳሪዎች (ራስ እምሩ፤ ሐኪም ወርቅነህና፤ በጆሮንድ ተክለ ሐዋርያት) ተሰጥታ የዘመናዊ አስተዳደር ላቦራቶሪ



ለመሆን በቅታለች። ከ1933 በኋላ በመላ ሀገሪቱ ለተዋቀረው የጠቅላይ ግዛት አስተዳደር ስልትም ፈር ቀዳለች።

በዚህ ሁሉ መሀል ከማዕከላዊው መንግሥት ቀጥተኛ ቁጥጥር ውጪ ሆኖ ለመቆየት የቻለው የትግራይ ግዛት ብቻ ነው። ሁለቱም የአፄ ዮሐንስ የልጅ ልጅ የሆኑት ራስ ሥዩም መንገሻና ራስ ጉግሣ አርአያ እንደኛው ምዕራብ ሁለተኛው ምሥራቅ ትግራይን ተከፋፍለው ከሞላ ጎደል በውስጣዊ ነፃነት ያስተዳድሩ ነበር። እነሱን ወደ ማዕከላዊ መንግሥት ለመሳብ የተሞከረው በቀጥተኛ አስተዳደራዊ ቁጥጥር ሳይሆን በጋብቻ መተሳሰር ነበር። በዚህም መሠረት ራስ ጉግሣ የኃይለ ሥላሴን የወንድም ልጅ የሻሸወርቅ ይልማን ሲያገባ፤ልጁ ኃይለ ሥላሴ ደግሞ የንጉሠ ነገሥቱን ልጅ ዘነበወርቅን አግብቶ ነበር። በሌላ በኩል ደግሞ የንጉሠ ነገሥቱ የበኩር ልጅና ኋላም አልጋ ወራሽ የሆነው የአስፋ ወሰን የመጀመሪያ ሚስት የራስ ሥዩም ልጅ ወለተ እሥራኤል ነበረች።

መንግሥት በግዛቶች ላይ ያለው ፖለቲካዊና አስተዳደራዊ ቁጥጥር በወታደራዊ አቅሙ ላይ ቀጥተኛ ተጽዕኖ ነበረው። ስለሆነም የተፈሪ የፖለቲካ የበላይነት እያደገ በመጣ ቁጥር የማዕከሉም ወታደራዊ ኃይል እንደዚሁ ያድግ ጀመር። ወታደራዊ ድርጅት አሁንም ግዛታዊ ወይም ክልላዊ ባሕሪውን ያልለቀቀ ቢሆንም ንጉሠ ነገሥቱ በሹሞቹ አማካይነት በክልላዊ ሠራዊት ላይ ማዘዝ ይችላል። ይሁን እንጂ ይህ ሁኔታ በተለይም የሰሜን ግዛቶችን በተመለከተ አለቅጥም ተጋኖ መቅረብ የለበትም። የኢጣልያ ወረራ እንደሚያሳየው ማዕከላዊው መንግሥት በነዚህ ግዛቶች ላይ የነበረው ወታደራዊ ሥልጣን ውሱን ነበር። ለምሳሌ ዘመዱን ጉግሣ ወሌን ከድቶ ለተፈሪ ያደረው የስሜኑ ደጃች አያሌው ብሩ የተመኘውን የጉግሣን ግዛት አለማግኘቱን ካወቀ በኋላ ልቡ በማዕከላዊው መንግሥት ላይ ሸፍቷል። ስለዚህም ጣልያኖችን የተቋቋመው በግማሽ ልብ ነበር፤ በመጨረሻም ወደነሱው ገብቷል። ጣልያኖችም የራስነት ማዕረግ ሰጥተው አዲስ በከለሉት የአማራ ግዛት ላይ ገዥ አድርገው ሾመውታል። ራስ ሥዩም መንገሻም የስሜኑ ግንባር ጦርነት ለኢትዮጵያ እንዳልተመረላት ካየ በኋላ ለጣልያኖች አድሯል። ከሁሉም በላይ ብዙ ጊዜ የሚጠቀሰው የደጃች ኃይለ ሥላሴ ጉግሣ በመጀመሪያው አጋጣሚ መክዳት ነው።

የወደፊቱን ወታደራዊ ሥርዓት በመጠቆም በኩልም ሊጠቀሱ የሚገባቸው ክንውኖች ነበሩ። በውጭ አገር ኤክስፐርቶች የሠለጠኑና በቀጥታ በማዕከላዊው መንግሥት የሚታዘዙ ወታደራዊ ክፍሎች ተመሥርተዋል። ከነዚህም መካከል ዋነኛው በጦርነቱ፤ በተለይም በማይጨው ውጊያ ላይ፤ስሙን ሊያስጠራ የቻለው የክብር ዘበኛ ነው። በትጋትና በቆራጥነት እነሱን ሊስተካከሉ የቻሉት በጦር ሚኒስትሩ በራስ ሙሉጌታ ይገዙ የሚመሩትና የዐድዋ መንፈስ ያልተለያቸው የቀድሞው የንጉሠ ነገሥቱ ወታደሮች ናቸው። የክብር ዘበኛን ጦር ያሠለጠነው በ1922 ወደ ኢትዮጵያ የመጣው የቤልጅግ አማካሪዎች ቡድን ነው። የክብር ዘበኛ በዚያን ወቅት ሦስት ባታሊዮን የእግረኛ ጦርና አንድ ባለ ከባድ መትረየስ ጦር ነበረው። አብዛኛዎቹ የጦር መኰንኖችም የፈረንሳይ ቁንጮ ወታደራዊ አካዳሚ በነበረው በሳን ሲር የሰለጠኑ ነበሩ። ይህን ዘመናዊ የጦር ድርጅት ከቀድሞው የንጉሠ ነገሥቱ ጦር ጋር የሚያገናኘው አንድ ሐረግ ነበር። እሱም ስድስት መቶ የሚያህሉ መሀል ሰፋሪዎች ወደዚሁ ክብር ዘበኛ ጦር



3.33 የትግሬው ገዥ ደጃች (ኋላ ራስ) ሥዩም መንገሻ

ግዛቶችን በማዕከላዊ መንግሥት ቁጥጥር ሥር የማድረጉ ሂደት ተጠናቀቀ ማለት ይቻላል:: አብዛኛው የደቡብ ክፍል ቀደም ሲል በምኒልክ የግዛት ማስፋፋት ዘመን ከሸዋ የሄዱ አገረ ገዦች ተሹመውበታል:: በሰሜኑ በኩል ወሎ ከሰገሌ በኋላ ቀስ በቀስ ወደ ማዕከሉ እየተሳበች መጥታ በመጨረሻ አስፋ ወሰን ኃይለ ሥላሴ ገዥ ሆኖ ሲሾምባት የቤተ መንግሥት ማድቤት ሆናለች:: ከአንችም ጦርነት በኋላ ደግሞ በጌምድር ለኃይለ ሥላሴ ባለው ታማኝነት ለታወቀው ለራስ ካሣ ኃይሉ ተሰጥታለች፤ እሱም ሥልጣኑን ለልጁ ለወንድወሰን አስተላልፏል:: ራስ ኃይሉ ተክለ ሃይማኖት እላይ እንዳየነው ለእስራት ሲበቃም ጎጃም ላይ ሌላ የንጉሠ ነገሥቱ የቅርብ ዘመድና ወዳጅ የሆነው ራስ እምሩ ኃይለ ሥላሴ ተሾመባት::

ከዚህም ባሻገር፣ የድኅረ 1933ቱን ሁኔታ የሚያበስር የጠቅላይ ግዛት አወቃቀር በሙከራ ላይ ነበር:: ይኸውም «ሞዴል አውራጃዎች» ተብለው በታወቁት እንደ ጨርጨር ባሉ ሥፍራዎች የተጀመረው ነው:: ጨርጨር በተከታታይ ተራማጅ ተብለው ለሚታወቁ አስተዳዳሪዎች (ራስ እምሩ፣ ሐኪም ወርቅነህና፣ በጅሮንድ ተክለ ሐዋርያት) ተሰጥታ የዘመናዊ አስተዳደር ላቦራቶሪ




ለመሆን በቅታለች:: ከ1933 በኋላ በመላ ሀገሪቱ ለተዋቀረው የጠቅላይ ግዛት አስተዳደር ስልትም ፈር ቀዳለች::

በዚህ ሁሉ መሀል ከማዕከላዊው መንግሥት ቀጥተኛ ቁጥጥር ውጪ ሆኖ ለመቆየት የቻለው የትግራይ ግዛት ብቻ ነው:: ሁለቱም የአፄ ዮሐንስ የልጅ ልጅ የሆኑት ራስ ሥዩም መንገሻና ራስ ጉግሣ አርአያ እንደኛው ምዕራብ ሁለተኛው ምሥራቅ ትግራይን ተከፋፍለው ከሞላ ጎደል በውስጣዊ ነፃነት ያስተዳድሩ ነበር:: እነሱን ወደ ማዕከላዊ መንግሥት ለመሳብ የተሞከረው በቀጥተኛ አስተዳደራዊ ቁጥጥር ሳይሆን በጋብቻ መተሳሰር ነበር:: በዚህም መሠረት ራስ ጉግሣ የኃይለ ሥላሴን የወንድም ልጅ የሸሸወርቅ ይልማን ሲያገባ፣ልጁ ኃይለ ሥላሴ ደግሞ የንጉሠ ነገሥቱን ልጅ ዘነበወርቅን አግብቶ ነበር:: በሌላ በኩል ደግሞ የንጉሠ ነገሥቱ የበኩር ልጅና ኋላም አልጋ ወራሽ የሆነው የአስፋ ወሰን የመጀመሪያ ሚስት የራስ ሥዩም ልጅ ወለተ እሥራኤል ነበረች::

መንግሥት በግዛቶች ላይ ያለው ፖለቲካዊና አስተዳደራዊ ቁጥጥር በወታደራዊ አቅሙ ላይ ቀጥተኛ ተጽዕኖ ነበረው:: ስለሆነም የተፈሪ የፖለቲካ የበላይነት እያደገ በመጣ ቁጥር የማዕከሉም ወታደራዊ ኃይል እንደዚሁ ያድግ ጀመር:: ወታደራዊ ድርጅት አሁንም ግዛታዊ ወይም ክልላዊ ባሕሪውን ያልለቀቀ ቢሆንም ንጉሠ ነገሥቱ በሹሞቹ አማካይነት በክልላዊ ሠራዊት ላይ ማዘዝ ይችላል:: ይሁን እንጂ ይህ ሁኔታ በተለይም የሰሜን ግዛቶችን በተመለከተ አለቅጥም ተጋኖ መቅረብ የለበትም:: የኢጣልያ ወረራ እንደሚያሳየው ማዕከላዊው መንግሥት በነዚህ ግዛቶች ላይ የነበረው ወታደራዊ ሥልጣን ውሱን ነበር:: ለምሳሌ ዘመዱን ጉግሣ ወሌን ከድቶ ለተፈሪ ያደረው የሰሜኑ ደጃች አያሌው ብሩ የተመኘውን የጉግሣን ግዛት አለማግኘቱን ካወቀ በኋላ ልቡ በማዕከላዊው መንግሥት ላይ ሸፍቷል:: ስለዚህም ጣልያኖችን የተቋቋመው በግማሽ ልብ ነበር፤ በመጨረሻም ወደነሱው ገብቷል:: ጣልያኖችም የራስነት ማዕረግ ሰጥተው አዲስ በከለሉት የአማራ ግዛት ላይ ገዥ አድርገው ሾመውታል:: ራስ ሥዩም መንገሻም የሰሜኑ ግንባር ጦርነት ለኢትዮጵያ እንዳልሠመረላት ካየ በኋላ ለጣልያኖች አድሯል:: ከሁሉም በላይ ብዙ ጊዜ የሚጠቀሰው የደጃች ኃይለ ሥላሴ ጉግሣ በመጀመሪያው እጋጣሚ መክዳት ነው::

የወደፊቱን ወታደራዊ ሥርዓት በመጠቆም በኩልም ሊጠቀሱ የሚገባቸው ክንውኖች ነበሩ:: በውጭ አገር ኤክስፐርቶች የሠለጠኑና በቀጥታ በማዕከላዊው መንግሥት የሚታዘዙ ወታደራዊ ክፍሎች ተመሥርተዋል:: ከነዚህም መካከል ዋነኛው በጦርነቱ፣ በተለይም በማይጨው ውጊያ ላይ፣ስሙን ሊያስጠራ የቻለው የክብር ዘበኛ ነው:: በትጋትና በቆራጥነት እነሱን ሊስተካከሉ የቻሉት በጦር ሚኒስትሩ በራስ ሙሉጌታ ይገዙ የሚመሩትና የዐድዋ መንፈስ ያልተለያቸው የቀድሞው የንጉሠ ነገሥቱ ወታደሮች ናቸው:: የክብር ዘበኛን ጦር ያሠለጠነው በ1922 ወደ ኢትዮጵያ የመጣው የቤልጅግ አማካሪዎች ቡድን ነው:: የክብር ዘበኛ በዚያን ወቅት ሦስት ባታሊዮን የእግረኛ ጦርና አንድ ባለ ከባድ መትረየስ ጦር ነበረው:: አብዛኛዎቹ የጦር መኰንኖችም የፈረንሳይ ቁንጮ ወታደራዊ አካዳሚ በነበረው በሳን ሲር የሰለጠኑ ነበሩ:: ይህን ዘመናዊ የጦር ድርጅት ከቀድሞው የንጉሠ ነገሥቱ ጦር ጋር የሚያገናኘው አንድ ሐረግ ነበር:: እሱም ስድስት መቶ የሚያህሉ መሀል ሰፋሪዎች ወደዚሁ ክብር ዘበኛ ጦር



3.34 የክብር ዘበኛ ጦር፣ 1928

እንዲገቡ መመልመላቸው ነው:: ዋናው የክብር ዘበኛ ጦር ሰፈር አዲስ አበባ ሲሆን፣ በዚሁ አምሳል የተደራጁ ክፍሉችም ባንዳንድ ግዛቶች (ለምሳሌ ባሌ፣ ሐረር፣ወለጋ) ይገኙ ነበር:: በ1927 ደግሞ በስዊድን ወታደራዊ ኤክስፐርቶች አማካሪነት የመጀመሪያው የጦር ትምህርት ቤት በሆለታ ተከፈተ:: ሆኖም ሦስት ዓመት የሚፈጅ የመጀመሪያው የሥልጠና ኮርስ ሳይፈጸም ኢጣልያ ኢትዮጵያን ወረረች:: ዕጩ መኰንኖቹም ወታደራዊ ሕይወታቸውን በመኰንንነት ሳይሆን በአርበኝነት እንዲጀምሩ ተገደዱ::

# ምዕራፍ አራት


# የኢጣልያ ወረራ (1928-1933)

## ጦርነት

ጣልያኖች በ1888 ዐድዋ ላይ ድል ከሆኑ በኋላ ለአጭር ጊዜ በሰሜን ምሥራቅ አፍሪቃ የሚከተሉትን የመስፋፋት ፖሊሲ እንደመግታት ብለው ነበር:: አዲስ የተሾመው ጠቅላይ ሚኒስትር ዲ ሩዲኒም ቀዳሚው ፍራንቼስኮ ክሪስፒ ያራምድ የነበረውን ፖሊሲ ሸሮታል:: ለቅኝ ግዛት ማስፋፊያ የተመደበው በጀት በግማሽ ተቀንሷል:: ከዐድዋ በፊት አንገቱን ደፍቶ የነበረው የፀረ ኰሎኒያሊስት ቡድንም አሁን የልብ ልብ አግኝቶ ኢጣልያ እስከናካቴው የአፍሪቃን ምድር ለቃ እንድትወጣ ለመጠየቅ ተዳፈረ:: ይህ ሁሉ ግን ለጊዜው ነበር:: ኢጣልያ ኢትዮጵያን ትታ አይሆንላትምና እንደገና ጥቅሟን ለማስጠበቅ ዲፕሎማሲያዊ ጥረቷን ቀጠለች:: እንዲያውም የሚገርመው ነገር ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ እርቀ ሰላም ወርዶ ኢጣልያ በኢትዮጵያ ሌጋሲዮን ለማቋቋም የመጀመሪያዋ አገር ሆነች:: ይህም ሊሆን የቻለው በከፊል ፌዴሪኮ ቺኪዚኮላን የመሰለ የበሰለ ዲፕሎማት ወደ ኢትዮጵያ በመላኳ ነው:: በሌላ ወገን ስናየው ግን የምኒልክና የኢጣልያ ግንኙነት (ባጠቃላይም የኢትዮጵያውያንና የጣልያኖች ግንኙነት ማለት ይቻላል) ፍቅርና ጠብን አቀላቅሉ የያዘ የመሆኑ ውጤት ነው::

ከእንግሊዝ ቀጥሎ ከኢትዮጵያ ጋር ረጅም የጋራ ድንበር ያሏቸው ቅኝ ግዛቶች የምታስተዳድረዋ ኢጣልያ ኢትዮጵያን ችል ብላ መኖር የምትችልም አልነበረችም:: ስለዚህ ቶሎ ብላ እርምጃዎቿን ከሌሉቱ ሁለት አጎራባች ቅኝ ገዥዎች፣ ማለትም ከፈረንሳይና ከእንግሊዝ፣ ጋር ማቀናጀት ጀመረች:: በ1899 ሦስቱ የተፈራረሙት ውልም የዚህ በኢትዮጵያ ላይ የነበረው የተቀናጀ ፖሊሲ የመጀመሪያው ውጤት ነው:: የውሉ ዋና ይዘት ኢጣልያ በኢትዮጵያ ላላት ጥቅም ቅድሚያ የሚሰጥ ነበር:: እንግሊዝና ፈረንሳይ የነበራቸው ቋሚ ዓላማዎች (ማለትም እንግሊዝ በዐባይ ሸለቆ፣ ፈረንሳይ በባቡሩ መሥመር) በግልፅ ሲብራሩ፣ ከኤርትራና ከኢጣልያ ሶማሊላንድ በስተጀርባ ያሉት የኢትዮጵያ ግዛቶች (ማለትም ሰሜንና ደቡብ ምሥራቅ ኢትዮጵያ) በጅምላው ለኢጣልያ ተከለሉ:: ይህ አልበቃም ብሉ የተናጠሉትን ሁለት ቅኝ ግዛቶቿን የማገናኘት መብቷ ተጠበቀላት:: ይህ ሊሳካ የሚችለው ሁለቱን ያለያየው የኢትዮጵያ ምድር ከኢጣልያ ሥር ሲውል እንደሆነ ሲታወቅ ውሉ ኢጣልያ ኢትዮጵያን ለመውረር ወይ ግዛቷን ለመቁረስ የሚያደፋፍር ነበር ማለት ይቻላል:: ለዚህም ነው አንድ የታሪክ ጸሐፊ ውሉን «ኢጣልያ በኢትዮጵያ ላይ ያላት ምኞት ማረጋገጫ ቻርተር» ብሉ የደመደመው:: (Baer፣6)

የኢጣልያ ፍላጎት ምን እንደሆነም በአንደኛው ዓለም ጦርነት ወቅት ገሃድ ወጣ:: ጦርነቱ በተጀመረ በዓመቱ የቃል ኪዳን መንግሥታቱ (ኢጣልያን ጨምሮ) ከድል በኋላ የጠላቶቻቸውን (ጀርመንና ቱርክ) ግዛቶች እንዴት እንደሚቃረጡ ሲያስሉ የኢጣልያ ትኩረት ሙሉ በሙሉ በአፍሪቃ ቀንድ ላይ ነበር:: የጠየቀችውም በአካባቢው ያለው የግዛትም ሆነ የኢኮኖሚ ጥቅም ድልድል ለሷ በሚያመች መንገድ እንደገና እንዲስተካከል ነው:: ዐይን ባወጣ



3.34 የክብር ዘበኛ ጦር፣ 1928

እንዲገቡ መመልመላቸው ነው። ዋናው የክብር ዘበኛ ጦር ሰፈር አዲስ አበባ ሲሆን፣ በዚሁ አምሳል የተደራጁ ክፍሎችም ባንዳንድ ግዛቶች (ለምሳሌ ባሌ፣ ሐረር፣ወለጋ) ይገኙ ነበር። በ1927 ደግሞ በስዊድን ወታደራዊ ኤክስፐርቶች አማካሪነት የመጀመሪያው የጦር ትምህርት ቤት በሆለታ ተከፈተ። ሆኖም ሦስት ዓመት የሚፈጅ የመጀመሪያው የሥልጠና ኮርስ ሳይፈጸም ኢጣልያ ኢትዮጵያን ወረረች። ዕጩ መኰንኖቹም ወታደራዊ ሕይወታቸውን በመኰንንነት ሳይሆን በአርበኝነት እንዲጀምሩ ተገደዱ።

## ምዕራፍ አራት

# የኢጣልያ ወረራ (1928-1933)

## ጦርነት

ጣልያኖች በ1888 ዐድዋ ላይ ድል ከሆኑ በኋላ ለአጭር ጊዜ በሰሜን ምሥራቅ አፍሪቃ የሚከተሉትን የመስፋፋት ፖሊሲ እንደመግታት ብለው ነበር። አዲስ የተሾመው ጠቅላይ ሚኒስትር ዲ ሩዲኒም ቀዳሚው ፍራንቼስኮ ክሪስፒ ያራምድ የነበረውን ፖሊሲ ሽሮታል። ለቅኝ ግዛት ማስፋፊያ የተመደበው በጀት በግማሽ ተቀንሷል። ከዐድዋ በፊት አንገቱን ደፍቶ የነበረው የፀረ ኰሎኒያሊስት ቡድንም አሁን የልብ ልብ አግኝቶ ኢጣልያ እስከናካቴው የአፍሪቃን ምድር ለቃ እንድትወጣ ለመጠየቅ ተዳፈረ። ይህ ሁሉ ግን ለጊዜው ነበር። ኢጣልያ ኢትዮጵያን ትታ አይሆንላትምና እንደገና ጥቅሟን ለማስጠበቅ ዲፕሎማሲያዊ ጥረቷን ቀጠለች። እንዲያውም የሚገርመው ነገር ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ እርቀ ሰላም ወርዶ ኢጣልያ በኢትዮጵያ ሌጋሲዮን ለማቋቋም የመጀመሪያዋ አገር ሆነች። ይህም ሊሆን የቻለው በከፊል ፌዴሪኮ ቺኮዲኮላን የመሰለ የበሰለ ዲፕሎማት ወደ ኢትዮጵያ በመላኳ ነው። በሌላ ወገን ስናየው ግን የምኒልክና የኢጣልያ ግንኙነት (በጠቃላይም የኢትዮጵያውያንና የጣልያኖች ግንኙነት ማለት ይቻላል) ፍቅርና ጠብን አቀላቅሉ የያዘ የመሆኑ ውጤት ነው።

ከእንግሊዝ ቀጥሎ ከኢትዮጵያ ጋር ረጅም የጋራ ድንበር ያሏቸው ቅኝ ግዛቶች የምታስተዳድረዋ ኢጣልያ ኢትዮጵያን ቸል ብላ መኖር የምትችልም አልነበረችም። ስለዚህ ቶሎ ብላ እርምጃዎቿን ከሌሎቹ ሁለት አጎራባች ቅኝ ገዥዎች፣ ማለትም ከፈረንሳይና ከእንግሊዝ፣ ጋር ማቀናጀት ጀመረች። በ1899 ሦስቱ የተፈራረሙት ውልም የዚህ በኢትዮጵያ ላይ የነበረው የተቀናጀ ፖሊሲ የመጀመሪያው ውጤት ነው። የውሉ ዋና ይዘት ኢጣልያ በኢትዮጵያ ላላት ጥቅም ቅድሚያ የሚሰጥ ነበር። እንግሊዝና ፈረንሳይ የነበራቸው ቋሚ ዓላማዎች (ማለትም እንግሊዝ በዐባይ ሸለቆ፣ ፈረንሳይ በባቡሩ መሥመር) በግልፅ ሲብራሩ፣ ከኤርትራና ከኢጣልያ ሶማሊላንድ በስተጀርባ ያሉት የኢትዮጵያ ግዛቶች (ማለትም ሰሜንና ደቡብ ምሥራቅ ኢትዮጵያ) ለጅምላው ለኢጣልያ ተከለሉ። ይህ አልበቃም ብሎ የተናጠሉትን ሁለት ቅኝ ግዛቶቿን የማገናኘት መብቷ ተጠበቀላት። ይህ ሊሳካ የሚችለው ሁለቱን ያለያየው የኢትዮጵያ ምድር ከኢጣልያ ሥር ሲውል እንደሆነ ሲታወቅ ውሉ ኢጣልያ ኢትዮጵያን ለመውረር ወይ ግዛቷን ለመቁረስ የሚያደፋፍር ነበር ማለት ይቻላል። ለዚህም ነው አንድ የታሪክ ጸሐፊ ውሉን «ኢጣልያ በኢትዮጵያ ላይ ያላት ምኞት ማረጋገጫ ቻርተር» ብሎ የደመደመው። (Baer፣6)

የኢጣልያ ፍላጎት ምን እንደሆነም በአንደኛው ዓለም ጦርነት ወቅት ገሃድ ወጣ። ጦርነቱ በተጀመረ በዓመቱ የቃል ኪዳን መንግሥታቱ (ኢጣልያን ጨምሮ) ከድል በኋላ የጠላቶቻቸውን (ጀርመንና ቱርክ) ግዛቶች እንዴት እንደሚቃረጡ ሲያስሉ የኢጣልያ ትኩረት ሙሉ በሙሉ በአፍሪቃ ቀንድ ላይ ነበር። የጠየቀችውም በአካባቢው ያለው የግዛትም ሆነ የኢኮኖሚ ጥቅም ድልድል ለሷ በሚያመች መንገድ እንደገና እንዲስተካከል ነው። ዐይን ባወጣ